# ማውጫ ገፅ

I መግቢያ-----------------------------------------------------------------------------------2

**ክፍል አንድ**

1. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዳራና ገጽታዎች----------------------------------------- 5

   1.1. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዳራ------------------------------------------5

   1.2. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ትርጉም --------------------------------------6

   1.3. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት-----------------------------------------------6

**ክፍል ሁለት**

2. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሂደትን ማመቻቸት----------------------------------------7

   2.1 የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተሳታፊ ህፃናት ባህርያት --------------------7

   2.2 የጥሩ አመቻች ባህርይ---------------------------------------------------------------------8

   2.3 በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሂደት ማመቻቸት-------------------------------10

**ክፍል ሶስት**

3. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ክፍሎችን ማመቻቸት-------------------------------------16

   3.1 በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች ማመቻቸት--17

   3.1.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋን የማስተማር ሂደት ማመቻቸት--------------------------17

   3.1.2. የእንግሊዝኛን ቋንቋን የማስተማር ሂደት ማመቻቸት-------------------------20

   3.1.3. የአካባቢ ሳይንስ ትምህርትን የማስተማር ሂደት ማመቻቸት----------------31

   3.1.4. የሂሳብ ትምህርትን የማስተማር ሂደት ማመቻቸት--------------------------63

**ክፍል አራት**

4. በክፍል ውስጥ ህፃናት ተማሪዎችን በማነቃቃትና በማትጋት የማመቻቸት ስልቶች ማስተማር------------------------------------------------------------------------------81

**ክፍል አምስት**

5. በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ክፍሎች የመማር ማስተማር ሂደት አደረጃጀትና አመራር-------------------------------------------------------------------------------83

**ክፍል ስድስት**

6. አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም------------------------------------------------------------------------ 85

6.1. አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዕቅድ ምንነትና አስፈላጊነት-------------- 85

6.2. የትምህርት መርሃ -ግብር--------------------------------------------------------------86

6.3. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም-------------------------------------88

**ክፍል ሰባት**

7. አማራጭ የትምህርት መስጫ ጣቢያ የሥራ ዕቅድ አዘገጃጀት------------------------- 90

7.1. የትምህርት ቤት መረጃ አያያዝ---------------------------------------------------- 92

7.2. የመረጃ አይነቶች------------------------------------------------------------------ 94

ዋቤ መፃህፍት------------------------------------------------------------------------------------ 98

# መግቢያ

## ሀ/ የማንዋሉ አስፈላጊነት

በሀገራችን አዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በ1986 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ሲወጣ በዋናነት ያተኮረባቸው ዐበይት ጉዳዮች የትምህርት ተደራሽነትን፣ፍታዊነትን፣ አግባብነትን ፣ ብቃት እና ጥራትን በላቀ ደረጃ ማሻሻልን ነው፡፡ በዚሁ ረገድ እጅግ ከፍተኛ ለውጦች የታዩ መሆናቸው አይካድም ለአብነትም ያህል በ2000 ዓ.ም በሀገሪቱ የነበሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥር 23, 354 ሲሆን በ2004 ዓ.ም 29, 482 ናቸው፡፡ በተመሳሳይ የንጽጽር ጊዜያት ውስጥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር ከ 15, 340,788 ወደ 16, 989,784 ከፍ ብሏል፡፡ እንደዚሁም የአንደኛ ደረጃ መምህራን ቁጥር ከ 253, 629 ወደ 321, 894 ከፍ ብሏል፡፡

በተመሣሣይ ጊዜያት የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር ከ 637, 243 ወደ 715, 968 ከፍ ብሏል፡፡ ይህም ሲሰላ ከአራት እስከ አምስት በመቶ ለአንደኛ ደረጃ የትምህርት ሽፋን አበርክቷል፡፡

በዚሁ መሠረታዊ ትምህርት የማስፋፋት እንቅስቃሴ ውስጥ መደበኛ ያልሆነ (Non-formal) ትምህርት የራሱ የሆነ አስተዋፆ አበርክቷል፡፡ በአጠቃላይ በተለያዩ ደረጃዎች የሚሠጡትን ትምህርትና ስልጠናዎች በስፋትና በጥራት መቀጠል አስፈላጊ መሆኑ ይታመንበታል ፡፡ በተለይም ለቀጣይ ትምህርት (Lifelong learning) መሠረት የሆነውን መሠረታዊ ትምህርትን ከሀገር ልማትና ከምእተ ዓመቱ የልማት ግቦች አኳያ ለማጠናከር አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን (alternative basic education) በከተማና በገጠር በተለያዩ ምክንያቶች የመደበኛ ትምህርት ዕድል ያላገኙትን ህፃናት (out- of- school children) እንዲሳተፉ እየተደረገ ነው፡፡ ለትምህርቱም መሣካት ከፍተኛ አስተዋፆ ካላቸው ጉዳዮች አንድ የአመቻች የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዓላማዎችን፣ሥርዓተ ትምህርቱንና የተሳታፊዎች ባህርያት፣ የትምህርት ፍላጐታቸውንና አቀባበል፣ እንዲሁም የተለያዩ አሣታፊ የማስተማር ዘዴዎችን ጠንቅቀው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመሆኑም የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አመቻች ይህንን የማስተማሪያ ማኑዋል በደጋፊ ሰነድነት መጠቀም ይችሉ ዘንድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

**ለ/ የማኑዋሉ ዝግጅት መሠረት ያደረጋቸው መርሆዎች** (principles)

ይህ ማኑዋል አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን የሚያስተምሩ አመቻች የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አቀራረብን ጠንቅቀው እንዲያውቁና የተሳታፊ ህፃናትን የኑሮ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ማመቻቸት እንዲችሉ የተዘጋጀ ነው ፡፡ ከዚህ አኳያ በዚህ ማኑዋል ዝገጅት ትኩረት የተደረገባቸው መርሆዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሀ) ለህፃናት የሚስማማ የመማር ማስተማር ስልት መከተል ፡፡

ለ) የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተሳታፊ ህፃናትን የኑሮ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የትምህርት ጊዜውን መወሰን

ሐ) የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተሳታፊ ህፃናትን የመማር ሂደት ማነቃቃትና ማትጋት

መ) አካቷዊነቱ (Inclusiveness)

# ክፍል አንድ

## 1. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርተ ዳራና ገጽታዎች (Background and Features)

**በዚህ ክፍል ሥር የተካተቱ ንዑሳን ርዕሶች ፡-**

- ✓ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዳራ
- ✓ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ትርጉም
- ✓ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ገጽታዎች የሚሉ ናቸው፡፡

**የዚህ ክፍል ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ፡-

- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዳራን ለይተው ያውቃሉ፡፡
- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ትርጉምና ገጽታዎችን ይገልፃሉ፡፡

### 1.1 የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዳራ (Background)

ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ልማት ትምህርት ቁልፍ ሚና አለው፡፡ በሥራ የሚያምኑ ታታሪና ብቁ ዜጎችን በሁሉም መስክ ለማፍራት፣ የአዳዲስ ቴክኖሎጂ ውጤቶችንና ሳይንሳዊ ግኝቶች ህብረተሰቡን ለማስተዋወቅ ትምህርት በመሣሪያነት ያገለግላል፡፡

በ 1986 ዓ.ም ተቀርፆ የወጣው የሀገራችን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲም ጥራት ያለው ትምህርትን ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ለማዳረስ ባለው ዓላማ በርካታ ለውጦች ታይተዋል፡፡ የትምህርት ሽፋን በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ፣ በከፍተኛ ትምህርትና በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና መስኮች እጅግ የጨመረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም ረገድ መደበኛ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማት በብዛት እንዲሳተፉ ተደርገዋል፡፡

በተለይ ዕድሜያቸው ለትምህርት ደርሶ እያለ በተለያዩ ምክንያት በመደበኛው ትምህርት መሣተፍ ያልቻሉትን ህፃናት ሀገራችን አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት (Alternative Basic Education) ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ ነች፡፡ ዛሬ ከ 6-7% የሚሆነውን የአንደኛ ደረጃ ተሳትፎ የሚሸፍነው የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ነው፡፡ ይህም በከተማ፣ በገጠር፣ በተለይም በአርብቶ አደሩ አካባቢ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ

ህፃናት ማንበብ፣ መፃፍና ማስላት ብቻ ሳይሆን ወደ መደበኛው ትምህርት ቤት በመግባት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ዕድል ተመቻችቶላቸዋል፡፡

**አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት፡-**

- ትምህርት እንዳለ "ሰብአዊ መብት" የሚለውን የተባበሩት መንግስታት ሠነድ ለማረጋገጥ ጠቀሜታው የጐላ ነው፡፡
- ሀገራችን የፈረመቻቸውን የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ለማሳካት ትምህርት ቁልፍ ሚና ይጫወታል ፡፡

## 1.2. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ትርጉም

አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መደበኛ ካልሆነው የትምህርት አሠጣጥ አካል ሲሆን ዕድሜያቸው ከ 7-14 ዓመት ሆኖ በተለያዩ ምክንያቶች የመደበኛው የትምህርት ዕድል ማግኘት ያልቻሉ ህፃናትን እንደዕድሜቸው በሦስት ወይንም በአራት ዓመታት ከጨረሱ በኋላ ወደ መደበኛው ትምህርት ተመዝነው 5ኛ ክፍል መሸጋገር የሚችሉበት ሥርዓት ነው፡፡

## 1.3. የአማሪጭ መሠረታዊ ትምህርት ገጽታዎች

አማራጭ መሠረዊ ትምህርት የሚከተሉት ዋና ዋና ገጽታዎች አሉት፡፡

- የተሳታፊ ተማሪዎችን የአኗኗር ሁኔታ ከግምት ያስገባል፡፡
- የትምህርት አሰጣጡ ቦታና ጊዜን ፣አካባቢን ፣ማህበራዊ ፣ባህላዊና የተፈጥሮ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሂደትን ማመቻቸት

**በዚህ ሥር የተካተቱ ንዑሳን ርዕሶች የሚከተሉት ናቸው፡-**

- ✓ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተሳታፊ ህፃናት ባህሪያት
- ✓ የጥሩ አመቻች ባህርያት፡
- ✓ በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሂደት የማመቻቸት ዘዴዎች

**የዚህ ክፍል አላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ፡-

- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተሳታፊ የህፃናትን ባህሪያት ያውቃሉ፤
- የጥሩ አመቻች ባህሪያትን ይለያሉ ፤
- በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የማስተማር ሂደት የተለያዩ የማመቻቸት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡

### 2.1. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተሳታፊ ህፃናት ባህሪያት

**የዚህ ንዑስ ክፍል አላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ፡-

- የትምህርቱ ተሳታፊ ህፃናቶች ባህሪያት ጠንቅቀው ያውቃሉ
- የጥሩ አመቻች ባህርያትን ይለያሉ፡፡

በዚህ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ተሳታፊ ህፃናት እንደማንኛውም በህፃንነት ዕድሜ ውስጥ እንደሚገኙ ህፃናት ሁሉ ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው ቢሆንም በተወሰነ መልኩ ግን ከአካባቢያቸው የአኗኗር ሁኔታ ከማህበራዊና ባሕላዊ ሁኔታዎች አንፃር ሲታይ ለየት ያሉ ባህርያት ሊኖራቸው እንደሚችል ይታመናል፡፡ ስለዚህ ተሳታፊ ህፃናቱ የሚገኙባቸው አውዶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- አብዛኛውን ጊዜ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢ ያሉ የአማራጭ ትምህርት ተሳታፊ ህፃናት ለረጅም ጊዜ በአንድ አካባቢ ቆይተው የመደበኛ ትምህርት ተጠቃሚ የመሆን እድላቸው ዝቅተኛ መሆን፡፡

- የዚህ ትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊ ህፃናት በከተማ አካባቢ ከሆነ በወላጆች ገቢ ማነስ፣ የሚያሳድግ ወላጅ ወይንም የሚረዳ ዘመድ ባለመኖር የተነሳ መደበኛውን ትምህርት ሊካፈሉ ያልቻሉ ህፃናት መኖር፡፡
- በተለይም ራሳቸውን ለመርዳትና ለማስተዳደር የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት የዕለት ኑሮአቸውን ለማሸነፍ የሚተጉ ህፃናት በመደበኛው የትምህርት መርሐ ግብር ሊሣተፉ ያልቻሉ በከተማም ሆነ በገጠር የሚገኙ

**በአጠቃላይ እነዚህ ህፃናት የሚከተሉትን ባህርያት ያሣያሉ፡፡**

- በራስ የመተማማን ስሜትና ዝንባሌአቸው ዝቅተኛ የሆኑ ናቸው፡፡
- ከዕድሜያቸው አንፃር ሲታይ ብዙ የህይወት ተሞክሮ ወይንም የገጠመኝ ክምችት የሌላቸው ናቸው፡፡
- ለመማር ያላቸው ዝግጅትና ጉጉት በአብዛኛው ከአካባዊ ዕድገትና ከቤተሰብ ወይንም ህብርተሰብ ግፊት የሚከሰት ነው፡፡
- የሚማሩትም በአብዛኛው ወዲያውኑ ሥራ ላይ ለማዋል ሣይሆን ለወደፊት የወጣትነትና ጐልማሳነት ዘመን ላይ ሊጠቀሙበት ያስባሉ፡
- በማማር ማስተማር ወቅት በትምህርት ይዘት ላይ ያተኩራሉ፡
- በአንድ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ በሚገኙ ህፃናት መካከል ልዩነቶች /የፆታ፣ የትምህርተ አቀባበል ደረጃ ወዘተ/ ስለሚኖር እነዚህን ልዩነቶች(individual differences) በሚገባ ማጤንና አስፈላጊውን እገዛ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡
- ህፃናትን ማበረታታትና አግባብነት ያለው እንክብካቤ ይሻሉ፡፡
- የህፃናት የክፍል ውስጥ ባሕርይ በቤተሰባዊ የአኗኗር ሁኔታና ባህርይ ተፅኖ ውስጥ ሊሆን ይችላል ፡፡
- የህፃናት የትምህርት አሰጣጡ ማራኪ ካልሆነ የመከታተል ፍላጎታቸው ዝቅተኛ ነው፡
- ህፃናት ሲማሩ በራሳቸው (Independently) የመሥራት ፍላጎት ያሳያሉ ነገር ግን ከተወሰነ ሙከራ በኋላ የጐልማሳውን /መምህር ወይንም ቤተሰብ/ ድጋፍ ይሻሉ፡፡

## 2.2. የጥሩ አመቻች ባህርይ

### የትምህርቱ ዓላማዎች

አመቻቾች ይህን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ፡-

- የጥሩ አመቻች ባህርያትን ይዘረዝራሉ፡፡
- የህፃናትን ባህርይ ባገናዘበ መልኩ የትምህርት አሰጣጡን ያመቻቻሉ፡፡

በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሐ ግብር ውስጥ የሚገኙ ህፃናትን በማነቃቃትና በማበረታታት የተመደበላቸውን ትምህርት በአግባቡ ተከታትለው እንዲያጠናቅቁ ማስቻል እንዲሁም ወደሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ በመሸጋገር ለህይወታቸው ጠቃሚ የሆነውን ዕውቀት፣ክህሎትና እሴቶች እንዲቀስሙና እንዲያዳብር ማድረግ ከአመቻች በከፍተኛ ደረጃ ይጠበቃል፡፡

ጥሩ አመቻች ተሳታፊ ህፃናትን በመማር ማስተማሩ ሂደት ሀሳባቸውን እንዲገልፁ፣ እንዲጠይቁ፣ እንዲከራከሩ እንዲሁም የሌሎች ተሳታፊዎችን ሀሳብ እንዲያደምጡ ያበረታታሉ፡፡

በተለይ ህፃናት ተማሪዎች ትምርትን እንደቋሚ ሥራቸው የሚቆጠር በመሆኑ አመቻች ሁልጊዜ ትምህርትን የሚያፈቅሩ ንቁ ዜጐች እንዲሆኑ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ማስታወሻ፡-

አንኳር ነጥቦች ለአመቻች፡

በመማር ማስተማሩ ሂደት ህፃናት ተማሪዎችን ለማነቃቃትና ለማትጋት አመቻች፡-

- ለትምህርት መርሐ ግብሩ ስኬት ከፍተኛ ተነሳሽነት ማሳየት ይኖርባቸዋል
- የሚጐድላቸውን የመለየትና የማመቻቸት ዕውቀትና ክህሎት በየጊዜው ራሳቸውን በመገምገም መለየትና የማሻሻያ ዘዴዎችን መቀየስና መተግበር ይጠበቅባቸዋል ፡፡
- የህፃናት ተማሪዎች የግብብነት ክህሎት(Communication Skills) እንዲዳብር እገዛ ማድረግ አለባቸው፡፡
- ህፃናት ተማሪዎች ሳይፈሩ የመጠየቅ፣ የመመለስና ሃሳባቸውን የመግለፅ፣ ልምድ እንዲያዳብሩ ማበረታታትና ማነቃቃት አስፈላጊ ነው ይህም በራሳቸው የመተማመን ዝንባሌን ያሳድጋል ፡፡
- አግባብነት ያላቸውን የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች በማዘጋጀት ፣ እንዲሁም ህፃናት ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ሠርተው የማሳየት ልምድ እንዲኖራቸው ማድረግ
- ለመማር ማስተማሩ ሂደት ከልብ የመነጨ አክብሮትና ዝንባሌ ማሳየት፡
- ሌሎች የልማት ዘርፍ ባለሙያዎችን በማማከርና በመጋበዝ ስለጤና፣ ስለአካባቢ ጥበቃ፣ ስለግብርና ወዘተ በሥርአተ ትምህርቱ ውስጥ ከተካተቱ ርዕሦች ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ባለው መልኩ የበለጠ ዕውቀት እንዲቀስሙ ማድረግ
- የህፃናት ተማሪዎችን መረጃ አያያዝ ሥርአትን በሚገባ ጠንቅቆ ማወቅ/
- ከማዕከሉ አመራር ኮሚቴ (center management committee) ጋር በየጊዜው በመገናኘት ወወያየትና የማማር ማስተማሩን ሥራ ማጠናከር\

- **በተለይ ሴት ህፃናት ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ከቤተሰብ፣ ከማዕከሉ አመራር ኮሚቴና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርብ መወያየት የሴት ተማሪዎችን ትምህርት** (girls' education ) **ማበረታታት ይገባል፡፡**

## 2.3. በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርተ ሂደት የማመቻቸት ዘዴዎች

### የንዑስ ርዕሱ ዓላማዎች

አመቻቾች ይህን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡
- የአማራጭ መሠረታዊ ተሳታፊዎችን ማትጋት ይችላሉ፡፡

አመቻቾች የተለያዩ የማመቻቸት/የማስተማር ዘዴዎችን የመጠቀም ዕውቀት፣ ክህሎትና ዝንባሌ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የሚከተሉትን የማስተማር ዘዴዎች  አመቻች ሊጠቀሙ የሚችሉ ሲሆን የእነዚህም ዘዴዎችና ቴክኒኮች ጠንካራና ደካማ ጐኖችን ለይተው ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

(1) **በውይይት የማስተማር ዘዴ** (the discussion mathod) በትምህርት ቤቶች አሣታፊ የማስተማር ሥነ-ዘዴዎችን የመጠቀም አስፈላጊነት የሀገራችን የ1986 ዓ.ም የትምህርትና ሥልጠና ፓሊሲ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይህንንም እውን ለማድረግ ከሚያስችሉ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ በውይይት የማስተማር ዘዴ ነው፡፡

<u>ጠንካራ ጐኖች፡-</u>

በውይይት የማስተማር ዘዴ ህፃናት ተማሪዎች፡-

- ሀሳባቸውን የመግለጽ ልምድ እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡
- ከክፍል አቻ ተማሪዎች ጋር አብሮ የመሥራት ፍላጉትን (team spirit) እንዲያዳብሩ ይጠቅማል ፡፡
- የሌሎችን ሀሳብ የማዳመጥ ክህሎት (Listening skills)ለማዳበር ይጠቅማቸዋል፡፡
- ችግሮችን የመተንተንና የጋራ መፍትሄ የመፈለግ ዕውቀትን ፣ ክህሎትንና ዝንባሌን እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡
- የአመራር ክህሎትን (leadership skills) እንዲያዳብር ያደርጋል

**ደካማ ጎኖች፡-**

- ውይይት እየሠፋ ሲሄድ ህፃናት ተማሪዎች ከውይይቱ ርዕስ ሊያፈነግጡ ይችላሉ፡፡
- ብዙ ጊዜን ይጠይቃል (time consuming)
- አንዳንዴ ጥቂት የውይይቱ ተሳታፊዎች ብቻ ሊቆጣጠሩት ይችላሉ፡፡

በውይይት ወቅት አመቻቾች የተሳሳቱ አካሄዶች ሲታዩ ማስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡ አመቻቾች በውይይት ወቅት የውይይቱ ተሳታፊዎች ሁሉ ሀሳባቸውን የመግለጽ ዕድል ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

**ማስታወሻ**

**አመቻቾች፡-**

- የውይይቱ ርዕስ፡ የህፃናት ተማሪዎች ችሎታ የሚመጥን እጥር ምጥን ያለ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም እንዲዘጋጁበት ቀደም ተብሎ ቢነገራቸው ይመረጣል፡፡
- በቅድሚያ የውይይቱን ዓላማና ከውይይቱ በኋላ እያንዳንዱ ተሳታፊ ህፃናት ተማሪ ከውይይቱ ርዕስ ሊጨበጥ የሚችለውን ግንዛቤ ማስፈር ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የክፍል ወንበሮችና ጠረጴዛዎችን ለውይይት አመቺ በሆነ መልክ ማደርጀት
- አንድ የውይይቱ ተሣታፊ ህፃን ተማሪ የሰጠው ሃሳብ ለሌላው ተማሪ ግልፅ ካልሆነለት ሀሳብ ላይ ማብራሪያ በመስጠት ግልፅ እንዲሆንለት ማገዝ
- በመጨረሻም የተነሱትን ሀሳቦችንና የተገኙትን የመፍትሔ ሀሳቦች በማሰባሰብ ጨምቆ በማውጣትና ከሥርዓተ-ትምህርቱ ዓላማዎችና ጠቀሜታ ጋር አዛምዶ ማጠቃለያ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
- በውይይቱ ወቅት ምንም ዓይነት ተሳትፎ የማያደርጉትን ተማሪዎች እንዲሳተፉ መገፋፋት(prompting)፡፡ ከዚያም አልፎ የመሳተፍ ዝንባሌ የማያሳዩ ከሆነ ለብቻ ቀርቦ ማነጋገር፣ ማበረታታት፣ ማነቃቃት አስፈላጊ ነው፡፡

(2) **በሠርቶ ማሳየት የማስተማር ዘዴ** ( Demonstration ,method)

ይህ የማስተማር ዘዴ ህፃናት ተማሪዎች በገለፃ የሰሙትን በተግባር ተሠርተው እንዲያዩ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም በተግባር ያዩትን እነርሱ ራሳቸውም በመስራት በተግባር እንዲለማመዱት ይረዳል፡፡

**<u>ጠንካራ ጎኖች</u>፡-**

- ፃናት ተማሪዎች የሰሙትን በተግባር ተሰርቶ በአይናቸው እንዲያዩትና በእጃቸው እንዲዳስሱት ይጠቅማል፡፡
- የመሰላቸት ዕድልን ይቀንሣል፡፡

**<u>ደካማ ጎኖች</u>፡-**

- በሠርቶ ማሣያ የማስተማር ዘዴ መጠቀም ሰፋ ያለ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ፣
- አንዳንድ የሠርቶ ማሣያ ሥራ/ዝግጅት/ ከአመቻቹ ውጪ ሌላ ባለሙያ የሚያስፈልገው መሆኑ፣
- ለአንዳንድ የሠርቶ ማሣያ ሥራ የተለያዩ መሣሪያዎች የሚያስፈልጉ መሆኑን
- አንዳንድ ለሠርቶ ማሣያ የሚውሉ መሣሪያዎች ከቦታ ቦታ በቀላሉ ማንቀሳቀስ አስቸጋሪ ሊሆን መቻሉ፡፡
- በጣም ትንሽ ነገር በክፍል ውስጥ አመቻች ለማሳየት ሲሞክር ከኋላ የተቀመጡት ተማሪዎች ላያዩት ይችላሉ፡፡
- አንዳንድ ጊዜ ለአመቻቹ የሚመቸው የሠርቶ ማሣያ ፍጥነት ለህፃናት ተማሪዎች ላይመች ይችላል፡፡

**በሠርቶ ማሳየት የማስተማር ቴክኒክ፡-**

በሠርቶ ማሣያ ዘዴ አንድ ነገር ለማስተማር ከተፈለገ የሚከተሉትን የአሠራር ደረጃዎች ማስተዋል አስፈላጊ ነው፡፡

- በቅድሚያ ስለሠርቶ ማሣያው መግለጽ (explanation)
- ተሳታፊ ህፃናት ተማሪዎቹ እንዲያዩትና እንዲረዱት ማድረግ
- ተሳታፊ ህፃናት ተማሪዎቹ ራሳቸው ሰርተው እንዲያሳዩ ማድረግ
- ህፃናት ተማሪዎቹ የሚሠሩትን መከታተል (Supervision)
- ህፃናት ተማሪዎች ሠርተው ያሣዩትን መገምገም (evaluation)

(3) **ሚና በማጫወት የማስተማር ዘዴ** (Role playing method) ይህ የማስተማር ዘዴ ለባህርይ ለውጥ ጠቃሚ የሆነ ገፀ ባህርይን ሚና ወስደው ተማሪዎች እንዲጫወቱ በማድረግ የሚፈፀም ዘዴ ነው፡፡

ከድራማ የሚለይበት ዋነኛ ነጥብ ህፃናት ተማሪዎች እቤታቸው ሆነው አጥንተው ተዘጋጅተውበት በመምጣት ሣይሆን ገፀ ባህርይውን የሚጫወቱት ወዲያውኑ (spontaneously) አመቻቹ ሁኔታውን በክፍል ውስጥ እንዲያሣዩ ሲጠይቃቸው ነው፡፡ በውስጡም ምልከታን (Observation) ፣ውይይትን (discussion) እና ትንታኔን (analysis) ማድረግን ይጠይቃል፡፡

<u>ጠንካራ ጎኖች</u>፡-

- አንድ ህፃን ተማሪ ሚናን ለመጫወት ያለውን ችሎታ ለመረዳት ይጠቅማል፡
- በቀጥታ ከዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ሰዎች እንዴት መግባባትን እየፈጠሩ እንደሚያከናውኑ ያንፀባርቃል፡፡
- ህፃናት ተማሪዎች በተግባር እንዲማሩ ይረዳል፡፡
- ህፃናት የእርስ በርሳቸውን ፍላጎት እንዲረዱ ይረዳል (interpersonal Skills)
- የአስተሳሰብና አመለካከት ለውጥ ለማምጣት ይረዳል፡፡

<u>ደካማ ጎኖች</u> ፡-

- ተማሪዎች በቀጥታ እያዩ እንዲማሩ እንጂ እንዲያነቡ ወይንም በገለፃ እንዲወያዩና በገለፃ እንዲሰሩ እምብዛም አይረዳም፡፡

**(4) በጥያቄና መልስ የማስተማር ዘዴ (Questioning and answering method)**

ይህ የማስተማር ዘዴ አመቻቹ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲያስቡ (thinking) እና እንዲረዱት (Understanding) የሚያደርግበት ዘዴ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪው ለመማር ሲመጣ ይዞ የመጣውን ዕውቀትና ክህሎት (entry competence) ለመገምገም ይጠቅማል፡፡

በጥያቄና መልስ የማስተማር ዘዴ፡-

ሀ) ስለተፈፀሙ ድርጊቶች/ ጉዳዮች መጠየቅ ሊሆን ይችላል፡፡

ለ) ችግር ፈቺ የሆነ አስተያየት (Problem Solving questioning) ሊሆን ይችላል፡፡

**ጠንካራ ጎኖች፡-**

- ህፃናት ተማሪዎችን ለማነቃቃት (stimulating) ይጠቅማል፡፡
- ህፃናት ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይረዳል (active parrticipation)

- አመቻቾች ህፃናት ተማሪዎችን ያልገባቸውን ነገር በጊዜ እንዲለዩ ይረዳል ፡፡
- ህፃናት ተማሪዎች ያላቸውን ዕውቀት፣ ክህሎትና ዝንባሌ ለመረዳት ይጠቅማል፡፡
- አመቻቾች ስለትምህርት ጥራት እንዲገነዘቡ የሚያስችል ግብረ መልስ (feedback) ይሰጣቸዋል፡፡

**ማስታወሻ**

አንኳር ነጥቦች ለአመቻች፡-

- ግልፅና አጠር ያለ ጥያቄ መጠየቅ
- ጥያቄው ከህፃናት ተማሪዎች ዕድሜና አቅም ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ
- ሁሉንም ተማሪዎች ማሳተፍ፣
- ጥያቄዎችን የተማሪን ስም ሳይጠሩ መጠየቅ፣
- ተማሪዎች ጥያቄውን ለመመለስ የሚያስፈልጋቸውን ጊዜ መስጠት፣
- ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በደንብ አዳምጦ መገምገም
- የተሳሳተ መልስ ከተማሪዎች ሲሰጡ በድጋሚ አለማስተጋባት
- ትክክለኛ መልስ የሚሰጡ ተማሪዎችን ማበረታታት፣

(5) **በመስክ ጉብኝት የማስተማር ዘዴ**(field visit)

ይህ የማስተማር ዘዴ ከተሰጠው ወይንም ከሚሰጠው የትምህርት ርዕስ ወይንም ይዘት ጋር ተያያዥነት ያለው ሥራ የሚከናወንበትን አሠራርና የሥራ ውጤት ህፃናት ተማሪዎች እንዲጎበኙ ማድረግ ነው፡፡

የመስክ ጉብኝት የማስተማር ዘዴ በውስጡ ሦስት ድርጊቶችን ይይዛል፡፡

1ኛ/ ከመስክ ጉብኝት በፊት የሚደረግ ውይይት

አመቻቾች የመስክ ጉብኝት ቦታን በመምረጥ ከተማሪዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይወያያሉ፡፡

2ኛ/ የመስክ ጉብኝት ማድረግ

ህፃናት ተማሪዎች እንዲጎበኙ/ እንዲመለከቱ የተነገራቸውን ቦታ አሠራርና ውጤት በሚገባ እንዲያዩ ማድረግ፣ በዚህም ወቅት አመቻች ህፃናት ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳይደርስ በንቃት መከታተል አለባቸው፡፡

3ኛ/ ከመስክ ጉብኝት በኋላ ውይይት ማድረግ፡፡ ከጉብኝቱ በኋላ አመቻች ህፃናት ተማሪዎች የቀሰሙትን ዕውቀት፣ ያገኙትን ልምድ እንዲወያዩበት ያደርጋሉ፡፡

**ጠንካራ ጎኖች፡-**

- ህፃናት ተማሪዎች የአስተሳሰብ አድማሳቸውን እንዲያሰፉ ይረዳል፡፡
- በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከላትና በህብረተሰቡ መካከል መቀራረብን ያመጣል፡፡

**ደካማ ጎኖች፡-**

- ሰፋ ያለ ጊዜና ወጪ ሊያስፈልገው ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት

## 3. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ክፍሎችን ማመቻቸት

### በዚህ ክፍል ውስጥ የተካተቱ ንዑሳን ርዕሶች

- *አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ተገቢነትና አመራረጥ፡*
- ✓ *በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የሚሠጡትን የትምህርት ዓይነቶች ማመቻቸት*
- ✓ *በክፍል ውስጥ ህፃናት ተማሪዎችን በማነቃቃትና በማትጋት የማመቻቸት ስልቶች ማስተማር*

**የክፍለ ትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማዎች፡-**

*አመቻቾች ይህን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- *ከህፃናት ተማሪዎች አካባቢና ፍላጐት ጋር ሊሄዱ የሚችሉ የመማር ማስተማሪያ መሣሪያዎች ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡*
- *አመቻቾች ተሳታፊ ህፃናት ተማሪዎችን በደስታ ትምህርታቸውን እንዲከተሉ ያደርጋሉ፡፡*
- *በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች ያመቻቻሉ፡፡*
- *አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማስተማሪያ ክፍሎችን ሳቢና ማራኪ በሆነ መልክ ያደራጃሉ፡፡*

*ከአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተሳታፊ ህፃናት ተማሪዎች ፍላጎትና አቅም ጋር የተገናዘቡና ተገቢነት ያላቸው የመማር ማስተማሪያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ መርጦ መጠቀም እጅግ አስፈላጊ ሲሆን በዚሁ ረገድ ትልቁን ሚና መጫወት ያለባቸው አመቻቾች ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ንዑስ ክፍል ሥር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*

## 3.1. በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች ማመቻቸት

### 3.1.1 <u>የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር</u>

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማዎች፣**

- የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክህሎትን ማዳበር
- የቃላትና የሰዋሰው ችሎታን ማጠናከር፣
- ለሁለተኛ ቋንቋ መሠረት መጣል ነው፡፡

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ክህሎቶች**

<u>*የአመቻች ማስታወሻ*</u>

*አንድ አመቻች የአፍ መፍቻ ቋንቋን ሲያስተምር የሚከተሉት ዋና ዋና ነገሮች ተያያዥነት ያላቸው መሆኑን መገንዘብ አለበት፡፡*

- *ማድመጥና ንግግር፣*
- *ቅድመ -ንባብና ጽሑፍ፣*
- *ንባብ፣ጽሁፍ፣*
- *በህይወት ሂደት የተኩረት ክህሎት*

**(1) ማድመጥና ንግግርን ማስተማር**

በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአፍ መፍቻ ቋንቋን የሚያስተምር/ የምታስተምር ማድመጥና ንግግርን እንደሚከተለው ለማስተማር ይቻላል፡፡

- ቀላል ተረቶችን ለተማሪዎች በማንበብ አድምጠው ስለ ገፀ ባህርያቱ ምንነትና ማንነት እንዲናገሩ ማድረግ፣
- ተረቶችን አዳምጠው መሠረታዊ ሀሳቦችን እንዲናገሩ ማድረግ፣
- በአካባቢያቸው የሚገኙ ስዕሎችን ምንነት እንዲገልጹ ማድረግ፣
- ቀለል ያሉ መመሪያዎችን አድምጠው በመመሪያው መሠረት ድርጊቶችን እዲያከናውኑ ማድረግ፣
- ባህላዊ ተረቶችን በማዳመጥ የተረቱን ገፀባህርያት እንዲገልጹ ማድረግ፣
- በአካባቢያዊ ባህልና ወግ ላይ ገንቢ አስተያየት እንዲያፈልቁ መጠየቅ፣
- በጤና ፣ በሥርዓተ ጾታና በአካባቢ እንክብካቤ ላይ በሥርዓት ተራ ጠብቀው እየተናገሩ እንዲወያዩ ማድረግ፣

ለምሳሌ ፡-

- ስለተክል የሚገልጽ አጭር ጽሁፍ ሲነበብ አድምጦ ቀለል ያለ የቃል ጥያቄዎችን እዲመልሱ ማድረግ፣
- በአካባቢያቸው የሚገኙ የተክል ዓይነቶችን  መናገር
- ለጤና አደገኛ የሆኑ ነገሮችን እንዲናገሩ መጠየቅ፣
- ከሬድዮ ያዳመጡትን ተረት መልሶ መናገር፣
- በግል ንጽህና ላይ የሚሰጠውን መመሪያ ተገንዝበው ሀሳብ መግለጽ፣
- የቤት እስሳትን በዘመናዊ መልክ ማደራጀት ያለውን ጥቅም መናገር፣
- አጫጭር ተረቶችን ከ4-6 ደቂቃ በሚደርስ ጊዜ ውስጥ መናገር፣
- በዓመት ውስጥ የሚገኙ ወራትን ስም መጥራት፣
- በዓመት ውስጥ የሚገኙ ወቅቶች መኖራቸውን አድምጦ መናገር፣
- የጓሮ አትክልት ጥቅምን መናገር፣
- የቤት ንጽህናን መጠበቅ ለምን እንደሚጠቅም መናገር፣
- የዱር እስሳት ስምና ጥቅማቸውን መናገር፣
- የምግብ ዓይነቶችን መዘርዘር
- በመልካም ፀባይና መጥፎ ፀባይ ዙሪያ በቡድን መወያየት፣
- የሚያውቁትን ባህላዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች ስም መዘርዘር፣
- በአካባቢ የሚከበሩ በዓላትን ስም መናገር፣
- የመልካም ጉርብትና መገለጫዎችን ካዳመጡ በኋላ እንዲናገሩ ማድረግ፣
- በእግራቸው ሲሄዱ የትኛውን የመንገድ ጎን ይዘው መሄድ እንዳለባቸው እንዲናገሩ ማድረግ
- ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን እንዲናገሩ ማድረግ፣ ወዘተ..፡፡

*ለአመቻች ማስታወሻ፡-*

*የማድመጥና መናገር ክህሎትን ማስተማር የተማሪዎችን ደረጃና ዕድሜ ባገናዘበ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡*

(2) **ቅድመ ንባብና ጽሁፍ**

*የአመቻች ማስታወሻ፡-*

*የደረጃ አንድ ተማሪዎችን ቅድመ ንባብና ጽሁፍ ለማስተማር አንድ አመቻች የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል፡፡*

- *ፅሁፍ ትርጉም ያለው ነገር መሆኑን ማስረዳት*
- *ጽሁፍ ከግራ ወደ ቀኝ መፃፍ እንዳለበት ማስገንዘብ፣*
- *ለሆሄ ቀረፃ የሚሆኑ መሠረታዊ ምልክቶችን እንዲለዩ ማድረግ፣*
- *ሆሄያት ድምፅን እንደሚወክሉ በምሳሌ ማሳየትና ተማሪዎች እንዲለማመዱ ማድረግ፣*

(3) **ጽሑፍና ንባብ፡-**

ንባብን በማስተማር ወቅት አመቻች ማድረግ የሚገባው፡-

- በአካባቢ የተለመዱ ቁሳቁሶችን ስም ከስዕል ጋር እያገናዘቡ እንዲያነቡ ማድረግ፣
- ድምፅ ሳያሰሙ ማንበብን ማለማመድ፣
- መመሪያን በዝመታ አንብበው ሥራ ላይ እንድያውሉ ማድረግ፣
- የተለያዩ አንቀጾችን በማንበብ የአንቀጹን ዋና ሀሳብ ከዝርዝሮችና ከምሳሌዎች መለየት፡፡
- የተለያዩ ዐረፍተ ነገሮች፣ አጫጭር ተረቶችን እንዲያነቡ ማድረግ፣
- ከጋዜጦችና መጽሄቶች መረጃ አንብበው እንዲረዱ መረዳት
- ምህፃረ ቃላትን እንዲያነቡ ማድረግ፣

ጽሑፍን በማስተማር ወቅት ከአመቻች የሚጠበቁ ዋና ዋና ነገሮች፡-

- ፊደላትን በትክክል ቅርፃቸውን ጠብቀው እንዲጽፉ ማድረግ፣
- ሙሉ ቃላትንና ዐረፍተ ነገሮችን እንዲገለብጡ ማድረግ፣
- ሥርዓተ-ነጥብን በአግባቡ ተጠቅመው እንዲፅፉ ማድረግ፣
- ገላጭ ወይንም ተራኪ አጭር ፅሁፍ ከራሳቸው አፍልቀው እንዲፅፍ ማድረግ፣
- በሁለቱም ወይም በሶስት አንቀጽ ስራሳቸው እንዲጽፉ ማድረግ
- ስለራሳቸውና አካባቢያቸው አጭር ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ
- የሌሎችን ሀሳብ በመደገፍ ይሁን በመንቀፍ ሀሳባቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ ማድረግ፣
- የሰላምታ ደብዳቤ እንዲጽፉ ማድረግ፣
- ማመልከቻ እንዲጽፉ ማድረግ፣

(4) **በህይወት ሂደት የሚገኝ ክህሎት ፡-**

በዚህ ትምህርት ወቅት አመቻች የሚከተሉት ማከናወን ይኖርበታል፡፡

- ተማሪዎቹ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን እንዲለዩ ማድረግ፤
- በት/ቤት የአደጋ ጊዜ ተጠሪ ማን እንደሆነ ለይተው እንዲያውቁ ማድረግ፤
- የግልና የአካባቢያቸውን ንጽህና እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ ማስረዳትና እንዲገልጹ ማድረግ፤
- ከመጥፎ ባህሪ ራስንና ሌላውን መጠበቅ እንዲችሉ ማድረግ፤
- በራስ በመተማመን ሀሳባቸውን በመግለጽ የአቻ ግፊትን ወይንም ተፅዕኖን መቋቋም እንዲችሉ ማድረግ፤

## 3.1.2 <u>የእንግሊዝኛ ቋንቋን የማስተማር ሂደትን ማመቻቸት</u>

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ

- የማዳመጥና የመናገር ክህሎቶችን ያስተምራሉ፡፡
- የማንበብና የመፃፍ ክህሎቶችን ተማሪዎች እንዲችሉ ይደረጋል፡፡

<u>ለአመቻች ማስታወሻ፡-</u>

በእንግሊዝኛ ትምህርት ጊዜ የማዳመጥን ክህሎት ለማስተማር አመቻች የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- ተማሪዎች ክፍል ውስጥ እርስ በእርሳቸው ሰላምታ እንዲሰጣጡ ማድረግ(greeting)
- የክፍል ውስጥ መመሪያዎችን በትክክል እንዲያከናውኑ ማድረግ፣
- ካዳመጡ በኋላ የሰውነት ክፍላቸውን በመንካት እንዲያሳዩ ማድረግ፣
- የተለያዩ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች (objects) እንዲገልጹ ማድረግ፣
- የእግሊዝኛ ፊደላትን (alphabets)በቃል እንዲናገሩ ማድረግ፣
- ቁጥሮችን እንዲናገሩ ማድረግ፣
- ግጥሞችና መዝሙሮችን ካዳመጡ በኋላ ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ፣
- በንግግራቸው ጊዜ በነጠላና የብዙ ቁጥር እንዲለዩ ማስቻል፣
- ስለሰዎችና ስለዕለታዊ ድርጊቶች መግለፅ እንዲችሉ ማድረግ፣
- ቃላትንና ስዕሎችን አዛምደው እንዲናገሩ ማድረግ፣
- አጫጭር አንቀጾችንና ተረቶችን አድምጠው ስለእነርሱ የተጠየቁትን ጥያቄዎች መመለስ እንዲችሉ ማድረግ፣

ምን (whay?) ፣ ምን( What?)፣ መቼ (when?)፣ እንዴት ፣ (how?) የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ እንዲችሉ ማድረግለየደረጃው የተመደቡትን ትምህርቶች አመቻቹ ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃና ችሎታ ጋር አመጣጥኖ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ እንደየክፍሉ ደረጃ የሚከተሉትን ድርጊቶች በመማር ማስተማር ወቅት ይተገብራሉ፡፡

### (1) ሰላምታ መጠያየቅ (Greeting) (ደረጃ አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች

- ሰላምታ በሚገባ እንዲጠያየቁ ያደርጋሉ፡
- የራሳቸው ስምና የክፍል ደረጃ እንዲናገሩ ያስችላሉ፡
- በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ስም መናገር እንዲችሉ ያደርጋሉ፡

- አንዳንድ የክፍል ውስጥ ትዕዛዞችን እንዲተገብሩ ይረዳሉ፡
- ፊደላትን በትክክል እንዲያነቡ ይከታተላሉ፡
- መዝሙር  አዳምጠው እንዲዘምሩ ያበረታታሉ፡፡

<u>የአመቻች ማስታወሻ</u>

አመቻች ተማሪዎች ሰላምታን በትክክል መለዋወጥ እንዲችሉ አስፈላጊ የሆኑ የሰላምታ ልውውጥ ሥርዓቶችን ማስረዳትና ማሳየት ይኖርበታል፡፡

- ( am,is,are,have,has,can) እንዲለዩና በአግበቡ እንዲጠቀሙ ማስቻል፡፡
- ባለቤትነትን የሚያመለክቱ ቃላትን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ማድረግ
- የብዝሀ ቁጥር ስሞች እንዴት እንደሚነበቡና እንደሚፃፉ መለየት እንዲችሉ ማድረግ
- መስተፃምር በአግባቡ እንዲለዩና እንዲጠቀሙ ማገዝ
- ለየደረጃው የተቀመጡትን መጽሐፍት እንዲያነቡ ማድረግ፣

**የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-**   ሰርቶ ማሳያ ዘዴና በቡድን ውይይት ዘዴ

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-** ሁለት ሁለት ሆነው የሰላምታ ልውጥጥ፣ የአቻ የሰላምታ ልውውጥ ያሳያሉ

(1) አመቻች ተማሪዎች ሁለት ሁነው እርስ በርሳቸው ሰላምታ እንዲጠያየቁ ያደርጋል

ለምሳሌ፡-   ደህና አደርክ? (Good Morning)

ስሜ__________እባላለሁ፡፡ (My name is________.)

የአባቴ ስም____ይባላል፡፡ (My father's name is_.)

እኔ የደረጃ አንድ ተማሪ ነኝ (I am Level one Student)

(2) ፊደላትን (Letter alphabets)   እንዲያነቡ ያደርጋል፡፡ በመጀመሪያ አመቻቹ/ቿ/ ያነባል/ታነባለች፡፡ ተማሪዎችም ደግመው ያነቡታል፡፡  a,e,c,o,t

(3) የፊደል አፃፃፍ ቅርጾችን (Patterns)  ያሣያቸዋል፡፡ ህፃናት ተማሪዎችም ፊደል ለመፃፍ የሚያገለግሉትን የአፃፃፍ  /መስመሮች/ይፅፋሉ፡፡

**ግምገማ**፡- ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁና ሰላምታ እንዲለዋወጡ ማድረግ፤

## (2) **የሰውነት ክፍሎች (ደረጃ አንድ)**

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፣

- የሰውነት ክፍላቸውን መናገር እንዲችሉ ያግዛሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-** በቡድን መወያየት

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**አመቻቹ/ቿ ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል የሰውነት ክፍሎቻቸውን እንዲገልጹ ይደረጋል፡፡

ይህ አፍንጫዬ ነው፡፡ (This is my nose)

ይህ ጣቴ ነው፡፡ (This is my finger)

አመቻች ፡- ይህ ጣት ነውን? (Is this a finger?)

ተማሪ ፡- አዎን ጣት ነው፡፡ (Yes, it is.) ጣት አይደለም (No, it isn't)

በተጨማሪም አመቻች፡- የስዕል ስምና የስዕሉን የመጀመሪያ ፊደል ህፃናት ተማሪዎች እንዲያዛምዱ ያደርጋል፡፡

**ግምገማ፡-** ህፃናት ተማሪዎች ጥንድ ሆነው አንደኛው የሰውነት ክፍሉን ሲያመላክት ሌላው ደግሞ ያን የሰውነት ክፍል እንዲናገር ማድረግ፤

**<u>የአመቻች ማስታወሻ፡-</u>**

አመቻች የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃና ዕድሜ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ

- ሰላምታ እንዲለዋወጡ ማድረግ፣
- የሰውነት ክፍላቸውን ስሞች ካዳመጡ በኋላ እንዲያሳዩ ማድረግ፣
- ቃላትንና ስዕልን ማዛመድ እንዲችሉ ማድረግ፣
- አጫጭር ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ እንዲችሉ መርዳት፣
- ቁጥሮችን በየደረጃው እንዲያነቡ ማድረግ፣
- የነገሮችን ቀለም መናገር እንዲችሉ ማድረግ፣
- ግጥምንና መዝሙርን በቃል መናገር እንዲችሉ ማድረግ
- አቅጣጫን ማመልከት እንዲችሉ መርዳት፣
- የፊደላትን ስም እንዲለዩና እንዲያነቡ ማስቻል፣
- ቀላል ቃላትንና ዐረፍተ ነገሮችን እንዲያነቡ ማስቻል

- አጫጭር አንቀጾችን እንዲያነቡ ማድረግ
- ቁጥሮችን እንዲያነቡ ማድረግ
- ፊደላትን በትክክል እንዲጽፉ ማድረግ
- በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የጎደሉ ቃላትን መሙላት ማስቻል
- ሁሉንም 26 ፊደላት በትክክል እንዲጽፉ ማስቻል
- ስለራሳቸው አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም እንዲፅፉ ማድረግ
- ሥርዓተ ነጥብን በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ

(3) **ቀለማት** (colours) ( **ደረጃ ሁለት**)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፣

- ቀለማትን እንዲለዩ ያግዛሉ፡፡
- የፊደላትን ቅርጽ ከጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲጽፉፋ ያበረታታሉ።

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በጥያቄና መልስ የማስተማር ስልት፣

**የትምህርቱ አቀራረብ ፡-** አመቻች ተማሪዎች የተለያዩ የአልባሳት ቀለማትን እንዲለዩና እንዲናገሩ ይደረጋል፡፡

- ቀለማትን ለይተው የቁሳቁሶችን ስም ይናገራሉ፡፡
  ቀይ እስኪርቢቶ (A red pen) ይህ ቀይ እስኪሪቢቶ ነው (This is a red pen.)
- ከ5-8 የሚሆኑ የተለያዩ ቀለማትን እያሳያቸው/ እያሳየቻቸው/ ያስተምራል/ታስተምራለች፡፡ (red,blue,green,yellow, black..)
- የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ቁሳቁሶች (ለምሳሌ አልባሳት) ለተማሪዎቹ በማሳየት የቀለሙን ስም እንዲናገሩ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡
- ስለቀለማት መዝሙር ( Song) እንዲዘምሩ ማድረግ ትምህርቱ የበለጠ እንዲገባቸው ማድረግ ይቻላል፡፡
- በጥቁር ሰሌዳ ላይ ለፅሁፍ ትምህርት የሚረዱ መስመሮችና ቅርጾችን ተማሪዎች የተጠየቁትን ፊደል ፈልገው እንዲያገኙ መጠየቅ፤
- የተለያዩ ፊደላት የተፃፉበትን ካርዶች (ወረቀት) በማደባለቅ ከዚያ ውስጥ ተማሪዎች የተጠየቁትን ፊደል ፈልገው እንዲያገኙ መጠየቅ፤

**ግምገማ** ፡- አንዱ ተማሪ ተነስቶ አንድ ነገር ለክፍል ጓደኞቹ እንዲያሳይ በማድረግ እነርሱ ደግሞ የነገሩን ቀለም እንዲናገሩ ማድረግ

## (4) ቁጥሮችን መቁጠር (ደረጃ አንድ )

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ከ 1 እስከ 10 ያሉትን ቁጥሮች እንዲለዩና መናገር እንዲችሉ ያፍዛሉ፡፡
- በአንድ ስብሰባ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ብዛት በቁጥርና በዓይነት እንዲናገሩ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡
- በስም (noun) ላይ “s” በመጨመር የብዙ ( plural ) ቁጥር አመልካች ስሞችን መመስረት እንዲችሉ ያበረታታሉ፡

**የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-** ሰርቶ ማሳያ ዘዴና የጥያቄና መልስ ስልት

**የትምህርቱ አቀራረብ፦** ከአንድ እስከ አስር ያሉትን ቁጥሮች አመቻቹ/ቿ ከተናገረ/ች በኋላ ተማሪዎች ያዳመጡትን ቁጥሮች እንዲናገሩ ማድረግ፤ በብላክቦርድ ላይ በመጻፍ እየጻፍ እንዲለማመዱ መድረግ።

**ግምገማ** ፡- ተማሪዎች ከአንድ እስከ አስር ያሉትን ቁጥሮች እንዲናገሩና እንዲጽፉ መጠየቅ።

## (5) የእኔ ቤተሰብ (My Family) (ደረጃ አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ፊደላትን እንዲለዩ ይደርጋሉ፡፡
- የቤተሰብ አባላትን የሚያሳዩ ቃላትን እንዲይቁ ያበረታታሉ፡፡
- የቤተሰብ አባላትን የሚያሳዩ የመጀመሪያ ፊደላትን በትክክል መፃፍ እንዲችሉ ያደርጋሉ፡፡
- ከቤተሰብ አባላት ጋር የተያያዙ ቃላትንና ዐረፍተ ነገሮችን ማንበብ እንዲችሉ ያግዛሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-** በቡድን ውይይት

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-** አመቻች ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ስለቤተሰቦቻቸው እንዲነጋገሩ ያደርጋል፡፡

ለምሳሌ፡- ሁለት ወንድሞች አሉኝ (I have two brothers).

- ሁለት እህቶች አሉኝ (I have three sisters.)

ወንድሜ አስር ዓመቱ ነው (My brother is 10 years old)

- ተማሪዎች በአመቻቹ የመነገሩት ቃላት ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ፤
- የመጀመሪያ ፊደላት የጎደሏቸውን ቃላት በጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፍና እንዲገለብጡ ማድረግ በመቀጠልም የጎደለውን እንዲሙሉ ማበረታታት።

**ግምገማ፡-** ተማሪዎች የቤተሰባቸውን ስም በመዘርዘር እንዲገልፁ መጠየቅ፤

ለምሳሌ፡- This is my father, etc እንዲሉ ማድረግ፤

## (6) ስለሰዎች ገለፃ ማድረግ (Describing People) (ደረጃ ሁለት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- የሰዎችን ቁመና እንዲገልጹ ያበረታታሉ፡
- ስዕሎችንና ስለስዕሎቹ የተፃፉትን ዐረፍተ ነገሮችን እንዲያዛምዱ ያግዛሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-** የጥያቄና መልስ ስልትና የቡድን ውይይት

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**አመቻች ለተማሪዎች የሰዎችን ስዕል በማሳየት ቁመናቸውን እንዲገልጹ ያደርጋል፡፡ ቀጭን (Thin)፣ ረጅም (tall)፣ ትልቅ (big)፣ ትንሽ (small) ወዘተ… እነዚህን ቃላት ተጠቅመው በዐረፍተ ነገር እንዲሰሩ ማድረግ

ለምሳሌ፡- እርሷ ቀጭን ናት (She is thin.)

- በጥቁር ሰሌዳ ላይ የተፃፉላቸውን ፊደላትና ቃላት ደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ማድረግ፤

- የመጀመሪያ ፊደላት የጎደሏቸውን ቃላት በጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፍና እንዲገለብጡ በማድረግ የጎደሉትን ፊደላት እንዲሞሉ ማገዝ።

***ግምገማ፡-*** ህፃናት አጫጭር ገለፃዎችን ከስዕሎች ጋር እንዲያዛምዱ መጠየቅ፤

## (7) ትምህርት ቤቴ (My School) (ደረጃ ሁለት)

***የትምህርቱ ዓላማዎች፡-***

*አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡*

- ስለ ት/ቤታቸው መግለጽ እንዲችሉ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡
- እርስ በርሳቸው ሰላምታ መለዋወጥ እንዲችሉ በምሳሌ ያሳያሉ፡፡
- ስለአንድ ቦታ የተሰጠውን ገለፃ ከስዕል ጋር እንዲያዛምዱ ጥያቄ ይጠይቃሉ፡፡

***የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-*** የጥያቄና መልስ ስልትና የቡድን ውይይት

***የትምህርቱ አቀራረብ፡-***

- አመቻች ተማሪዎችን ስለትምህርት ቤታቸው የጥያቄና መልስ ዘዴን በመጠቀም እንዲገልጹ ያደረጋል፡፡
- አመቻች ለተማሪዎቻቸው የት/ቤቱን ፎቶ ወይንም ስዕል በማሳየት አጭር ዐረፍተ ነገር እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡-ት/ቤቱ የተወሰኑ ትልልቅ ክፍሎች አሉት (The school has some large rooms?)

- ት/ቤቱ ብዙ ወንበሮች አሉት (It has many chairs.)
- ሁሉም ክፍሎች ጠረጴዛ አላቸው (All the rooms have tables)

በጥያቄና መልስ መልክ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።

ለምሳሌ፡- የስፖርት ሜዳ የት ጋ ነው?(Where is the Sports Field?)

- ከህንፃው በስተጀርባ ነው፡፡ (It is at the back of the building)

እንደዚሁም ተማሪዎች ሰላምታ (greetings) እንዲለዋወጡ አድርጉ፡፡

**ግምገማ፡-** ተማሪዎች ስለት/ቤታቸው እንዲነጋገሩና እንዲጽፉ ማድረግ፤

(8) **ልጆች ምን እየሰሩ ነው? (What are the children doing?) (ደረጃ ሦስት)**

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ሰዎች ምን እየሠሩ እንደሆነ እንዲገልጹ ያበረታታሉ፣
- በአክብሮት መጠየቅና ማመስገንን ያለማምዷቸዋል፣
- በማሳጠር የተፃፉትን ግሦች (Verbs) እንዲለዩ ያግዟቸዋል፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴዎች** ፡- የጥያቄና መልስ ዘዴና የቡድን ውይይት

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻች ሁለት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቆመው የሚሰሩትን ነገር ሌሎች እንዲያብራሩ ይጠይቃል፡፡
- አመቻች የተለያዩ ስዕሎችን ያሳያል/ታሳያለች፡፡ ከዚያ በኋላ በሥዕሉ ላይ የተመለከተው ሰው ምን እያደረገ መሆኑን ተማሪዎች ይናገራሉ፡፡

ምሳሌ፡- ምን እያደረጉ ነው? (What are they doing?)

መፃህፍት እያነበቡ ነው (They are reading books.)

ምን እያደረገች ነው? (What is she doing? )

ደብዳቤ እየፃፈች ነው (She is writing a letter.)

ምን እያደረገ ነው? (What is he doing?)

ክፍሉን እያፀዳ ነው፡፡ (He is cleaning the room.)

በተጨማሪም የማኅበረሰቡን የአክብሮ የጥያቄ አጠያየቅ አባባሎችን ይለማመዳሉ፡

ምሳሌ፡- ይህን መፃህፍ መውሰድ እችላለሁን? (Can I take this book, please?)

እዚህ መቀመጥ እችላለሁን? (Can I sit here?)

በማሳጠር የተፃፉትን ግሦች (Verbs) መናገርና መፃፉ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡-I'm = I am

I can't = I cannot

**ግምገማ**፡- አመቻች 10 ተማሪዎችን መርጠው ድርጊትን የሚያመለክቱ ስዕሎችን ይሰጧቸዋል እያንዳንዱን ሥዕል ያገኘ ተማሪ በስዕሉ ላይ የተመለከተውን ድርጊት ይሠራል፡፡ ሌሎች ተማሪዎች ግን፡ ምን እያደረገ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

## (9) በእርሻ ሥራ ላይ (on the Farm)(ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- በእርሻ ሥራ ላይ የሚያገለግሉ እንስሳትንና የሰብል ዓይነቶችን መናገር እንዲችሉ ያበረታቷቸው፣
- የነጠላ (Singular) የብዙ ቁጥርን (Plural) እንዲለዩ ያግዞቸው፣
- ስለ እንስሳት አጭርና ቀላል ገለፃ እነዲያቀርቡ በምሳሌ አሳዩዋቸው ወይንም ያስረዷቸው፣
- ስለሚችሉትና ስለማይችሉት ነገር እንድናገሩ ያግዟችሁ፣

**የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-** ጥያቄና መልስ ዘዴና የቡድን ውይይት

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻች ለተማሪዎች የጥያቄና መልስ ዘዴን በመጠቀም በእርሻ ላይ ጠቀሜታ ያላቸውን እንስሳት እንዲለዩና እንዲገልጹ ያደርጋል፡፡
- አመቻች የእንስሳ ስዕል በመያዝ የእንስሳውን ስም ለተማሪዎቹ ይናገራል፡፡ ተማሪዎችም ደግመው እንዲናገሩ ያደርጋል/ታደርጋለች ከዚያ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ዓይነት ይጠየቃሉ፡፡

ምሳሌ፡- ይህ ምንድነው? (What is this?) ላም ናት(This is a cow.)

ያ ምንድ ነው? (What is that? )

ያቺ ፍየል ናት.( That is a goat)

ስለ"can" እና "can't"በመጠቀም ይገልፃሉ፡፡

ምሳሌ፡- ወፍ መብረር ትችላለች (A bird can fly.)

ፍየል መብረር አትችልም፡፡ (A goat can't fly)

እንደዚሁም ከተለያዩ እንስሳት ምን እንደሚገኝ መናገር ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡- ከላም ምን እናገኛለን? (What do we get from a cow?)

ከላም ወተት እናገኛለን፡፡(We get milk from a cow )

ከዶሮ ምን እናገኛለን? (What do we get from a hen?)

**ግምገማ**፡- ተማሪዎች ስለአንድ እንስሳ በስዕል የተደገፈ አጭር ታሪክ በመፃፍ እንዲያቀርቡ መጠየቅ፡፡

## (10) ስንት ሰዓት ነው? (What time is it?) (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ
ተማሪዎች፡

- ድግግሞሽ ( Frequency) አመልካች ቃላትን መጠቀም እንዲችሉ እገዛ መስጠት፡፡
- ጠዋት ፣ ቀትር፣ ምሽት የሚባሉ የጊዜ አመልካች ቃላትን መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዲችሉ መደገፍ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-** የጥያቄና መልስ ዘዴና የቡድን ውይይት

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻች በጥቁር ሰሌዳ ላይ የተለያዩ ጊዜያትን የሚያመለክቱ ሰዓት በመሳል ተማሪዎች ሰዓቱን እንዲናገሩ ያደርጋል፡፡
- ተማሪዎች የግድግዳ ላይ ሰዓት (digital clock) በማየት ስንት ሰዓት እንደሆነ ይናገሩ፡፡
- ተማሪዎቹ አመቻቹ የሚያነበውን/ የምታነበውን ምንባብ በማዳመጥ በምንባቡ ውስጥ የተነገረውን ሰዓት ይናገሩ፡፡

- ተማሪዎቹ በቡድን ተከፍለው ስለትምህርት በቤታቸው ክፍለ ጊዜያት መረጃ ይለዋወጡ፡፡
- አንዱ ተማሪ በቀን ውስጥ የሚያከናውናቸውን ድርጊቶች ካዳመጡ በኋላ ድርጊቶቹን ከሰዓት ጋር ያዛምዱ፡፡
- አመቻቹ የሰዓት አገላለፅ ቋንቋ እንዲለምዱ እገዛ ይስጡ፡፡

ምሳሌ፡-ስንት ሰዓት ነው? (What time is it?)

ስምንት ሰዓት ነው (It is 2 o'clock.)

1 ሰዓት ከሩብ ነው፡፡ (It is quarter past 7 o'clock. )

10 ተኩል ነው (It is 4:30 (It is four thirty=?)

ለዘጠኝ 20 ጉዳይ ነው (It is 20 to 3 o'clock)

ለ2 ሩብ ጉዳይ ነው፡፡ (It is quarter to 8 o'clock)

11 ተኩል ነው (It is half past 5 o'clock )

**ግምገማ፡-** ተማሪዎች በስዕል የተመከተቱን ሰዓት (ጊዜ) በደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ማድረግ፤

## (11) ይህ ከምንድነው የተሠራው? (What's this made of?) (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ባለቤትነት የሚያመለክቱ ቃላትን መጠቀም ይችላሉ፣
- አንድ ነገር ከምን እንደተሠራ መግለፅ ይችላሉ፣
- የነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን ይለያሉ፣
- ተውላጠ ስሞችን በትክክል ይጠቀማሉ፣
- ዐረፍተ ነገሮችና ቃላትን ያነባሉ፣ ይፅፋሉ፣

**የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-** ጥያቄና መልስ ዘዴና የቡድን ውይይት

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻች ተማሪዎች ወደ ክፍል ይዘው የመጡትን ቁሳቁስ ከምን እንደተሠራ እንዲገልጹ ያደርጋል፡፡

- አመቻቹ/ቿ ስለአንድ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ወደ ክፍል ይዞ/ዛ ይመጣል/ትመጣለች፡፡ በመቀጠልም ቁሳቁሶች ምን እንደሚባሉ፣ ለምን እንደሚያገለግሉ ፣ ከምን እንደተሠሩ ይጠያየቃሉ፣ ይናገራሉ፤

**ግምገማ**፡- ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸው ያሏቸውን ቁሳቁሶች እንዲሁም ቁሳቁሶቹ ከምን እንዲሠሩ እንዲገልጹ ማድረግ፡፡

### 3.1.3 <u>የአካባቢ ሳይንስ የማስተማር ሂደትን ማመቻቸት</u>

**የትምህርቱ ዓላማዎች**

አመቻቾች ይህንን ክፍለ ትምህርት ጠንቅቀው ከተረዱ በኋላ ለተማሪዎቹ፡-

- ስለ ሰውና ኑሮው  የማስተማሪያ ስልት ያቀያሳሉ
- ስለጤናና ስለቤተሰብ  ማስረዳትና ማሳወቅ ይችላሉ
- ስለተፈጥሮአዊና ማህበራዊ አካባበቢዎች ተስማሚ በሆነ የማስተማሪያ ዘዴ በመጠቀም ያስተምራሉ፡፡

## (1) ሰውና ኑሮው (ደረጃ አንድ)

በዚህ ምዕራፍ ሥር ተማሪዎች ስለ ሰውነት ክፍሎችና ጥቅማቸው ምንነት በተለያዩ መንገዶች ጠንቅቀው እንዲያውቁ፣ እንዲረዱ፣ እንዲከባከቡ እና ከራሳቸው አልፎ ለሌሎች ሰዎች እና ለአካባቢያቸው ህብረተሰብ ደህንነት ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች እንዲያዳብሬ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ዋና ዓላማ በመነሳት ለተዘረዘሩት የትምህርት ይዘቶች ዝርዝር ዓላማዎችን በዕለት ተዕለት ትምህርት ዕቅድ አካቶ ማዘጋጀት የትምህርት አመቻች ኃላፊነት ነው፡፡

**ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች**

**የማስተማር ዘዴ**፡- የቡድን ውይይት፣ ጥያቄና መልስ፣ትረካ የሚና ጨዋታ፣ገለፃ፣ የመስክ ምልከታ፣ ክርክር፣ የቃል ዘገባ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች**፡- ፖስተሮች፣ ሥዕሎች፣እውነተኛ ናሙናዎች፣ሞዴሎች ልብሶች፣ ወረቀቶችን፣ የቤት ቁሳቁሶች፣ በአካባቢ የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች) እንስሳት ፣ ዕፅዋት)፣ ግዑዝ ነገሮች፣

ለአመቻች ማስታወሻ፡-

- ትምህርቱን ከመጀመራቸው በፊት ይዘቱን በደንብ በማንበብ ተማሪዎች የትምህርቱን ይዘት ሲማሩ ሊመጡ የሚችሉ የባህሪይ፣ ዕውቀት፣ ክህሎትና ዝንባሌ፣ ወ.ዘ.ተ) ለውጥ ግምት ውስጥ በማስገባት ንዑስ ዓላማዎችን መዘርዘር፣
- ተፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን አስቀድሞ መለየትና ማዘጋጀት፣
- ተማሪዎቹ የትምህርቱን ዓላማዎች ማሳካታቸውን ለመገንዘብ የሚያስችል የግምገማ ስልት አስቀድሞ መተለም ለምሳሌ፡- የቃል ጥያቄ መጠየቅና ተማሪዎች እንዲገልጹ ማድረግ ወዘተ.

ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በማካተት የምትህርት እቅዶች ማዘጋጀት፡፡)

**የትምህርቱ አቀራረብ**

- ተማሪዎች በትናንሽ ቡድኖች ተከፋፍለው በመጠቀም የየራሳቸውን ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ለሌሎች ጓደኞቻቸው በስም እንዲናገሩ ማድረግ፣
- ፖስተሮችን በመጠቀም ተማሪዎች ተራ በተራ ወደፊት ወጥተው በፖስተሩ ላይ የሚገኙትን የሰውነት ክፍሎች ስም እንዲዘረዝሩ ማበረታታት፣
- የተለያዩ የአካል ክፍሎች ስም በመጥቀስ ለአንዳንዱ የአካል ክፍል ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ተማሪዎች የተቻላቸውን ሁሉ እንዲዘረዝሩ ማበረታታት፣ በመጨረሻውም ገለፃ በማድረግ የተማሪዎችን ሀሳብ ማዳበር(ዐይን፣ ጥፍር፣ ወዘተ ምን ምን ጥንቃቄዎች እንደሚያስፈልጋቸው መዘርዘር፡፡)
- እያንዳንዱ የአካል ክፍል በጥንቃቄ ባይያዝ ምን ችግር ሊያስከትል እንደሚችል በቡድን ውይይት እንዲገልፅ ማድረግ፣ በአካባቢያቸው ካሉት ሰዎች መካከል የአካል ክፍል ችግር ያጋጠመው ሰው እንዳለ እንዲያስቡና ይህንኑ ለጓደኞቻቸው በክፍል ውስጥ ገለፃ ( ትረካ) እዲያደርጉ ማነሳሳት፣
- ከላይ የገለጿቸው ችግሮች እንዳይከሰቱባቸው ለራሳቸው የአካል ክፍሎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እዲያብራሩ በድጋሚ መጠየቅ፣

**ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለክፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን

**መሠረታዊ ፍላጎታችን**

**የማስተማር ዘዴዎች፡-** የቡድን ውይይት፣ የመስክ ምልከታ፣ ገለፃ ፣ ሚና ጨዋታ፣ ጥያቄና መልስ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣** ፖስተሮች፣ ሥዕሎች፣ ሞዴሎች፣

**ለአመቻች ማስታወሻ**

ይህ ትምህርት የሰው ልጅ በህይወት እንዲኖር የሚያስችሉት መሠረታዊ ነገሮች ምን እንደሆኑ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ነው፡፡ የትምህርቱን ይዘት የተለያዩ ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም አስፈላጊውን ዕውቀት እንዲጨብጡ ካደረጉ በኋላ ይህንኑ ይበልጥ ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራት ምን መምሰል እንዳለባቸው መወሰን፣ ተግባራቱን በቅደም ተከተል ማዘጋጀት፣ ተማሪዎች እንዲሰሯቸው መወሰንና ተማሪዎቹ የትምህርቱን ዓላማዎች አሳክተው ንደሆነ ማወቅ የሚችሉበትን የግምገማ ዘዴ ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ**

- ተማሪዎቹን በትናንሽ ቡድኖች ከፋፍሎ ማስቀመጥ፣
- የትምህርቱን ርዕስ ካሳተዋወቁ በኋላ ለሰው ልጅ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ምን እንደሆኑ ለ15 ደቂቃ እንዲወያዩ ማድረግ፣
- የውይይታቸውን ውጤት ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲገልጹ ዕድል መስጠት፣
- የክፍል ውይይቱን በማጠቃለል ገለፃ ማስጠት፣
- ተጨማሪ የክፍል ውስጥ ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸውን መገምገም፣ የማሻሻያ ርምጃዎችን መውሰድ፣

ለሰው ልጅ ኑሮ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ መሠረታዊ ተፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን ከተረዱ በኋላ፣ ተማሪዎች በእያንዳንዱ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎት ላይ ቀጣይ ውይይት እንዲያካሂዱ መጋበዝ፡፡ ምግብን በተመለከተ በአካባቢያቸው የሚዘወተሩ የምግብ ዓይነቶችን ስም እንዲጠቅሱ ፣ እያንዳንዳቸው የትኛውን ዓይነት ምግብ እንደሚወዱ ሀሳብ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡

ተማሪዎች ምግብ ባይበሉ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል መጠየቅ እና ምግብ ምን ዓይት ጥቅም እንደሚሰጠን መጠየቅ፡፡ ተማሪዎች ማብራሪያ እንዲሰጡ ዕድል መስጠት፡፡

የተማሪዎቹን መልሶችና የክፍል ውይይት በማጠቃለል ምግብ ጉልበት እንደሚሰጠን፣ እንደሚያጠነክረንና እንደሚያሳድገን ማብራራት፡፡

በየቤታቸው የሚመገቡት ምግብ ምን፣ ከምን እንደሚሠራ እንዲናገሩ ማድረግ
ለምሳሌ፡- እንጀራ፣ ገንፎ፣ ወጥ፣ ቆሎ ፣ ቂጣ፣ ንፍሮ፣ ዳቦ ወዘተ. ከምን እንደሚሠራ የምግቡን ዓይነት ስም መጀመሪያ በቡድን ውይይት ጊዜ እንዲዘረዝሩ ማድረግና ለእያንዳንዱ ለተዘረዘሩት የምግብ ዓይነቶች ምን እንደሆነ እንዲገልጹ ማድረግና ውይይቱን ማጠቃለል፡፡

የልብስን አስፈላጊነትና ምን ዓይነት ጥቅም እንደሚሰጥ በትናንሽ ቡድኖች እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ ከዚያም በቡድን ተወካዮች አማካይት የደረሱብትን ሀሳብ ለሌሎች የክፍል ተማሪዎች ማብራሪያ እንዲሰጡ ዕድል መስጠት፡፡ በቀረብ የክፍል ውስጥ ማብራሪያቸው ላይ በመመርኮዝ አጠቃላይ ገለፃ መስጠት፤ ለምሳሌ፡- ልብስ ውበት እንደሚሰጠን ፣ ከብርድ እንደሚከላከል፣ ከፃሐይ እንደሚከላከልና ከዝናብ እንደሚከላከል መግለፅ፡፡

የልብስ ዓይነቶችን በቀንና በሌሊት የልብስ ዓይነቶች፣ የበጋ እና የክረምት ልብስ፣ የሥራና የመዝናኛ ጊዜ የሚለበስ ልብስ፣ ወዘተ. በመክፈል እያንዳንዱ የልብስ ዓይነት ለምን እንደሚያስፈልግ ተጨማሪ ውይይት እንዲያደርጉ መጋበዝ፡፡ ውይይታቸውን ማጠቃለል፤ ግንዛቤያቸውን የበለጠ ማዳበር የሚያስችሉ ተግባራትን አስቦ በማቀድ የቤት ሥራ፣ የክፍል ሥራ የመሳሰሉትን መስጠት፡፡

በአካባቢያቸው ልብስ የሚሠሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች እንዳሉ ምን ዓይነት ልብስ እንደሚሰሩ እንዲሁም እያንዳንዱን የልብስ ዓይነት ከምን እንደሚሰሩ ወላጆቻቸውን ጠይቀው እንደሚመጡ መንገር፡፡ ከወላጆቻቸው ጠይቀው ባገኙት መልስ መሠረት መጀመሪያ የልብሶቹን ዓይነት እንዲዘረዝሩ ማድረግ፤ የዘረዘሯቸው ልብሶች ከምን ከምን እንደሚሰሩ ቀጣይ ውይይት እንዲያደርጉ፣ እያንዳንዳቸው የትኛው ዓይነት ልብስ መልበስ እንደሚወዱና ለምን እንደወደዱ በግል እንዲገልፁ እድል መስጠት፡፡
ከውይይቱ ማጠቃለያ ላይ ልብስ በአካባቢ ከሚገኙ የተለያዩ ነገሮች ማለትም እንደ ጥጥ፣ ቃጫ፣ ቆዳ፣ ሱፍ፣ ናይለን ካሉት እንደሚሰራ መግለፅ፡፡ በተለያየ የአየር ፀባይ ውስጥ እንኳ የአየር ፀባዩ ምቹ የሆነ ልብስ መልበስ እንደሚያስፈልግ ማስገንዘብ፤

ለምሳሌ በፀሐይና በበጋ ጊዜ ስስ ልብሶች፣ በክረምትና በቅዝቃዜ፣ ጊዜ ወፍራም ልብሶች እንደሚያስፈልጉ ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡ ተማሪወች ቤታቸው አካባቢ እያሉ ድንገት ዝናብ ቢዘንብና ዓየሩ ቀዝቃዛ ቢሆን ምን እንደሚያደርጉ በትናንሽ ቡድን በውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ ትምህርቱን የበለጠ ያጠናክራል፡፡

የመጠለያ ቤትን አስፈላጊነት በማስመልከት በአካባቢያቸው የሚገኙ ቤቶችን የመስክ ምልከታ በማድግ እንዲጎበኟቸው በማድረግ ከምን፣ እንደሚሠሩ እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡ መጠለያ ቤት ጥቅሙ ምን እደሆነ እንዲናገሩ መጋበዝና በቡድን እና በአጠቃላይ ውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ፡፡ የመጠለያ ከተለያየ የአየር ፀባይ ማለትም ከፀሐይ፣ ከዝናቡ፣ ከቅዝቃዜና ከሙቀት እንደሚከላከልና ከአደገኛ አውሬዎችም ሊከላከል እንደሚችል እንዲዘረዝሩና አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲይዙ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት፡፡ የቤቶች ግድግዳዎችና ጣሪየዎች ከምን፣ ከምን እንደሚሠሩ ለይተው እንዲወያዩ ማበረታታት፡፡
ለምሳሌ፡- ጣሪያ ከቆርቆሮ፣ ከሣር ወይም ከፕላስቲክ፣ ግድግዳ ከእንጨት፣ ከሸክላ ፣ ከብሎኬት፣ ከድንጋይ ከብረት ሊሠራ እንደሚችል ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ፡፡

## (2) ጤነኞች ነን (ደረጃ አንድ)

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-** የቡድን ውይይት ፣የሚና ጨዋታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የቃል ዘገባ፣ የመስክ ምልከታ ፣ ገለፃ

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡-** በጤና ድርጅቶች ተዘጋጅተው የሚወጡ ፖስተሮች ፣ ስዕሎች።

ለአመቻች ማስታወሻ

ትምህርቱ በግል እና በህብረተሰብ ጤና ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ ስለጤና ለመረዳት ያመቻቸው ዘንድ በጤነኛ እና በታመመ ሰው መካከል ባለው ልዩነት ጀምረው የየራሳቸውን ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት፡-**

- ተማሪዎቹ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩ ማበረታታት

- በቡድን ውይይት ውስጥ የታመመ ሰው በአካባቢያቸው አይተው እንደሆነ ወይም በቤተሰባቸው ውስጥ የታመመ ሰው እንዳለ እርስ በርስ እንዲነጋገሩ ማድረግ
- እነዚህ ያዩአቸው የታመሙ ሰዎች ከጤነኛ ሰዎች በምን እንደሚለዩ እንዲወያዩ ማድረግ
- የታመሙ ሰዎች ከህመማቸው ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለባቸው መጠየቅና ለውይይት መጋበዝ
- እራሳቸው ቢታመሙ ምን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ማወያየት
- በውይይት ወቅት የተገኘውን ግንዛቤ ይበልጥ ለማዳበር ተማሪዎች እንደበሽተኛና እንደሃኪም ሆነው የሚና ጨዋ እንዲሠሩ ማበረታታት
- አጠቃላይ ገለፃና ውይይት ማካሄድ

## የግል ንፅህናችንን እንጠብቅ

- የግልን ንፅህና መጠበቅ ጠቃሚ እንዲሆን በትናንሽ ቡድኖች ከፋፍሎ ማወያየት
- የግል ንፅህናን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማበረታታት
- የግል ንፅህናን አለመጠበቅ ከራስ አልፎ ሌሎች ሰዎችን ህመም ሊያመጣባቸው እንዲሚችል ምሳሌ በማንሳት እንዲወያዩ ማድረግ፡፡

  ለምሳሌ፡-ተቅማጥ የያዘው ሰው ሽንት ቤት ሂዶ ሲመለስ እጁን ሳይታጠብ የምግብ ዕቃዎችን ከነካካ ወይም ምግብ ካዘጋጀ ሌሎች በምግብ ዕቃዎቹ የሚጠቀሙ ሰዎች ወይም ምግቡን የሚበሉ ሰዎች በተመሳሳይ በሽታ እንደሚጠቁ መግለፅ፡፡
- የግል ንፅህናን መጠበቅ በበሽታ የመያዝ አጋጣሚዎችን እንደሚቀንስ የተለያዩ ምሳሌዎችን በማንሳት ማወያየት፣ለምሳሌ የዓይን ማዝ በሽታ የወስፋት በሽታ ወዘተ
- በኤድስ የተያዘ ሰው የተለያዩ በሽታዎችን የመቋቋም አቅም ስለሚያጣ በበሽታዎቹ እጅግ ሊጠቃ እንደሚችል በመግለፅ በኤድስ የመያዝ አጋጣሚዎችን እንዲከላከሉ ማስረዳት፣ለምሳሌ ስለታም ነገሮችን በጋራ ከመጠቀም መቆጠብ፣ከሌላ ሰው ጋር የደም ንክኪ አለማድረግ፣ ወዘተ..
- የት/ቤት ግቢ ቆሻሻዎችን አፅድተው በአንድ ቦታ እንዲጠራቀም በማድረግ ንፁህ አካባቢን መፍጠር የሚችሉበትን ልምድ ማስቀሰም

- ውሃን ከበሽታ አምጪ ህዋሳት እንዴት ነፃ ማድረግ እንደሚቻል ማወያየት(ለምሳሌ፣ ውሃን ማፍላት፣የተለያዩ ኬሚካሎች እንደውሃ አጋር ያሉትን መጠቀም፣የታሸጉ የፋብሪካ ውጤት የሆኑ ውሃዎችን ለመጠጥ መጠቀም)
- የማይንቀሳቀስ ወይም የረጋ ውሃ በምን ምክንያት ሊፈጠር እንደሚችል እንዲወያዩ ማድረግ (የተዘጋ ቦይ፣አሸንዳ፣በጉድጓድ ውስጥ፣በተከፈተ ዕቃ ውስጥ የተጠራቀመ ውሃ ወዘተ ለወባ ትንኝ መራቢያ ማገልገሉንና የወባ በሽታ በዚህ ምክንያት መዛመት መቻሉንና ወባን ለመከላከል ምን መደረግ እንዳለበት ይወያዩ)፡፡ የሽንት ቤት ጉድጓድን መክደኛ በማዘጋጀት መጠቀም፣ከሽንት ቤት መልስ እጅ መታጠብ ጠቃሚ መሆኑን ግንዛቤ ማስጨበጥ
- የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ስም እንዲዘረዘሩና የስሜት አካላትን እንዲለዩ ማድረግ ለምሳሌ ዓይን-- የማየት ስሜት አካል፤ ጆሮ-- የመስማት ስሜት አካል መሆኑ በውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ ፣ ለስሜት አካላት መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ እንዲዘረዘሩ ማድረግ፣
- በተለያዩ ተግባራት በማሳተፍ ተማሪዎች ቀለማትን፣ድምፅን፣ሙቀትን፣ቅዝቃዜን፣ ሸካራና ለስላሳ ነገርን፣ ጣፋጭና መራራ የሆኑ (የታወቁ) ነገሮችን እንዲለዩ ጥሩና መጥፎ ሽታን እንዲለዩ ተግባራዊ ትምህርት ውስጥ ማሳተፍ
- ተማሪዎች የማያውቁአቸውን ነገሮች ማሽተት ወይም መቅመስ ጉዳት እንደሚያስከትል እንዲያውቁ ማድረግና በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የሚና ጨዋታ እንዲያሳዩ ማበረታታት፡፡

**ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለክፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን።

## (3) ቤተሰባችን (ደረጃ አንድ)

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-** የቡድን ውይይት፣ የመስክ ምርምር፣ጥያቄና መልስ፣ የቃል ዘገባ፣ የሚና ጨዋታ፣ ገለፃ፣ የመስክ ምልከታ፣

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡-** ፖስተሮች (በጤና ድርጅቶች፣ በግብርና ልማት መስሪያ ቤቶች የሚዘጋጁ ፖስተሮች)፣ የተለያዩ የቤት ዕቃዎች ፣ ሥዕሎች።

ለአመቻች ማስታወሻ

ትምህርቱ ቀደም ሲል ቀርቦ የነበረውን ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በክለሳ እና በተጠናከረ መልኩ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለዚህ ምግብ፣ልብስና መጠለያ ከቤተሰብ ጤና ጋር ያላቸውን ዝምድና እና በቤተሰብ ኑሮ ውስጥ ለምግብ ልብስና መጠለያ መደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ አክብረው እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡ ጥንቃቄዎቹም በግልና በጋራ ጤንነት አጠባበቅ ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን ተረድተው ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባራት በማሳተፍ በሽታን በመከላከል ያተኮረ የጤና አጠባበቅ ልምድ እንዲያዳብሩ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት፡-**

- ተማሪዎች የምግብን ጥቅም ከትላልቅ የቤተሰብ አባላት (ወላጆች) በመጠየቅ ከመጡ በኋላ በትንንሽ ቡድኖች እንዲወያዩ ማድረግ
- በአካባቢያቸው የሚዘወተሩ ምግቦችን በቡድን ውይይቶች ከዘረዘሩ በኋላ እያንዳንዱ የምግብ ዓይነቶች ከምን እንደሚዘጋጅ ይዘርዝሩ
- የዘረዘሯቸውን የምግብ ዓይነቶች ምንጭ እንዲናገሩ ወይም እንዲገልጹ ማድረግ
- የምግቦቹን ምንጭ ከዕፅዋት ወይም ከእንስሳት መሆኑን እንዲገልፁ ካደረጉ በኋላ ከዕፅዋት የተገኙትን ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬ፣አትክልት በማለት እንዲከፋፍሉ ማድረግ፣ በሥዕል እንዲገልፁ ማድረግ
- ከእንስሳት የሚገኙትን ምግቦች ሥጋ፣ ወተት፣እንቁላል ወዘተ በማለት እንዲከፋፍሉና እነዚህን ምግቦች የሚያስገኙትን እንስሳት እንዴት መንከባከብ እንደሚገባ በውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ
- ተማሪዎች የልብስ ዓይነቶችን ለይተው እንደዘረዘሩና እያንዳንዱ ዓይነት ልብስ ለምን ዓይነት ጥቅም እንደሚያገለግል ሀሳብ እንዲለዋወጡ ከተደረገ በኋላ የእያንዳንዱን ልብስ ምንጭ ይግለፁ፡፡ይህም ማለት ዕፅዋት፣ እንስሳት በማለት ከገለፁ በኋላ ልብሶችን በምንጮቻቸው ዓይነት ከዕፅዋት ከእንስሳት ብለው ይለዩ፤ በስዕል እንዲገለፁ ይደረግ
- የመጠለያ ጥቅም፣ዓይነትና ከምን እንደሚሰሩ በውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ፡፡

- በአካባቢያቸው የሚገኙ ቤቶች ዓይነት የመስክ ምልከታ በማድረግ ወይም ወላጆቻቸውን በመጠየቅ በክፍል ውስጥ የቃል ዘገባ እንዲያደርጉ በትናንሽ ቡድኖች ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ፡፡
- የቤት መሥሪያ ቁሳቁሶች በየቤቱ ዓይነት ለይተው እንዲዘረዘሩ ማድረግ (መስክ ምልከታ ካደረጉ በኋላ)
- የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ከነጥቅማቸውና ምንጫቸው የመስክ ምርምር በማድረግ (ወላጆችን፣ሌሎች የጎረቤት ሰዎችን፣ ታላላቅ ሰዎችን በመጠየቅ) በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድኖች በመሆን ሀሳብ ከተለዋወጡ በኋላ የቃል ዘገባ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡
- የቤት ዕቃዎችን ምንጭ ከአካባቢ ከሚገኙ ዕፅዋት ፣ እንስሳት ፣ ግዑዝ ነገሮች ወዘተ በማለት መግለፅ እንዲችሉ ዕድል መስጠት፣ በክፍል እንዲወያዩ ከተደረገ በኋላ አጠቃላይ ገለፃ ማድረግ፡፡
- የቤት ዕቃዎችን በሚሰጡት ጥቅም አንፃር እንዲዘረዝሩ ማድረግ(ለምሳሌ የምግብ ማብሰያ፣ መመገቢያ፣ ጌጣጌጥ፣ ማከማቻ፣ መቀመጫ፣ መኝታ፣ መሥሪያ መሣሪያ፣ ወ.ዘ.ተ. በማለት እንዲከፋፈሉ መርዳት
- ለቤት ዕቃዎች ምን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግና እነዚህ ጥንቃቄዎች ከጤና ጋር ምን ግንኙነት እንዳላቸው እንዲረዱ ማስቻል
- መኖሪያ ቤትን ማፅዳትና ማናፈስ፣ የመፀዳጃ ቤቶችን ሰርቶ መጠቀም ጥቅሙ ምን እንደሆነ መገንዘብ የሚችሉባቸውን የተለያዩ የግልና የቡድን ሥራዎች አዘጋጅቶ ማሳተፍ፡፡ ለመፀዳጃ ቤቶች ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ እንዲያስረዱ ማድረግ
- የቤት ቆሻሻዎችን ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ በማለት እንዲለዩ እና እነዚህ የቆሻሻ ዓይነቶች እንዴት መወገድ እንዳለባቸው ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ፣ ቆሻሻዎችን በማዳበሪያ መልክ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ገለፃ ማድረግና ይህ ለጤና አጠባበቅ ያለውን ጠቀሜታ ማስረዳት
- ተማሪዎች በቤታቸውና በአካባቢያቸው ምግብ ሲዘጋጅ የሚከናወኑ ተግባራትን ምሳሌ አንስተው እንዲወያዩና በጤና ላይ የሚያስከትለውን አወንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲዘረዝሩ ማድረግና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ የምግብ አዘገጃጀት ሂደቶችን እንዴት ማሻሻል (መቀየር) እንደሚቻል እንዲወያዩ ዕድል መስጠት፣ በልብስ ንፅህና እና በቤት ንፅህና አያያዝ ላይ በአካባቢያቸውና በቤታቸው ያለውን

ልምድ በውይይትና በቃል ገለፃ እንዲያደርጉ ማበረታታት፡፡ የልብስና የመኖሪያ ቤት አካባቢ ንፅህና አጠቃቀም ልምዶች ሊያስከትሉ የሚችሉት ጉዳት ምን እንደሆነ እንዲዘረዝሩና እነዚህን ልምዶች ለመቀየር ምን ማድረግ እንዳለበት በቡድን ውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ካደረጉ በኋላ አጠቃላይ ገለፃ መስጠት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

- በአጠቃላይ የምግብ የልብስ ፣የመጠለያ፣ የግል፣ የቤተሰብና ህብረተሰብ አካባቢ በንፅህና መያዝ ጤናን ለመጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ ያለባቸውን ኃላፊነት በግልና በጋራ መወጣት እንዲለዩ መግለፅ።

**ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለከፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን።

## (4) ትምህርት ቤታችን (ደረጃ አንድ)

**ማስተማሪያ ዘዴ፡-** የቡድን ውይይት፣ የሚና ጨዋታ፣ የመስክ ምልከታ፣ የቃል ዘገባ፣ ገለፃ፣ ጥያቄና መልስ፣ የመስክ ተግባራዊ ልምምድ

**የማስተማሪያ መሣሪያ፡-** ሜትር፣ ገመድ፣አመድ( አቧራ)፣ የጠመኔ ዱቄት ፖስተሮች፣ ስዕሎች

ለአመቻች ማስታወሻ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች ህጎችን፣ ደንቦችንና ስነ ስርዓትን ማክበር እንዲለምዱና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሌሎችንም እንዲያስተምሩ ማስቻል ሆኖ፡፡ ይህም ለሰላም የሚያደርገውን ጥቅም እንዲረዱ ለማድረግ ያለው እገዛን ማስረዳት፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ህግን ከማውጣትና ከመተግበር ጀምረው ከሌሎች ጋር በሰላምና በመከባበር መኖር እንዴት እንደሚቻል በቂ ልምምድ የሚያደርጉበትን አጋጣሚዎች መፍጠር ይገባል፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት**

- ተማሪዎች በቤተሰባቸው ውስጥ የሚተገበራቸውን ህጎች በቡድን ውይይት እንዲነጋገሩ እና እንዲዘረዝሩ ማድረግ

ምሳሌ፡- እናትና አባትን ማክበር፣ ታላላቆችንና የጎረቤት ሰዎችን ማክበር፣ ለወላጆች መታዘዝ፣ የቤት ውስጥ ዕቃና ንብረትን በጥንቃቄ መጠበቅ፣ የሰዎችን ንብረትና ገንዘብ አለመንካት፣ የጎበረቤትና የአካባቢ የጋራ ንብረትን መጠበቅ፣ መንከባከብ

- ተማሪዎች ከጎረቤታቸውና ከአካባቢያቸው ጋር በሰላም ለመኖር መፈፀም ያለባቸውን ህጎች እንዲዘረዝሩ ማድረግ

  ምሳሌ፡- የጎረቤት ሰዎችን ማክበር፣ ሰላምታ መስጠት፣ መታዘዝ ፣ ትሁት መሆን፣ ተግባቢ መሆን፣ በችግር ላይ መረዳዳት፣ መፈቃቀር፣ መተባበር
- በቤትና በአካባቢ ህብረተሰብ ውስጥ ህግን አክብሮ መኖር ጠቀሜታው ምን እንደሆነ ወላጆቻቸውን ጠይቀው በመምጣት በክፍል ውስጥ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ ማድረግ
- በትምህርት ቤት ውስጥ መከበር የሚገባቸውን ህጎች እንዲዘረዝሩ የቡድን ሥራ መስጠት፣ ለምሳሌ ያህል
  - የትምህርት ሰዓት ማክበር
  - ከትምህርት ገበታ ላይ እንዳይቀሩ ፣ መቅረት ካለባቸው ፈቃድ መጠየቅ እንዳለባቸው
  - ታላላቆችን ማክበር
  - መምህራንን መታዘዝ
  - የተሰጣቸውን የክፍልና የቤት ሥራ መስራት
  - የሌሎችን ተማሪዎች ንብረት አለመንካት
  - ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አለመጣላት( አለመሰዳደብ፣ አለመደባደብ)
  - የግል ንፅህናን መጠበቅ
  - የሰንደቅ ዓላማ ሥነ ሥርዓት ማክበር
  - ከትምህርት ሲቀሩ በቂ ማስረጃ ማቅረብ
- ከህብረሰተሰብ አባላት ጋር ተግባብተው በሰላም መኖር እንዳለባቸው ግንዛቤ ለማስጨበጥ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎች የሚና ጨዋታ አዘጋጅተው በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ ሰላምታ መለዋወጥ፣ ግልፅ መሆን ፣ ተግባቢ መሆን፣ፍቅርን መግለፅ፣ እርዳታ ማድረግ፣ መተባበር፣ ወዘተ ጉዳዮች ላይ የሚና ጨዋታ ማቅረብና አጠቃላይ ውይይትና ገለፃ ማድረግ

- ተማሪዎች የትራፊክ አደጋን በማስመልከት የመስክ የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ፤ሜትር ገመድና አመድ በመገልገል በት/ቤት ግቢ ውስጥ መንገድ አስመስለው እንዲሰሩ እና የትራፊክ ደንቦችን እንዲለማመዱ ማድረግ

  - መንገድ ማቋረጥ የሚቻለው ተሽከርካሪ አለመኖሩን ካረጋገጡ በኋላ መሆን እንዳለበት
  - በመንገድ ዳር መጫወት እንደሌለባቸው
  - በመንገድ ላይ ግራ ጠርዝ ይዘው መጓዝ እንዳለባቸው
  - በከተሞች ውስጥ ከሆነ የትራፊክ መብራት ምልክቶችን ምንነት ተረድተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ
  - መንገድ ማቋረጥ በዜብራ ምልክት ላይ መሆን እንዳለበት እንዲረዱ ማስቻል፥

- የትራፊክ አደጋ በአካባቢቸው አጋጥሞ ከሆነ በቡድን ውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ፣ ያዩት ወይም የሰሙት የትራፊክ አደጋ ምን እንደሆነና በምን ምክንያት ሊከሰት እንዲቻል በውይይት ለመግለፅ እንዲችሉ በመስክ ምርምር ወላጆቻቸውን ወይም የጎረቤት ሰዎችን ጠይቀው እንዲገልጹ ማድረግ
- የትራፊክ አደጋን መቀነስ እንዲቻል ምን መደረግ እንዳለበት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግና አጠቃላይ ገለፃ መስጠት።

  **ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለክፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን።

## (5) አካባቢያችን (ደረጃ አንድ)

**ማስተማሪያ ዘዴ፡-** የመስክ ምልከታ፣የመስክ ምርምር፣የቡድን ውይይት፣ የሚና ጨዋታ፣ ክርክር ፣ የቃል ዘገባ፣ ጥያቄና መልስ፣ገለፃ፣ ሳይንሳዊ ሙከራ

**የማስተማሪያ መሣሪያ፡-** የወረቀት ውልብልቢት፣ ቁርጥራጭ ወረቀቶች ሥዕሎች፣ ፖስተሮች፣ ዱላ፣ ብርጭቆ ፣ ቀሰም፣ አፈር ፣ውሃ ፣ ከአፈር የተሠሩ ቅርፃ ቅርፆች

ለአመቻች ማስታወሻ፡-

በዚህ ምዕራፍ  የቀረበው  ትምህርት አካባቢ ማለት ህይወት  ያላቸውና የሌላቸው ነገሮች መስተጋብር ፈጥረው የሚገኙበት መሆኑን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሲሆን፡፡ ተማሪዎች አፈር፣ አየርና ውሃ በአካባቢ ውስጥ መገኘታቸውንና የእነዚህን ጥቅም ለይተው በማወቅ ህይወት ያላቸው ነገሮች እንደ እንስሳት እና ዕፅዋት እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የትምህርት አቀራረብ ሂደት

- የአየርን መኖር ለማወቅ የተለያዩ ሙከራዎችን እንዲሠሩ ማበረታታትና መሳተፍ፡፡ ለምሳሌ የወረቀት ውልብልቢት ሰርተው እንዲጫወቱበት ማድረግ፣ ውሃን በብርጭቆ ግማሽ ድረስ ሞልተው ቀሰም በማስገባት በአፋቸው እየነፉ የአየር እንክብሎች ሲፈጠሩ እንዲያዩ ማድረግ፣ቁርጥራጭ ወረቀቶችን (ካርቶኖችን) በመጠቀም አየር መቅዘፍና ፊታቸው ላይ አየር ሲመላለስ እንዲገናዘቡ ማድረግ፣
- አየር ህይወት ላላቸው ነገሮች የሚሰጠው ጥቅም ምን እንደሆነ እንዲገልፁ መጠየቅ፡ ሰው አየር ባያገኝ ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲናገሩ ማድረግ፤ የነፋስ መኖር ምን ጥቅም እንደሚሰጥ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ ለምሳሌ ፀሐይ በሌለበት ጊዜ ታጥቦ የተሰጣ ልብስ እንዲደርቅ የሚያደርገው አየር መሆኑን ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ተማሪዎች የውሃን ምንጭ(መገኛ) ወላጆቻቸውን በመጠየቅ፣ የመስክ ምልክት በማድረግ በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድኖች ተከፋፍለው ውይይት እንዲያደርጉና እንዲዘረዝሩ በመጨረሻም የቃል ዘገባ ለጠቅላላው ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ (ለምሳሌ፣ ከዝናብ ፣ከምንጭ፣ከጉድጓድ፣ ከቧንቧ፣ ከወንዝ፣ ከሀይቅ፣ ከባህር፣ ውቅያኖስ መገኘቱን አጠቃላይ ገለፃ መስጠት
- ውሃ ለተክሎችና ለእንስሳት በህይወት መኖር በጣም ጠቃሚ መሆኑን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ፣ውሃ ከሌላ ህይወት እንደማይኖር ማስረዳት
- ተክሎች ውሃን በሥሮቻቸው አማካኝነት ስበው ሲጠቀሙ እንስሳት በአፋቸው ውሃን እንደሚጠጡ በቡድን ውይይት ከተነጋገሩ በኋላ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ
- አፈር ህይወት ካላቸው ነገሮች መካከል ለማን ጥቅም እንደሚሰጥ እንዲያስረዱ ማድረግ፣ የመስክ ምልከታ በማድረግ አፈር ለዕፅዋት ምን ጥቅም እንዳለው እንዲመራመሩ፣ እንዲወያዩና የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ

- አፈር ከተክሎች ውጭ በሰው ልጆች የሚሰጠውን ጥቅም በውይይት ሀሳብ ከተለዋወጡ በኋላ የቡድን ዘገባ ለክፍሉ በሙሉ ተራ በተራ እንዲያቀርቡ ማበረታታትና መጋበዝ፡፡ ለምሳሌ፡- የቤት መሥሪያ ሸክላ የሚሠራበት መሆኑን፣ ለእንጨት ቤቶች የግድግዳ ምርጊት እንደሚያገለግል፣ የሸክላ ድስት፣ ምጣድ እና ሌሎች ቅርፃቅርጾችን ለመሥራት እንደሚረዳ እንዲገልፁ በጥያቄና መልስ ማሳተፍ የክፍልና የቤት ሥራ መስጠት፤ ወላጆቻቸውን ጠይቀው ስለአፈር ጥቅም በሰፊው እንዲያብራሩ ማድረግ፡፡
- በት/ቤት ግቢ ውስጥ አፈር ቆፍረውና አቡክተው የተለያዩ ፊደላት ቅርጾችን፣ ክብ ነገሮችን፣እንደኳስ ድቡልቡል የሆነ ቅርፆችን እንዲሠሩ በተግባራዊ ልምምድ ማሳተፍ
- የመስክ ምልከታ እንዲያደርጉና በአካባቢው የሚገኙ ተክሎችን ከተመለከቱ በኋላ ዛፎች፣ ቁጥቋጦ፣ ሣር፣ ትናንሽ ተክሎች ብለው እንዲመድቡ ማበረታታት
- በመስክ ምልከታ ወቅት ያዩአቸው ተክሎች ጥቅማቸው ምን እንደሆነ በጥያቄና መልስ ማወያየት ( ለምግብነት፣ ለቤት መሥሪያ ለውበት፣ ለማገዶ፣ ለቤት ቁሳቁስ መሥሪያ፣ ወ.ዘ.ተ) አገልግሎት እንደሚውሉ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ለአፈርና ለተክሎች ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ እንዲገልፁ መጠየቅ ፣ አፈርና ተክሎችን መንከባከብ አካባቢን መንከባከብ መሆኑን እንዲረዱ ማድረግ
- የሚያውቁአቸውን እንስሳት ስም እንዲዘረዝሩ ማድረግ (አስቀድሞ ከወላጆቻቸው ጠይቀው እንዲመጡ ማድረግ)
- የዘረዘሩአቸውን እንስሳት ለማዳ (የቤት) እንስሳ እና ለመዳ ያልሆኑ (የዱር እንስሳት) ብለው እንዲመድቡ ማድረግ
- የሚያውቁአቸውን እንስሳት (የቤት ወይም የዱር) በሥዕል እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- የቤት እንስሳትን ጥቅም መጠየቅና ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ (የሥጋ፣ የወተት፣ የእንቁላል፣የቆዳ ወዘተ ምንጭ መሆናቸው)፣ ድመትና ውሻ ምን ጥቅም እንደሚሰጡ መጠየቅ
- እንደ አህያ፣ በቅሎ ፣ፈረስ፣ ግመል ያሉት ለመጓጓዣነት እንደሚያገለግሉ እንዲረዱ በጥያቄና መልስ ማሳተፍ
- ለእንስሳት መደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ እንዲያስረዱ ማበረታታት

- እንስሳትን ምግብ ማብላት ውሃ ማጠጣት መጠለያ ቤት እንዲሠራላቸው ማድረግ ምን ጥቅም እንደሚሰጥ መጠየቅና ማወያየት
- የአካባቢያቸውን ህብረተሰብ የሥራ መስክ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ
- አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ በየትኛው ሥራ ላይ ተሰማርቶ እንደሚገኝ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ
- የሥራ ዓይነቶችን የግልና የመንግሥት ብለው እንዲከፋፍሉ ማድረግ
- ተማሪዎች የራሳቸው ሥራ ምን እንደሆነ እንዲገልፁ መጠየቅ፣ የወላጆቻቸውን ሥራ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ሰው ሥራ መሥራቱ ምን ምን ጥቅሞች እንደሚያስገኝ አስበው እንዲወያዩና ለክፍል ተማሪዎች እንዲገልፁ ማድረግ
- የሰው ልጅ ሦስቱ መሠረታዊ ፍላጎቶች( ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ) የሚያገኙት በሥራ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማበረታታት፣ ማገዝ
- በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ ሰዎች ሥራቸውን በትክክል ባይወጡ የሚመጡ ችግሮች ምን እንደሆነ መጠየቅና በቡድን ተወያይተው እንዲዘረዝሩ ማድረግ ለምሳሌ ፦ በሰንጠረዡ የተሰጠውን ምሳሌ በማየት የተቀሩትን ሙሉ፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መስክ | አለመሥራት የሚያስከትለው ችግር |
|---|---|---|
| 1. | ህክምና | ሰዎች በበሽታ ይጠቃሉ ብሎም ይሞታሉ፡፡ |
| 2. | | |
| 3. | | |
| 4. | | |
| 5. | | |
| 6. | | |
| 7. | | |

**ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለክፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን

## (6) ተፈጥሮአዊ አካባቢያችን (ደረጃ ሁለት)

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በምልከታ፣ የቡድን ውይይት፣ ሳይንሳዊ ሙከራ፣ ምደባ፣ ሰርቶ ማሳያ፣ ገለፃ፣ ጥያቄና መልስ፣ ክርክር

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡-** ሥዕሎች፣ ፖስተሮች ፣ የተለያዩ ቀለማት፣ ተጠቅላይ ሜትር፣ ማስመሪያ፣ ሰዓት፣የክብደት መለኪያ ሚዛን፣ የተለያዩ ሰው ሠራሽ ዕቃዎች ፣ ተፈጥሮአዊ ነገሮች፣ ቻርቶች፣ የተለያዩ የአፈር ዓይቶች

ለአመቻች ማስታወሻ

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን ለይተው በማወቅ የክስተቶችን አሉታዊ ጎኖች መከላካል እንዲችሉ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ሳይንሳዊ ዘዴ በመጠቀም ቀለል ያሉ ሙከራዎችን እንዲሠሩ የሚረዳ ነው፡፡ በሳይንሳዊ ዘዴ በመጠቀም ነገሮችን እንደየፀባያቸው በተለያዩ መንገዶች መመደብ፣ ተፈጥሮን መንከባከብ የሚቻልበትን ልምድና ዕውቀት ማዳበር እንዲችሉ ለማድግ ይረዳል፡፡ የተለያዩ ሳይንሳዊ መለኪያዎችን በመጠቀም ርቀትን፣ ክብደትን፣ጊዜን፣ ወ.ዘ.ተ እንዲላኩ ማድረግና ከልማዳዊ መለኪያዎች ጋር ያላቸውን ልዩነቶች በንፅፅር እንዲለዩ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የአንዳንድ እንስሳትን አረባብና ለእፅዋት አበቃቀል መሠረታዊና አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ነገሮች ( አየር፣ ውሃ፣ አፈር) ለይተው እንዲዘረዝሩ ማድረግ ጠቃሚ እንደሆነ ይጠበቃል፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት**

- ተማሪዎች በቡድን ሆነው በቀንና በሌሊት መካከል ያለውን ልዩነት ተወያይተው እንዲዘረዝሩ ማድረግ
- ወቅቶችን ክረምትና በጋ በማለት እንዲከፋፍሉና ልዩነታቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት
- ጎርፍና ድርቅ ምን ጊዜ እንደሚበዙ መጠየቅ፣ ጎርፍና ድርቅ የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንዲያብራሩ የቡድን ውይይት እንዲያካሂዱ ማበረታታት፡፡
- የመስክ ምልከታ በማድረግ በጎርፍ የተሸረሸሩ ቦታዎችን እንዲመለከቱና ያገኙትን ግንዛቤ በክፍል ውስጥ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ፤ ጎርፍን እንዴት መከላከል ይችላል በሚል ርዕስ ላይ ክርክርና ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ

- የዝንብ ወይም የቢራቢሮ የህይወት ዑደት ደረጃዎችን የሚያሳዩ ቻርቶች በማሳየት በራሳቸው ደብተር ውስጥ ሥዕሉን መልሰው እንዲሰሩ ማድረግ፣ማብራሪያና ገለፃ መስጠት።
- የተለያዩ የእህል ዘሮችን በተለያዩ ሳጥኖች ውስጥ በማብቀል የብርሃን እና የውሃን አስፈላጊነት እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- ያበቀሉትን ተክል በመንቀል ሥር፣ ግንድና፣ ቅጠል የተባሉ ክፍሎችን መለየት
- የተለያዩ የመለኪያ መሣሪያዎችን በመጠቀም ጊዜን፣ ክብደትንና ርዝመትን መለካት፣ የየራሳቸውን ቁመት በመለካት ጭምር እንዲለማመዱ ማድረግ
- የተለያዩ ቁሳቁሶችን ሰው ሠራሽንና ተፈጥሮአዊ በማለት እንዲመደቡ ዕድል መስጠት። እነዚህን የመደቧቸውን ነገሮች በየመደባቸው ሥር ስም ዝርዝራቸውን እንዲፅፉ ማድረግ።
- ያበቀሉትን ዕፅዋት በሥዕል እንዲያሳዩ መጠየቅና ማበረታታት፣
- ያበቀሉአቸውን የተለያዩ ተክሎች ቁመት በመለካትና በዓይን በመመልከት ያወዳድሩ( ለምሳሌ ውሃ ያገኘና ያላገኘ ተክል፣ በብርሃንና በጨለማ ቦታ የበቀለ ተክል፣ አየር ያገኘና ያላገኘ ተክል ያላቸውን ልዩነት ማወዳደር / ማነፃፀር)
- በቤታቸውና በአካባቢያቸው የሚገኙ እንስሳትን ስም ዝርዝር እንዲያዘጋጁ ከተደረገ በኋላ እነዚህን እንስሳት የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም እንዲመደቡ ማድረግ(ለምሳሌ በአረባባቸው ሁኔታ፣ በአመጋገባቸው ፣ በሰውነታቸው ሽፋን፣ በእንቅስቃሴአቸው፣ በመኖሪያቸው ወዘተ በመመደብ እንዲዘረዝሩ ማድረግ) ለእያንዳንዱ ዝርዝር ሥዕል ማዘጋጀት እንዲችሉ ማበረታታት
- ከእንስሳት የሚገኙ ጥቅሞች ላይ ወላጆቻቸውን ጠይቀው በመምጣት በክፍል ውስጥ ውይይት እዲያካሂዱ፣ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ( ለምሳሌ፣ ሥጋ፣ ወተት፣ ዓይብ፣ ቅቤ፣ ቆዳ፣ ሌጦ፣ ፀጉር/ሱፍ)
- ለእርሻ ሥራ የሚያገለግሉ እንስሳት ሊደረግላቸው የሚገባውን ጥንቃቄ ከውይይት በኋላ የቃል ዘገባ በማቅረብ በክፍል ደረጃ እንዲወያዩበት ማድረግ
- እንስሳቱን ለመመገብ የሚጠቀሙባቸውን ዕቃዎች ስዕል እንዲያዘጋጁ መርዳት
- የተለያዩ የአፈር ዓይቶች እንዲለዩ ማበረታታት፣ አፈር ለተክሎች ያለውን ጥቅም እንዲናገሩ መርዳት፣ለአፈር መጠበቅ መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ አፈር እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል ውይይት እንዲያካሂዱ መርዳት

- በህብረተሰባቸው ውስጥ ውሃ እንዴት ባለሁኔታ ጥቅም ላይ እንደሚውል በውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ፣ ውሃ እንዴት ሊበከል እንደሚችልና ለብክለት መከላከል ምን መደረግ እንዳለበት በውይት፣ በሚና ጨዋታ፣ በክርክር እንዲያቀርቡ ማድረግ
- የአየር ብክለት መንግዶችና የመከላከያ ዘዴዎችን እንዲዘረዝሩ ማበረታታት
- የደኖችን ጥቅም እንዲያስረዱና እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣የደን መጨፍጨፍ የሚያስከትለውን ጉዳት እንዲገልፅ ማድረግ፣ የደን መጨፍጨፍን ለመከላከል ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ዕውቀትና ልምድ እንዲያካብቱ ማድረግ
- የዱር እንስሳትን ጥቅም ወላጆቻቸውን ጠይቀው መጥተው የቃል ዘገባ በማቅረብ በአጠቃላይ ውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ
- የዱር እንስሳትን በሥዕል እንዲያሳዩ ማበረታታት
- የዱር እንስሳት የሚደርስባቸውን ጉዳቶች በውይይት ሀሳብ በመለዋወጥ እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ ሊደረግላቸው የሚገባውንም ጥንቃቄ እንዲያስረዱ ማድረግ
- ተማሪዎች ሙቀትና ብርሃን የጉልበት ምንጭ መሆናቸውን እዲረዱ ለማስቻል በምልከታ፣ በሙከራ ወዘተ  ያገኙትን ውጤት በክፍል ከተወያዩበት በኋላ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ
- የሙቀት ምንነትና ሊያስከትል የሚችለውን ተፅዕኖና ጥቅም እንዲገልጹ ማድረግ( ለምሳሌ በረዶን ወደ ውሃ ፣ ውሃን ወደ እንፋሎት መለወጡን፣ አንዳንድ ነገሮችን ለማቅለጥ እንደሚጠቅም፣ ምግብ ለማብሰልና በሽታ አምጪ ተህዋስያን እንደሚገድል ፣ ወ.ዘ.ተ)
- ብርሃን ከፍተኛ ጉልበት እንዳለውና የሚቀትን ኃይል ሊያመጣ እንደሚችል እንደረዱ የእጅ ሌንሶችን በጥንቃቄ በመጠቀም ደረቅ ቅጠሎችን ወይም ቁርጥራጭ ወረቀቶችን በመቃጣል ሙከራ እንዲያካሄዱ መርዳት
- የድምፅ አፈጣጠርን እንዲገነዘቡ በማስመሪያና የብር ማሠሪያ ላስቲክ በመጠቀም እርግብግቢት የመፍጠር ሙከራ እንዲያካሂዱ ማድረግ፣ ድምፅ በጠጣር፣ በፈሳሽ በአየር ውስጥ መሄድ መቻሉን ማስረዳት
- በአካባቢያቸው የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ስም እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ ከተቻለም የሙዚቃ መሣሪያዎቹን ወደ ክፍል እንዲያመጡ መጋበዝ

- ወደ ክፍል የመጡ መሣሪየዎችን መጫወት የሚችሉ ካሉ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲጫወቱ ማበረታታት፣ በአካባቢ ከሚገኙ ጥሬ ዕቃዎች በመጠቀም እንደ ክራርና ዋሽንት ከበሮ ያሉ ነገሮችን ሠርተው እንዲጠቀሙ ማበረታታት
- የኃይልን ምንነትና ተፅዕኖ ለማወቅ የተለያዩ ሙከራዎች ማድረግ ( ለምሳሌ አንድ ነገር ለመነተት ኃይል ያስፈልጋል ለመግፋትም ኃይል ያስፈልጋል፣ ተፅዕኖዎችም አቅጣጫ መቀየር ቦታ መቀየር ቅርፅ መቀየር ግፊት መቀየር ወዘተ)
- ቀላል መኪናዎች የሚባሉት አነስተኛ ኃይል በመጠቀም ሥራን በቀላሉ ለመሥራት የሚያስችሉ ነገሮች መሆናቸውን የተለያዩ ቀላል መኪናዎች ( ለምሳሌ ዘንባይ ወለል/Inclined plane) መፈንቀል፣ በከራ ወዘተ በመጠቀም ሙከራ እንዲያደርጉ መርዳት፣ ዘንቦይ ወለሎችን፣ መፈንቅሎችንና በከራዎችን በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ሠርተው በክፍል ውስጥ እንዲጠቀሙ ማበረታታት።
- **ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለክፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን።

## (7) ህብረተሰባችን (ደረጃ አንድ)

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-** ውይይት፣ የመስክ ምልከታ ፣ ክርክር፣ የቃል ዘገባ፣ ፕሮጀክት ሥራ፣

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡-** የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች ፣ የእህል ዘሮች ፣ ውሃ፣ ሸክላ ዕቃዎች፣ የተጣሉ የቤት ውስጥ ውሃ መያዣ ዕቃዎች፣ መኮትኮቻ፣ አካፋ፣ ዶማ፣ ሥዕል ፣ ፖስተር፣ ወስን ጥናት( Case Study)

ለአመቻች ማስታወሻ

በዚህ ምዕራፍ የቀረበው ትምህርት ተማሪዎች የህፃናትን መብቶች ጠንቅቀው እንዲያውቁና እንዲከበርላቸው እዲያደርጉ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ሲሆን የየዕለቱ የግልና የቡድን ተግባራትን ለማከናወን ዕቅድ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ እንዲረዱና እንዲተገብሩ ለማድረግ እንዲሁም ለማህበረሰብ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮች ማለትም የጉልበት አስፈላጊነት፣ የጉልበት ምንጮች፣ የመገልገያ ቁሳቁስ፣ የየዕለት ሥራዎችና የሥራ ወቅቶችን ለይተው እንዲያውቁና በተግባር ላይ እንዲፈትሹ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው

**የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት፡-**

- ህፃናት ያላቸውን መብት ያውቁ እንደሆነ ለመገመት በቡድን ውይይት በማሳተፍ መብቶችን እንዲዘረዝሩ ዕድል መስጠት (ለምሳሌ የመማር መብት፣ ከጉልበት ብዝበዛ ነፃ የመሆን መብት፣ ምግብ ልብስና መጠለያ የማግኘት መብት፣ የመናገር መብት፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- የህፃናት መብት ተጥሰው አይተው ወይም ሰምተው ከሆነ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲገልጹ ማድረግ፣ የህፃናትን መብት የጣሱ ሰዎች ምን ርምጃ እንደተወሰደባቸው እንዲገልጹ ያድርጓቸው።
- የየዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያካሂዱትን ሥራ በዕቅድ ነድፈው ተግባራዊ ቢያደርጉ፣ ጊዜያቸውን ጉልበታቸውን ለመቆጠብ እንደሚረዳ ለማወቅ የሚሠሩትን ሥራ ከዘረዘሩ በኋላ ምን ጊዜ እንደሚሰሩ ንድፍ ማዘጋጀት( ለምሳሌ የቤት ሥራ ምን ጊዜ እንደሚሠሩ፣ ምን ጊዜ እንደሚተኙ፣ ከመኝታ ምን ሰዓት እንደሚነሱ፣ ፊታቸውን ምን ጊዜ እንደሚታጠቡ፣ ምን ጊዜ ት/ቤት እንደሚሄዱ ዝርዝር ተግባራትን ካወጡ በኋላ ጊዜ እንዲመደቡላቸው ማድረግ
- በአካባቢያቸው ያለው ህብረተሰብ ምን ዓይነት ሥራዎችን ሠርቶ እንደሚተዳደር ከዘረዘሩ በኋላ አያንዳንዱ ሥራ ምን ጊዜ እንዲሠራ የጊዜ ሰሌዳውን እንዲያወጡ (ለምሳሌ ገበሬ የሆኑ ሰዎች መሬት የሚያለሰልሱት፣ ዘር የሚዘሩት፣ የሚኮተኩቱት የሚያጭዱትና የሚከምሩበት ወይም የሚወቁበት ጊዜ መቼ እንደሆነ እንዲመድቡ ማድረግ)
- ለማህበረሰቡ ጉልበት አስፈላጊ መሆኑንና ይህንኑ ጉልበት ከምን ምንጭ ማግኘት እንደሚቻል መገመት እንዲችሉ በቤታቸው ውስጥ ጉልበት ለምን እንደሚፈለግ እንደዘረዝሩ በቡድን ማዋቀር (ለምሳሌ ምግብ ለማብሰል የኤሌክትሪክ ወይም የማገዶ እንጨት ጉልበት ተፈላጊ መሆኑን፣ ልብስ ለማድረቅ የፀሐይ ወይም የነፋስ ጉልበት ማስፈለጉን፣ መኪና እና ሌሎች ተሽከርካሪዎች ጉልበት የሚያገኙት ከነዳጅ መሆኑን እንዲረዱ እና ይህም ጉልበት ለትራንስፖርት አገልግሎት አስፈላጊ መሆኑን መረጃ ማስጨበጥ
- የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ሞዴል መሥራት እንዲችሉ የፕሮጀክት ሥራ በግል መስጠት (ንድፍ ማውጣት፣ ቅርፅ ማውጣት፣ ማስጌጥ)

- ለሰብል ምርት የድብልቅ አፈር አስፈላጊነቱን በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ ዕፅዋት በማብቀል በሙከራ እንዲያሳዩ ማድረግ
- የንብ የህይወት ዑደት በማጥናት ከዝንብና ወባ ትንኝ የህይወት ዑደት ጋር እንዲያወዳድሩ ማድረግና የንብ ጥቅም ምን እንደሆነ እንዲያስረዱ ማድረግ።

**ግምገማ፡-** በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለከፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን።

## (8) ህብረተሰባችን (ደረጃ ሁለት)

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-** ውይይት፣ የመስክ ምልከታ ፣ ክርክር፣ የቃል ዘገባ፣ ፕሮጀክት ሥራ፣

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡-** ካርታ ( የኢትዮጵያ ፣ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የቀበሌ))

ለአመቻች ማስታወሻ

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ተማሪዎች አቅጣጫንና የቦታ አቀማመጥን እንዲለዩ ስለ ቤታቸው ፣ ት/ቤታቸው፣ ቀበሌአቸው፣ ወረዳ፣ ዞን እና ክልላቸው አቀማመጥ/ መገኛ ለይተው እንዲያውቁ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ስለወረዳቸው ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ፣ ስለሥራ ክቡርነት ስለታሪካዊ ቅርሶች አጠባበቅና ጠቀሜታ፣ ስለብሔራዊና ክልላዊ ሰንደቅ ዓላማ፣ወዘተ ያላቸውን ግንዛቤ ይበልጥ የሚያሰፉበት ትምህርት ነው፡፡

### የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት

- ተማሪዎች መጀመሪያ አራቱን አቅጣጫዎች እንዲለዩ በሥዕልና በተግባር ሥራ ማሳተፍ
- አቅጣጫዎችን መለየት ከቻሉ በኋላ በክፍላቸው ወለል ላይ አንድ ድንጋይ መሐል በማስቀመጥ ሌላውን ከድንጋይ በስተምሥራቅ፣ ሁለተኛውን በስተምዕራብ፣ ሶስተኛውን በስተሰሜንና አራተኛውን በስተደቡብ በማስቀመጥ የአንድን ነገር መገኛ አቅጣጫ ኬላው ጋር በማወዳደር እንዲለዩ ማለማመድ፣ ከዚያም በኋላ ተማሪዎቹን ወደ ት/ቤቱ ሜዳ በማውጣት በአካባቢው የሚገኙ መንገዶች ፣ ቤቶች፣ ዛፎች፣ ተቋሚት፣ ወዘተ... ከት/ቤቱ በየትኛው አቅጣጫ ላይ እንዳሉ እርስ በራስ እንዲወያዩ ማድረግ

- እያንዳንዱ ተማሪ የራሱ መኖሪያ ቤት ከት/ቤቱ በየትኛው አቅጣጫ እንዳለ እንዲለይና በሥዕል እንዲያሳይ ማድረግ
- ትምህርት ቤታቸው ከአጎራባች ሌሎች ተቋማት በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኝ ስዕል በመሳል ያስቀምጡ (ለምሳሌ መስጊድ፣ቤተክርስቲያን፣ጤና ጣቢያ፣የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት) የየራሳቸው መኖሪያ ከየትኛው ተቋም በየትኛው አቅጣጫ ላይ እንዳለ ስዕል በመሳል እዲያሳዩ ማድረግ
- በወረዳቸው ውስጥ ያሉ የተለያዩ ጠቃሚ ቦታዎችን የወረዳውን ካርታ በመሳል እንዲያመለክቱ ማድረግ፣ የተለያዩ የወረዳቸውን አካባቢዎች በመጎብኘት ወንዝ፣ ተራራ፣ ሸለቆ ወዘተ የት የት እንደሚገኝ በካርታ የተደገፈ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማበረታታት፣ በቡድን መድቦ ማሰራት
- በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ተቋማት ስም ዝርዝር እንዲያዘጋጁና እነዚህ ተቋማት በወረዳው ውስጥ በየት ሥፍራ እንደሚገኙና አንዱ ከሌላው በምን አቅጣጫ እንደሚገኝ ካርታ ስለው እንዲያሳዩ ፕሮጀክት ሥራ መስጠት
- የወረዳቸውን ካርታ እና በውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን ጭቃ በመጠቀም ሞዴል እንዲሰሩ ማድረግ
- በወረዳቸው ስለሚገኘው የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ በቡድን ተወያይተው እንዲዘረዝሩ ማድረግና በእያንዳንዱ የሥራ መስክ የተሰማሩትን ሰዎች ብዛት በግምት እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- እያንዳንዱ ሰው በተሰማራበት የሥራ መስክ ባይሠራ ሊደረስ የሚችል ችግር ምን እንደሆነ እንዲወያዩ ማድረግና የሥራን ክቡርነት እንዲረዱ ማድረግ
- የወረዳቸውን አቀማመጥ ከሌሎች አጎራባች ወረዳዎች ጋር በማነፃፀር እዲለዩ ይህንኑ በካርታ አስደግፈው የቃል መግለጫ እንዲሰጡ ማድረግ፣ ከዚያም ክልላቸው ከሌላው ክልል ጋር ያለውን አቀማመጥ የኢትዮጵያን ካርታ በመሳል እዲያሳዩ ማበረታታት፣ ይህንኑ በራሳቸው ደብተር ውስጥ እንዲስሉ ማድረግ
- የክልልና ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማትን ዝርዝር እዲፅፉ ካደረጉ በኋላ የተለዩ ቀለማትን በመጠቀም የክልልና ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማዎችን በመሳል እንዲያቀልሙ ማድረግ
- የክልላቸውን የተለያዩ ተቋማት ስም ዝርዝርና መገኛ አቅጣጫ ( ቦታ)፣ የተረካዊና ባህላዊ ቅርሶች መገኛ፣ የቱሪስት መስህቦች መገኛ በስዕል እንዲያሳዩ ማድረግ፣ ሀገር

ጎብኚ ለሆኑ ቱሪስቶች ማደረግ ያለባቸውን ክብርና (እንክብካቤ) አቀባበል እንዲገልጹ ማድረግ

- በክልላቸው ውስጥ በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው የላቀ ውጤት ያስገኙ የልማት ጀግኖችን ስም እንዲዘረዝሩ እና አስተዋጽአቸው ምን እንደሆነ በየስማቸው አንፃር ጽፈው እንዲገልጹ ቢቻል ፎቶግራፋቸውን በክፍል ውስጥ እንዲያስቀምጡ ማበረታታት

| **ተ.ቁ** | **የሥራ መስክ** | **የልማት ጀግና ስም** | **ያበረከተው/ችው አስተዋፅኦ** |
|---|---|---|---|
| 1. | ግብርና | | |
| | | | |
| 2 | ንግድ | | |
| | | | |
| 3 | ሀገርን መከላከል | | |
| | | | |
| 4 | ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ | | |
| | | | |
| 5 | | | |
| | | | |
| 6 | | | |
| | | | |
| | | | |

***ግምገማ***፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለክፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን

## (9) ሰውነታችን (ደረጃ ሦስት)

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-** ምልከታ፣ ውይይት ፣ ክርክር፣ ምደባ፣ የቃል ዘገባ፣ ጥያቄና መልስ፣ ፕሮጀክት

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-** ፖስታዎች ፣ ሥዕሎች፣ ሞዴሎች፣ በአካባቢ የሚመረቱ የምግብ ዓይነቶች ናሙና፣

ለአመቻች ማስታወሻ

በዚህ ምዕራፍ የቀረበው ትምህርት ስለምግብ ዓይነቶች ምንነትና ጥቅም ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ሲሆን በምግብ መፍጨት እና ዝውውር ውስጥ ዋና ሚና ያላቸውን የሰውነት ክፍሎች ተግባርና አሠራር ጠንቅቀው እንዲረዱ፣ ጤናማና የተመጣጠነ ዕድገት ያለው ደስተኛ ቤተሰብ ለመፍጠር የቤተሰብ ምጣኔን ጥቅም እንዲገነዘቡና በወደፊት ህይወታቸው እንዲተረጉሙ አስፈላጊውን ዕውቀት የሚያስጨብጥ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በጉርምስና ወቅት በወንዶችና ሴቶች ልጆች የሚከሰቱ የአካል ለውጦችን እንዲለዩ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከጋብቻ በፊት መፈፀም የሚያስከትለውን ችግር በመረዳት እንዲጠነቀቁ፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን አጣርተው እዲያውቁና ኤድስን ለመግታት እራሳቸውን ከመጠበቅ አልፈው ለሌሎች የህብረሰቡ አባላት ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄና በኤድስ የተያዙ ሰዎችን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ተገቢውን ግንዛቤ የሚጨብጡበት ነው፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት፡-**

- ስድስት ዓይነት ንጥረ ምግቦች መኖራቸውንና እነዚህም ንጥረ ምግቦች ለሰውነታችን የተለያየ ጥቅም (ኃይል፣ ዕድገት፣ ከበሽታ መከላከል) እንደሚሰጡ በሰፊው ማብራሪያ በመስጠት ማብራራት፣ ተማሪዎች በቡድን ውይይት በመሳተፍ የእያንዳንዱን ንጥረ ምግብ መገኛ ምንጭ በዝዝር እዲያስቀምጡ ማበረታታት

| ተ.ቁ | ንጥረ ምግብ | የንጥረ ምግብ ጥቅም | የንጥረ ምግብ ምንጭ |
|---|---|---|---|
| 1. | ካርቦኃይድሬት | ኃይል መስጠት<br>ሙቀት መስጠት | ዳቦ፣ ፓስታ፣ ሩዝ ስንዴ ገብስ፣ በቆሎ ፣ ድንች፣ የተለያዩ አትክልት |
| 2. | ቅባት( ስብ) | ኃይል መስጠት<br>ሙቀት መስጠት | ወተት፣ ቅቤ፣ዓይብ፣ለውዝ፣ ዘይት፣ተልባ፣ሱፍ |
| 3. | ፕሮቲን (ገንቢ ምግብ) | ሰውነትን መገንባት ማሳደግ | ሥጋ፣ እንቁላል፣አተር፣ ባቄላ ፣ ቦሎቄ፣ ምሥር |
| 4. | ማዕድናት | ከበሽታ መከላከል፣ ሰውነት በአግባቡ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | እንዲሠራ ማድረግ | |
| 5. | ቫይታሚኖች | ከበሽታ መከላከል የሰውነት አካላት በትክክል እንዲሠሩ ማገዝ | |
| 6. | ውሃ | ሰውነታችን ምግብን በደም አማካይነት እንዲዘዋወር በትክክል እንዲሠራ ማድረግ | ንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ ከምንመገባቸው ምግቦች |

- በአካባቢያቸው የሚመረቱ የምግብ ዘሮች፣ አትክልት ፍራፍሬ እንዲዘረዝሩ በማድረግ በተለያዩ ንጥረ ምግብ እንዲመደቡ ማድረግ፣ የምግብ ዝርዝር በመስጠት የተመጣጠነ ምግብ ለቁርስ ምሳና እራት ለማዘጋጀት የሚያስችል ሰንጠረዥ እዲሠሩ ማድረግ (የተለያዩ የምግብ ጥሬ ዕቃዎችን በማቀላቀል)
- የምግብ ስርዓተ እንሽርሽሪት ውስጥ የሚታቀፉ የሰውነት ክፍሎችን እንዲዘረዝሩና ምግብ ከየትኛው የአካል ክፍል ተነስቶ በየትኛው አልፎ የት እንደሚደርስ እንዲወያዩ ማድረግ
- የምግብ እንሽርሽሪት ክፍሎችን በቅደም ተከተላቸው አስቀምጠው በስዕል እንዲያሳዩ ማድረግ፣ በአካባቢ ጥሬ ዕቃዎች በመጠቀም የምግብ እንሽሽሪት ስርዓት አካላትን ሞዴል እንዲሠሩ ማድረግ
- በምግብ ስርዓት እንሽርሽሪት ልሞ የደቀቀው ምግብ በትንሹ አንጀት ግድግዳ ውስጥ ከተቀመጠ በኋላ በደም ሥሮች አማካይነት ወደተለያዩ የሰውነት ክፍሎች እንደሚደርስና በዚህ ሂደት ውስጥ የደም፣ የደምስሮችና የልብ ሚና ምን እደሆነ እንዲያውቁ ለማድረግ ጠለቅ ያለ ገለፃ መስጠት። የደም ዝውውርን የሚያሳይ ስዕል እንዲስሉ ማድረግ።
- የልብን ምንነትና አሠራር ካስረዱ በኋላ ተማሪዎች በአካባቢያው ከሚገኙ ነገሮች የልብ ሞዴል እንዲሠሩ ማበረታታት

- ከደም ዝውውር ጋር በማያያዝ የአዴስ በሽታ የሚተላለፍላቸውን ዋና ዋና መንገዶች እንዲያውቁ ማድረግ (በደም ንክኪ፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት እና በእርግዝና ወቅት ከእናት ወደ ልጅ እንደሚተላለፍ)፣ የኤድስ መከላከያ ዘዴዎች (ንክኪን ማስወገድ፣ መታቀብ፣ የህክምና ርዳታ ማግኘት፣ ወዘተ) ላይ የቡድኑ ውይይት ማካሄድ፣ አቅራቢያቸው ወዳሉ የጤና ተቋማት በመሄድ ስለኤድስ ቃለ መጠይቅ በማድረግ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ
- ስለኤድስ በሽታ አስከፊነትና መደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ተማሪዎቹ በዝርዝር እንዲገልጹ ማድረግ፣
- ኤድስን በመከላከል ረገድ የህብረተሰብ ሚና በሚል ርዕስ በሁለት ተከፍለው ክርክር እንዲያካሂዱና ክርክሩን ተከትሎ አጠቃላይ ውይይት እዲያደርጉ መጋበዝ፣ ማበረታታት፣ ማሳተፍ፡፡
- ተማሪዎች በጉርምስና ወቅት በወንዶችና ሴቶች ልጆች ላይ የሚከሰቱ ለውጦች ምን እንደሆኑ ለማወቅ ትልልቅ ልጆችንና ትንንሽ ህፃናትን በማነፃፀር ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ፣ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ያታዊ ጥቃት በአካባቢያቸው ምን እንደሚመስልና ለሴቶች መደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ የሚና ጨዋታ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ማበረታታት።
- ተማሪዎች የቤተሰብ ምጣኔን ምንነት እንዲረዱና ጥቅሙ ምን እንደሆነ የቡድን ውይይት ውስጥ በመሳተፍ ግንዘቤ እንዲጨብጡ ማድረግ፣ የቤተሰብ ምጣኔን አለመጠቀም ምን ጉዳቶች ሊያስከትል እንደሚችል በትናንሽ ቡድኖች በመሆን ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ።

  **ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለክፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን።

## (10) ተፈጥሮአዊ አካባቢያችን (ደረጃ ሦስት)

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-** ውይይት፣ ምልከታ፣ ፕሮጀክት፣ ምደባ፣ የመስክ ምርምር፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥያቄና መልስ፣ የቃል ዘገባ፣ የፓናል ውይይት (በተጋባዥ እንግዳ)፣ ተግባራዊ ሥራ፣

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡-** የእጅ ባትሪ ቀፎ፣ አምፑል፣ ባትሪ ድንጋይ፣የኤልክትሪክ ሽቦ፣ ምስማር ፣ የወረቀት መርፌ፣ ሻማ፣

ለአመቻች ማስታወሻ

በዚህ ምዕራፍ የቀረበው ትምህርት ተማሪዎች የቁስ አካልን ምንነት እንዲያውቁና በእነሱ ላይ የሚታዩትን ለውጦች እንዲረዱ፣ የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ምንነት እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ በአካባቢ ላይ ሊያመጣ ስለሚችለው ተፅዕኖ፣ ለአየር ንበረት መልካም መሆን የዕፅዋት ሚና እና ዕፅዋትን ለመንከባከብ መደረግ ያለባቸውን ጥንቃቄዎች ያስገነዝባል፡፡ የውሃ ዑደት ለአካባቢ የሚያበረክተውን ጥቅም፣ የኃይል ምንነትና የተለያዩ የኃይል ምንጮችን አንድነትና ልዩነት በተለይም የኤሌክትሪክ ኃይልን አስመልክቶ ተግባራዊ ልምድ እንዲያዳብሩ የሚረዳ ነው፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት፡-**

- የቁስ አካል ምንነት ከተገለፀላቸው በኋላ ምሳሌዎቹን በቡድን ውይይት እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ ቁስ አካል፣ መጠነ ቁስ እንዳለውና የተለዩ ለውጦች ሊደረጉበት እንደሚችሉ፣ አንዳንድ የቁስ አካል ለውጦች ሊቀለበሱ እንደማይችሉ እና ሌሎቹ ግን ሊቀየሩ እንደሚችሉ የተለያዩ ሙከራዎችን በማድረግ እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነት ምን እንደሆነ እንዲረዱ ትምህርቱን በሚማሩበት ወቅት በየዕለቱ የሙቀት መጠን እንዲለኩ ፣ ዝናብ ይዘንብ እንደሆነ እንዲዘግቡ፣ ደመና ለስንት ቀናት እንደታየ እንዲመዘገቡ፣
- ይህ የአየር ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ይቆይ እንደሆነና እንዳልሆነ በየዕለቱ በሚያደርጉት ምልከታ እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- የአየር ንበረት በየጊዜው መቀየር በዕፅዋት ላይ በቀጥታና በተዘዋዋሪ እንዲሁ በእንስሳት ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ በውይይት ሀሳብ እንዲለዋወጡበት ማድረግ፣ የዝናብ መጠን መለኪያ የሚገኝ ከሆነ በየዕለቱና በየወራቱ የሚዘንበውን ዝናብ መጠን ለክተው ያገኙትን ውጤት እንዲመዘግቡ ከዚያም የየቀኑን አማካይ የዝናብ መጠን ካወጡ በኋላ የግራፍ ወረቀት በመጠቀም የዝናቡን መጠን በግራፍ ስለው እዲያሳዩ ማበረታታት፣የሠሩትን ግራፍ በመተንተን በየትኛው ወር የት/ቤታቸው አካባቢ ከባድ እንዲሁም ቀላል ዝናብ እንደሚያገኝ ለክፍል ጓደኞቻቸው መግለጫና ማብራሪያ እዲያደርጉ ዕድል መስጠት፡፡

- የውሃ ዑደትና የተፈጥሮ ሀብት (ዕፅዋት) ጥበቃ ዝምድናን እንዲገልጹ ማድረግ
- የመስክ ምልከታ በማድረግ በጉበኙት አካባቢ የሚገኙትን ዕፅዋት ዛፍ፣ችፍርግ፣ በማለት እንዲመድቡ ማድረግ፣ የዕፅተዋትን አስፈላጊነት በጥልቀት ዘርዝረው እንዲያብራሩ ማድረግ
- ዕፅዋትን ለመጠበቅና አካባቢ እንዳይራቆት ለማድረግ ይረዳ ዘንድ በት/ቤታቸው አካባቢ የዛፍ ችግኝ ተከላ እንዲያካሄዱ ማበረታታት፣ በችግኝ አፈላል ሥራ ማሳተፍ
- የዛፎችን ጠቀሜታ በማስመልከት የአካባቢውን የግብረና ባለሙያ ወደ ክፍል በመጋበዝ ገለፃ እንዲያደርጉ ማድረግ
- የጉልበት ምንነት ከተገለፀላቸው በኋላ በቡድን ውይይት የጉልበትን ምንጭ እንዲያብራሩ ከተለያየ ምንጭ የሚገኘውም ጉልበት ለምን ጥቅም ሊውል እንደሚችል ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማበረታታት
- ኤሌክትሪክ አንዱ የጉልበት ዓይነት መሆኑን ተረድተው የኤሌክትሪክ ምንጭን አስመልክተው ውይይትና ሙከራ እንዲያካሄዱ ማድረግ፣ የኤሌክትሮ ማግኔቱስ ምንነትና ጥቅም እንዲያብራሩ ማበረታታት
- የአካባቢ ጥበቃን ዕውን ከማድረግ አንፃር አማራጭ የኃይል ምንጮችን የመጠቀም ዝንባሌ እንዲያዳብሩ፣ በቤተሰባቸውና በአካባቢያቸው ትምህርቱን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማበረታታት

  **ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለክፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን።

## (11) ሀገራችን (ደረጃ ሦስት)

**የማስተማር ዘዴ፡-** ምልከታ፣ ዘገባ፣ውይይት፣ ምደባ፣ ጥያቄና መልስ፣ሰርቶ ማሳያ፣ ገለፃ፣ ፕሮጀክት፣ ውስን ጥናት

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-** የኢትዮጵያ ካርታ፣የአፍሪካ ካርታ፣ ሉል(ግሎብ)፣ ሥዕሎች፣ ፖስተሮች፣ የግራፍወረቀት፣ ማረከር፣እርሳስ

ለአመቻቹ ማስታወሻ

በዚህ ምዕራፍ የቀረበው ትምህርት ተማሪዎች ስለሀገራቸው ኢትዮጵያ ጂኦግራፊያዊ መገኛ፣ የኢትዮጵያን አጎራባች ሀገሮች በሁሉም አቅጣጫ እንዲያውቁና የጎረቤት ሀገሮች በሰላም ተከባብሮ መኖር ለልማት ምን ያህል

ፋይዳ እንዳለው እንዲረዱ ለማድረግ የሚረዳ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የኢትዮጵያን ህዝብ ብዛት መረጃ እንዲያገኙ፣የህዝብ ብዛት በአካባቢና በአኗኗር ላይ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ የሚመረምሩበትና ተፅዕኖውን ለማቃለል የሚቻልባቸውን ርምጃዎች ለመውሰድ የሚያስችል ዕውቀት፣ ልምድና ክህሎት የሚያዳብሩበት ነው፡፡ የሀገሪቱን ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በመዳሰስ ትራንስፖርትና ቴክኖሎጂ በተለይም የግንኙት ቴክኖሎጂ መስፋፋት ለኢኮኖሚ ዕድገት የላቸውን ፋይዳ ለይተው እንዲያውቁ፣ የራሳቸውንም ድርሻ እንዲያበረክቱ ለማድረግ ይረዳል፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት፡-**

- ተማሪዎች ሀገር ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በውይይት ግንዛቤያቸውን እንዲያዳብሩ፣ ሀገርና ህዝብ ምን ግንኙነት እንዳላቸው ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ
- የኢትዮጵያን አቀማመጥ በአፍሪካ ካርታ ላይ ከተመለከቱ በኋላ የጎረቤት ሀገሮችን ጨምረው የኢትዮጵያን ካርታ በደብተራቸው ላይ እንዲስሉ ማድረግ፣ በአራቱም አቅጣጫ ያሉትን የጎረቤት ሀገሮች ዝርዝር በወረቀት ላይ እንዲፅፉና ለጓደኞቻቸው እንዲያስረዱ ማድረግ
- የኢትዮጵያ ካርታን ስለው የተለያዩ መልክዓ ምድሮችን (ወንዞች፣ ተራሮች፣ ሀይቆች) የሚገኙባቸውን ቦታዎች በተለያዩ ቀለማት ማሳየትና ስም ዝርዝራቸውን ማመልከት እንዲችሉ ዕድል መስጠት
- ከእነዚህ መልክዓ ምድሮች ውስጥ የተወሰነውን በግል አይተው ከሆነ ለሌሎች የክፍል ጓደኞቻቸው የሚያውቁትን እንዲያስረዱ ማበረታታት።
- **ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለክፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን።

## (12) ማህበራዊ አካባቢያችን (ደረጃ ሦስት)

**የማስተማር ዘዴ፡-** ምልከታ፣ ዘገባ፣ውይይት፣ ምደባ፣ ጥያቄና መልስ፣ሰርቶ ማሳያ፣ ገለፃ፣ ፕሮጀክት፣ ውስን ጥናት

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-** የኢትዮጵያ ካርታ፣የአፍሪካ ካርታ፣ ሉል(ግሎብ)፣ ሥዕሎች፣ ፖስተሮች፣ የግራፍወረቀት፣ ማረከር፣እርሳስ

ለአመቻቹ ማስታወሻ

በዚህ ምዕራፍ የቀረበው ትምህርት ተማሪዎች ስለኢትዮጵያ ህዝቦች ቋንቋ፣ ባህል፣ልማድና ወግ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ፣ እንዲያደንቁ፣ የባህል ቅርሶችን እንዲንከባከቡ፣ ጠቃሚ የሆኑ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዲያሳድጉና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዲያስወግዱ ለማድረግ የሚያስችል ሲሆን፣ የሀገሪቱን ታሪካዊ ቅርሶች ምንነትና ጥቅም በመረዳት ለቅርሶች እንክብካቤ በግልና በቡድን ማድረግ የሚገባቸውን ጉዳይ እንዲገነዘቡ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰለኢትዮጵያ የተለያዩ አርበኞችና ስላበረከቱት ውጤት (በስፖርት፣ ሙዚቃ፣ ስነፅሑፍ፣ በልማት ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በሀገር መከላከል፣ ወዘተ) እንዲያደንቁና የእነርሱን ምሳሌ ለመከተል እንዲያነሳሱ የሚያደርግ ሲሆን፣ የመልካም አስተዳደርን ምንነት በመረዳት በወደፊት ህይወታቸውና በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ውስጥ ፍትሀዊነትን፣ እኩልነትን፣ ታማኝነትን፣ እውነተኝነትን፣ ህግና ደንብ አክባሪነትን፣ ሰብአዊነትን፣ አለማዳላትን፣ በሰላም ተግባብተው መኖርን ችግሮችን በውይይት የመፍታት ዲሞክራዊያዊ አሠራርን እንዲለማመዱ ከሌሎች ጋር ያላቸውን የሚኖራቸውን የግኙነት ክህሎችን የሚያዳብሩበት ትምህርት ነው፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ ሂደት፡-**

- የተለያዩ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቅርሶች (የአክሱም ሀውልት፣ የሶፍዑመር ዋሻ፣ የላሊበላ ውቅር አብያተክርስቲያን፣ የጎንደር ቤተመንግሥት፣የሀረር ግንብ ጢያ ትክል ድንጋዮች፣ የሰሜን ተራሮች፣ የተለያዩ ብሔራዊ ፓርኮች፣ ወዘተ) በሥዕሎች በመጠቀም ውይይት እንዲያደርጉ ማበረታታት ፣ በአካባቢያቸው የሚገኝ ቅርስ ካለ በቦታው ተገኝተው የመስክ ጉብኝት እንዲያደርጉና ያዩትን ነገር በመመዝገብ በክፍል ውስጥ የቃልና የፅሁፍ ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ፤
- ተማሪዎች ባህል ምን ማለት እንደሆነ እንዲያውቁ ለማስቻል ማብራሪያዎችን በገለፃ መልክ ካቀረቡ በኋላ በምን በምን ነገሮች እንደሚገለፅ (ቋንቋ፣ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ሙዚቃና ጭፈራ፣ የጋብቻ ስነ ሥርዓት ፣ የዘመን አቆጣጠር፣ የሀዘን የደስታ አገላለፅ፣ የችግር አፈታት ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ወዘተ) በግል እንዲዘረዝሩ፣ ከዚያም በሁለት በሁለት፣ ቀጥሎም በአራት አራት ተገናኝተው ከተመካከሩ በኋላ የተግባቡባቸውን ነገሮች በፅሁፍ አጠናክረው በቡድን ተወካይ አማካይነት ለክፍሉ

ተማሪዎች በሙሉ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ፣ የቡድኑም አባላት ተጨማሪ ሀሳቦችን እንዲያክሉ ማድረግ፣ የቡድን ዘገባውን ተከትሎ የክፍሉ አጠቃላይ ውይይት እንዲቀጥል መገፋፋት፣ መርዳት

- በኢትዮጵያ የሚገኙ የቋንቋ ቤተሰቦችን (ሴሜቲክ፣ ኦምቲክ፣ ኩሽቲክ፣ ኒሎ ሳህራው) ማብራሪያ በመስጠት ተማሪዎች በትናንሽ ቡድኖች ሆነው በእያንዳንዱ የቋንቋ ቤተሰብ ሥር የሚመደቡ ሁለት ሁለት ሥራዎቻቸውን ተለዋውጠው እንዲገመግሙ ማድረግ፣ ከዚያም በኋላ አጠቃላይ የክፍል ውይይት ማድረግ
- ተማሪዎች ለብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዎች አክብሮት እንዲኖራቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲወያዩ፣ አንድ ቋንቋ የሚናገር ህዝብ መካከል የማይችል ሰው ቢያጋጥማቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሰፊ ውይይትና ክርክር እንዲያደርጉ ማደፋፈር
- በአካባቢያቸው የሚዘወተሩ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች( ግግ ማስነቀል፣እንጥል ማስቆረጥ፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ጠለፋ፣ ሴት ልጅን ያለራስዋ ፍላጎትና ውሳኔ ማጋባት) እንዲዘረዝሩ ማድረግና የጉዳታቸውን ምንነት በማስመልከት የሚና ጨዋታ ሰርተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ማነሳሳት፣ ማበረታታት
- ስለጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች ከአካባቢያቸው ታላላቅ ሰዎች ጋር ቃለ መጠየቅ አድርገው ውጤቱን በፅሁፍና በቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ መመደብ
- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙና ጠቃሚ ስለሆነ ልማዳዊ ድርጊቶች በመወያየት (ለምሳሌ፣ ባህላዊ ህክምና ፣ ባህላዊ የግጭት አወጋገድ፣ ወዘተ) ዘርዝረው እንዲያስቀምጡ በማድረግ የእያንዳንዱን ጠቃሚ ባህላዊ ድርጊት ጥንካሬና ድክመት እንዲገመግሙና ድክመቶቹን ለማሻሻል ምን ማድረግ እንዳለበት በክርክር መልክ እንዲያሳዩ ማበረታታት
- ተማሪዎች በሀገራቸው ኢትዮጵያ በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው አስተዋጽኦ ያበረከቱት አርበኞችን ስም ዝርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ እንዲዘረዝሩ ማድረግ።

| የሥራ መስኮች ዝርዝር | የአርበኞች ዝርዝር | የአርበኛው አጭር ታሪካዊ መግለጫ |
|---|---|---|
| ሙዚቃ | | |
| ስፖርት<br>• እግር ኳስ<br>• መረብ ኳስ<br>• ቅርጫት ኳስ<br>• አትሌቲክስ (ሩጫ) | | |
| ሥነ ፅሑፍ | | |
| ግብርና | | |
| ንግድ | | |
| ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ | | |
| ሀገርን መከላከል | | |
| የአካባቢ እንክብካቤ | | |

- ከላይ ከዘረዘሯቸው አርበኞች መካከል የትኞቹን እንደሚያደንቁ ከግላቸው አስተያየት ጋር እንደገልጹ በማድረግ ስለሚያደንቋቸው አርበኞች ፅፈው ለጓደኞቻቸው በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ማድረግ
- በማህበረሰብ ውስጥ ስለሚዘወተሩ የግንኙነት ዓይነቶችና በእያንዳንዱ ግንኙነት መከተል የሚገባቸውን አሠራሮችና ማሳየት የሚገባቸውን ባህርያት ለይተው

እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ ማህበራዊ እሴቶችንና መገለጫዎቻቸውን እንዲያስረዱ፣ የመልካም አስተዳደርን ምንነት እና መገለጫዎችን በተለያዩ የመንግስ መሥሪያ ቤቶች በማከፋፈል እንዲናገሩ ማድረግ፤

- በትምህርት ቤታቸው መልካም አስተዳደር ምን እንደሚመስልና የመልካም አስተዳደር እጦት ምን ሊያስከትል እንደሚችል በክርክር መልክ እንዲያቀርቡ ማበረታታት።

**ግምገማ**፡- በተቀመጠው ዓላማ መሠረት የተለያዩ ጥያቄዎችን ለከፍል ሥራና ለአጠቃላይ ፈተና እንዲሁም የተለያዩ መልመጃዎችን ለቤት ሥራ በመስጠት ብቃታቸውን መመዘን።

## 3.1.4 <u>የሂሣብ ትምህርት ማመቻቸት</u>

### (1) ከ1- 20 ያሉ የመቁጠሪያ ቁጥሮች (ደረጃ አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ከ1-20 ያሉ የመቁጠሪያ ቁጥሮችን ለይተው እንዲቆጥሩ ያደርጋሉ፤
- ከ1-20 ያሉ የመቁጠሪያ ቁጥሮችን በአሀዞች እንዲፅፉ ያበረታታሉ፡፡
- ከ1-20 ያሉ የመቁጠሪያ ቁጥሮችን " <" እና " >" በመጠቀም እንዲያወዳድሩ እገዛ ያደርጋሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻቹ/ቿ ተቆጣሪ ነገሮችን በመስጠት ተማሪዎች እንዲቆጥሩና መጠናቸውን እንዲገልጹ ማድረግ፤
- የቁጥር ሰሌዳ ወይም የቁጥር ካርዶችን በማዘጋጀት ለተማሪዎች መስጠትና ተማሪዎቹ " ቀዳማይ" እና" ተከታይ" የተባሉ ሀሳቦችን እንዲጠቀሙባቸው ማዘዝ፤
- የተቆጣሪ ነገሮችን ስብስባችን የአባላት ብዛት "<" , "=" እና ">" ምልክቶችን በመጠቀም ማነፃፀር እንዲችሉ ምሳሌ መስጠትና በቡድን ከፍሎ ማሠራት፤
- ቀላል መደመርና መቀነስ (ከ9 የማይበልጡ ቁጥሮችን ተጠቅሞ) ማሳየትና ተማሪዎች እንዲሠሩ ማድረግ፤

**የምዘናና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

- ከ1-20 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸው እንዲናገሩ ማድረግ

- ከ9 የማይበልጥ የሦስት መቁጠሪያ ቁጥሮችን ድምር እንዲያሰሉ የተለያዩ ጥያቄዎችን መስጠት

## (2) መደመርና መቀነስ እስከ 20 ባሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች ( ደረጃ አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ከ1-20 ያሉ የመቁጠሪያ ቁጥሮችን እንዲደምሩ ያበረታታሉ፡፡
- በመደመርና መቀነስ ላይ የዜሮን ባህርይ እንዲለዩ ያደርጋሉ፡፡
- ሶስት ቁጥሮችን እንዲደምሩ እገዛ ያሰጣሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻቹ/ቿ ብዛታቸው ከ20 የማይበልጡ የተለያዩ ሁለት ስብስቦች በመስጠት ተማሪዎቹ እንዲቀላቅሏቸውና ቆጥረው ውጤቱን እንዲናገሩ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡
- ቁጥራቸው ከ20 ያልበለጠ ስብስቦች በመስጠት ከላያቸው የተወሰኑትን እንዲያነሱና ቀሪውን እንዲቆጥሩ ማድረግ፤
- መደመር፣ መቀነስ ተደማሪ፣ ተቀናሽ የመሣሰሉት ቃላት በአግባቡ እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡

ምሳሌ፡- 8+9= 17
ተደማሪ ማነው?
9-7= 2
ተቀናሽ ማነው?
ዋና ቁጥር ማነው?

**የምዘናና የግምገማ ዘዴዎች፡-**

- ከ1-20 ባሉ ቁጥሮችን የመደመርና የመቀነስ ጥያቄዎችን መጠየቅና በትክክል መሥራታቸውን ማረጋገጥ፡
- በመደመርና በመቀነስ ላይ የዜሮን ባህርይ መጠየቅ
    - ምሳሌ፡- 5+0= ------
      9-0= -----

## (3) ማባዛትና ማካፈል እስከ 20 ባሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች (ደረጃ ሁለት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- የማባዛትና የማካፈልን ምልክት ለይተው መጠቀማቸውን ያረጋግጣሉ

- ውጤታቸው እስከ 20 የሆኑትን የማብዛት ፕሮብሎች እንዲከውኑ ያበረታታሉ፤

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻቹ/ቿ ለተማሪዎቹ በቂ ምሳሌ ከሰጠ/ች በኋላ አንድ አይነት ድማሪዎችን በመስጠት ደምረው ውጤታቸውን እንዲፅፉ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡

  ምሳሌ፡- 2+2+2= 6

- የማብዛት ምልክት "x" አጠቃቀሙን ማሳየትና እንዲፅፉ ማድረግ ፣ ቦታ እየቀያየሩ ሲያሰሉ ውጤታቸው አንድ መሆኑን ማሳየት፣

  4x2x2= 16

  2x4x2= 16

  2x2x4= 16

- የማካፈልን ምልክት እንዲያውቁና እንዲፅፉ ማድረግ
- እስከ 20 የሚደርስ አባላት ያሏቸውን ስብስቦች በመስጠት ሁለት እኩል ቦታ እንዲያካፍሉ ማድረግ፣

**የምዘናና የግምገማ ዘዴዎች፡-**

- የማካፈልን ምልክት መለየታቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ፤
- " ተከፋይ"፣ " አካፋይ" ፣ ድርሻ የተባሉትን ሀሳቦች መለየታቸውን መጠየቅ
- የማብዛትና የማካፈልን ዝምድና በራሳቸው አባባል እንዲገልጹ መጠየቅ፤

## (4) ሙሉ ቁጥሮች ከ0-100 እና ቅደመ ተከተላቸው (ደረጃ አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ከ0-100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቤት ዋጋቸው እንዲለዩ ያደርጋሉ፡፡
- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ ይደግፋሉ፡፡
- በ10 ብዜቶች አራቱን ስሌቶች እንዲያሰሉ ያሰያሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻቹ/ቿ አሥር አሥር አባላት ያላቸውን ስብስቦች አዘጋጅቶ/አዘጋጅታ ለተማሪዎቹ ከሠጠ/ች በኋላ እያንዳንዳቸውን እንዲቀላቅሉ በማድረግ 2 አሥሮች ፣ 3 አሥሮች፣4 አሥሮች ወዘተ እያሉ ይህንንም ወደ ማባዛት እንዴት እንደሚቀይሩት እንዲያሳዩ ማገዝ፤

- የ10 ብዜቶችን እንዲያወዳድሩ ማስቻል፤

  ምሳሌ፡- 40>30
  30<40
  30=30

- ሀገኛ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እያሉ እንዲጠሩ ፣ እንዲያነቡና እንዲጽፉ ማድረግ

**የምዘናና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

- እስከ 100 ባሉ ቁጥሮች ቀዳሚና ተከታይ እንዲሰጡ መጠየቅ

  ምሳሌ፡- የ 80 ቀዳሚ ማነው?
  የ80 ተከታይ ማነው?

- ከበደ 60 ደብተሮች አሉት ፡፡ ለ5 ተማሪዎች እኩል ቢያካፍል ስንት ስንት ደብተሮች ይደርሳቸዋል?

## (5) መደመርና መቀነስ እስከ 100 (ደረጃ አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማዎች**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡-

- እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች አለኝታንና መበደርን የማያስከትሉ መደመርና መቀነስን እንዲያሰሉ ያበረታታሉ፤
- እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መደመርና መቀነስን የሚጠቀሙ የቃላት ፕሮብሌሞችን እነዲፈቱ ያስችላለሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻቹ/ቿ በርካታ ምሳሌዎችን በማቅረብ ባለሁለት ሆሄ ቁጥሮችን በመውሰድ ድማሪዎቹ በአንድ የ10 ብዜት ክልል በማድረግ መደመርን እንዲለማመዱ ያደረጋል/ታደርጋለች፡፡

  ምሳሌ፡- 31+34=65
  32+35=67
  43+44=77
  36-33= 3
  48-46=2

- በይበልጣል ፣ ያንሣል፣ በእኩልነት ዐረፍተ ነገሮች ላይ ተመስርተው ፕሮብሌሞችን እንዲሰሩ ማሳየት፤

ምሳሌ፡-

4<6= 4+2

4<5= 4+1

**የምዘናና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

- እስከ 100 ባሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች የመደመርና የመቀነስ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መሥራታቸውን መመልከት፤
- የማወዳደሪያ ምልክቶችን( ">" ፣"<"፣ "=") በመጠቀም የተሰጡ ፕሮብሌሞችን እንዲፈቱ ማድረግ፤

## (6) ክፍልፋዮች (ደረጃ ሁለት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የተሰጠን ነገር በግማሽ ስለው እንዲያሳዩ ያደርጋሉ
- የተሰጠን ሙሉ ነገር በሩብ ስለው እንዲያሳዩ ያደርጋሉ፡፡
- የግማሽንና የሩብን ግንኙነት እንዲረዱ በምሳሌ ያሳያሉ፡፡
- የተሰጠን ሙሉ ነገር አንድ ሶስተኛ (ሲሶ) በስዕል እነዲያሳዩ ያደርጋሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻቹ/ቿ በቂ ምሳሌዎችን ካሳየ/ች በኋላ ሙሉ ነገሮችን (ለምሳሌ ወረቀት፣ ብርቱካን) በመጠቀም ግማሽንና ሩብን የሚያሳዩ ስዕሎች ተማሪዎቹ እንዲስሉ ማድረግ፤
- ተማሪዎች የግማሽ (½ )፣ የሩብን( ¼) ፣የአንድ ሶስተኛን (1/3 )እና የሁለት ሶስተኛን (2/3 )አፃፃፍ እንዲለዩ ማድረግ፤

**የምዘናና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

- ተማሪዎች የክብን ሩብ፣ ግማሽ፣ሁለት ሩቦች፣ ሶስት ሩቦች እንዲስሉና እንዲቀቡ ማድረግ፣
- አንድ ብርቱካን ሶስት እኩል ቦታ ቢከፋፍል ለእያንዳንዱ ምን ያህል ይደርሳል?

## (7) መስፈሪያ መደቦች (ደረጃ ሁለት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ሜትርና ሳንቲሜትር የርዝመት መስፈሪያ መሆናቸውን እንዲያውቁ ያደርጋሉ
- የብርና ሳንቲሞችን ዝምድና እንዲለዩ ያበረታታሉ፡፡
- ጊዜን እነዲሰፍሩ ያበቃሉ፡፡
- በደቂቃና በሰዓት መካከል ያለውን ዝምድና እንዲገነዘቡ ያደርጋሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻቹ/ቿ ማስመሪያና ሜትር ይዞ/ይዛ በመምጣት ተማሪዎቹ የጠረጴዛቸውን፣ የደብተራቸውን ጠርዝ ወዘተ እንዲለኩ ማድረግ ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡
- የኢትዮጵያ ሣንቲሞችንና የብር ኖቶችን ማሳየትና በትክክል እንዲለዩ ማድረግ፣
- የተለያዩ የጊዜ መሥፈሪያ ስልቶችን ማለትም ደቂቃ፣ሰዓት፣ቀን ሳምንት እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣

  ምሳሌ፡-በአንድ ሰዓት ውስጥ ስንት ደቂቃዎች ይገኛሉ?
  በአንድ ደቂቃ ውስጥ ስንት ሰኮንዶች ይገኛሉ?
  በአንድ ሳንቲም፣በአምስት ሳንቲም፣በአሥር ሳንቲም፣በሀምሳ ሳንቲምና በአንድ ብር መካከል ያለውን ግንኙነት ማስረዳትና እንዲገልጹ ማድረግ፤

- የሊትር፣የኪሎግራም ሀሳቦችን ማስረዳት፣

**የምዘናና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

- የርዝመት መለኪያዎችን እንዲገልጹ ማድረግ፣
- የብር ኖት በመሳየት ወደ ሣንቲም እንዲቀይሩ መጠየቅ፤
- የጊዜ መስፈረያ መደቦችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፤
- የፈሳሽ ነገሮች መለኪያ ምን እንደሆነ መጠየቅ፤
- የተለያዩ መጠነ ቁሶችን እንዲደምሩና እንዲቀንሱ መጠየቅ፤

## (8) ሙሉ ቁጥሮች ከ101 - 1000 (ደረጃ ሁለት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ከ101-1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ማበረታታት፡፡
- እስከ 1000 ያሉትን የ10ን እና የ100ን ብዜቶች እንዲደምሩ ያደርጋሉ፤
- እስከ 1000 ባለሙሉ ቁጥሮች መደመርንና መቀነስን የሚያስከትሉ የቃላት ፕሮብሌሞችን እንዲፈቱ ያበረታታሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻቹ/ቿ ከ101 እስከ 1000 ያሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቁጥር ጨረር መስመር ላይ ካስቀመጠ/ች በኋላ ተማሪዎች ቀደማይና ተከታይ ቁጥሮችን እንዲያሳዩ መጠየቅ፤
- ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል ባለሶስት ሆሄያት ሙሉ ቁጥሮች በመጠቀም ቀዳሚና ተከታይ ቁጥሮች እንዲያስቀምጡ ማድረግ፤
- መሠረታዊ የመደመርና የመቀነስ ፕሮብሌሞችን በመጠቀም ባለሶስት ቁጥሮች ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስን ማሳየትና ማሠራት፤
- ባለሶስት ቁጥሮች ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና ማቀናነስ ማሳየት

  ምሳሌ፡- 400+200 = 600

  800-300 =500

**ምዘናና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

- ከ0-1000 ያሉትን የ10 ብዜቶችና የ100 ብዜቶችን በቃላትና በጽሁፍ መጠየቅ፤
- ባለሶስት ሆሄያት ቁጥሮችን የመደመርና የማቀናነስ ፕሮብሌሞች መስጠትና ሥራቸውን መከታተል፡፡

## (9) መስፈሪያ መደቦች (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ነጥብ፣ ውስን ቀጥታ መስመር፣ ጎነ ሦስት፣ ጎን አራት የተባሉትን ጽንስ ሀሳቦች እነዲረዱ የበረታታሉ፡፡
- የውስን ቀጥታ መስመሮችን ርዝመት እንዲለከ ያደርጋሉ፡፡
- ክብን፣ጎነ ሶስትን፣ጎነ አራት የምስል ቅርጽ ያላቸውን ቁሳቁሶች በአካካቢያቸው ውስጥ እንዲለያ ያደርጋል፡፡


**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አመቻቹ/ቿ ስለቀጥታ መስመሮች፣ ስለተቋራጭ ቀጥታ መስመሮችና ስለነጥብ ተማሪዎችን ያስረዳል/ታስረዳለች፡፡
- ጎነ ሶስትን፣ ጎነ አራትን ወረቀት እየቆራረጡ መሥራት እንዲችሉ ማገዝ ፤
- ውስን ቀጥታ መስመሮችን ማሰማሪያ በመጠቀም እንዲልኩና እንዲያወዳድሩ ማድረግ፤
- የኢትዮጵያ ሣንቲሞችንና የብር ኖቶችን ማሳየትና በትክክል እንዲለዩ ማድረግ፣
- ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል 1ኛው ቡድን ጎነ ሶስትን፤ 2ኛው ቡድን ጎነ አራትን ፣ 3ኛው ቡድን ውስን ቀጥታ መስመርን ፣ 4ኛው ቡድን ክብን በመሣል ከየቡድኑ ደግሞ አንድ ሰው ተነስቶ ለሌሎች የክፍሉ ተማሪዎች እንዲያሳይና ስለስዕሉ እንዲናገር ማድረግ፡፡

### የምዘናና ግምገማ ዘዴዎች፡-

- የጎኑ ሶስትና ጎነ አራት ፅንስ ሀሳቦችን እንዲለዩ መጠየቅ፣
- ውስን መስመሮችን መለየታቸውን የተለያዩ ምስሎችን በመስራት መጠየቅ

ይህ ስዕል ባለስንት ጎንን ያሳያል?




## (10) መረጃ አያያዝና ፖተርኖች (ደረጃ ሁለት)

### የትምህርቱ ዓላማዎች


አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፣

- ቀለል ያሉ መረጃዎችን ሰብሰብው መመዝገብ እንዲችሉ ያደርጋሉ፡፡
- መረጃን ከቀላል ስዕላዊ መግለጫዎች ላይ እንዲያነቡ እገዛ ያደርጉላቸውል፡፡
- ቀለል ያሉ የቅርጽና የቁጥር ፖተርኖችን እንዲለዩ በማድረግ፣ ያልተሟሉ ሲሰጧቸው ማሟላት እንዲችሉ ያደግፋሉ፡፡

### የትምህርቱ አቀራረብ፡-

- አመቻቹ/ቿ ተማሪዎችን በቡድ በመክፈል የቡድኑ አባላት የየራሳቸውን ቁመት ሜትር በመጠቀም እንዲለኩና በሰንጠረዥ እንዲያደራጁ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡
- ተማሪዎች የተጀመሩ ፖተርኖችን እንዲቀጥሉባቸው ማድረግ

ለምሳሌ ሀ) 2፣00፣2፣00፣2፣00፣……..

ለ)  ---

### የምዘናና ግምገማ ዘዴዎች፡-

- ተማሪዎች ቀለል ያሉ መረጃዎችን ከት/ቤት አካባቢ በሰንጠረዥ እንዲያደራጁ መጠየቅ።

## (11) ማባዛትና ማካፈል እስከ 100 (ደረጃ ሁለት)

### የትምህርቱ ዓላማዎች፡-

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡-

- በማባዛትና በማካፈል መካከል ያለውን ልዩነትና ግንኙነት እንዲብራሩ የደርጋሉ፡፡
- መሠረታዊ የማባዛትና የማካፈል ፕሮብሌሞችን እንዲፈቱ ያበረታታሉ

- የማባዛትና የማካፈል ባህሪያት እንዲዘረዝሩ ያግዛሉ

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- የሚቆጠሩ ነገሮች በማደራጀት መስጠት
- ማባዛት በመደመር ማስተማር
- ለምሳሌ፡-( 3x4= 4+4+4 መሆኑን ማሳየት )
- ማባዛትና ማካፈልን በስብሰባ ማስረዳት

**የግምገማ ዘዴዎች፡-**

- ለተማሪዎች የክፍል ስራ በመስጠት መመልከት
- የቤት ሥራ ሰጥቶ ማረም
- የቃላት ፕሮብሌሞች በመጠቀም እንዲለማመዱ ማድረግ

## (12) ሙሉ ቁጥሮች እስከ 10,000 ( ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡-

- እስከ10,000 ያሉ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ እገዛ ያደርጋሉ፤
- እስከ10,000 ያሉ ቁጥሮችን ለይተው እንዲጽፉ ያደርጋሉ፤
- እስከ10,000 ያሉትን የ10 ብዜት እንዲደምሩና እንዲቀንሱ ያበረታታሉ
- ለቁጥሮች አቅራቢ ዋጋ እንዲሰጠ ያግዛሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

ለአመቻች ማስታወሻ


(1) በመቁጠር በስብስቡ ስንት ነገሮች እንዳሉ ይነገራል፡፡
(2) ጥሩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ከቁጥሮቹ አይነትና ከሁኔታዎች ጋር የሚቀያየር ነው
(3) ጥሩ የማስተማሪያ ዘዴ መምረጥ ይዘትን በተገቢው ሁኔታ መርዳትን ይጠይቃል፡
(4) ተማሪዎች ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ መቻል አለባቸው
(5) ሙሉ ቁጥሮች ማለት 0 እና መቁጠሪያ ቁጥሮችን የሚያካትት የቁጥሮች ስብስብ ነው፡፡
ምሳሌ፣ 0,1,2,3,4,5,….

በዚህ እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል፡፡

1. ቁጥሮችን በቅደም ተከተል እንዲቆጥሩ ማድረግ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 10 | 20 | 30 | 40 | 50 |
| 100 | 200 | 300 | 400 | 500 |
| 1000 | 2000 | 2000 | 4000 | 4000 |

2. ተማሪዎች ቁጥሮችን እንዲፅፉ ማድረግ
   ( በቅደም ተከተልና ከትልቅ ወደ ትንሽ)
3. ተማሪዎች ቁጥሮችን እንዲያወዳድሩ መጠየቅ፤
4. ተማሪዎች ቁጥሮችን ከፊት ወይ ከኋላ እያሉ እንዲለዩ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ 900 ከ1,000 በስንት 10 ከፊት ነው 900 ከ800 በስንት 10 ከኃላ ነው፡፡
5. አባከስ በመጠቀም በ10 ብዛት በመመደብ ቁጥሮችን ማስተማር ይቻላል፡፡
   ለምሳሌ-



3 የመቶ ፣ 8 የአስር እና 3 የአንድ

**የምዘናና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

1. ተማሪዎች ቁጥሮችን በቅደም ተከተል እንዲፅፉ
   ለምሳሌ፡- ከ121 እስከ 200 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ፃፉ
2. ተማሪዎች ከትልቅ ወደ ትንሽ ወይም ከትንሽ ወደ ትልቅ እንዲያስቀምጡ መጠየቅ፡፡
   ለምሳሌ፡- ከ121 እስከ 200 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ፃፉ
3. ተማሪዎች ቁጥሮችን እንዲያወዳድሩ መጠየቅ

ለምሳሌ 91----- 19

218----812

520---502

## (13) መደመርና መቀነስ እስከ 10,000 (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፦**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡-

- እስከ10,000 ባሉ ቁጥሮች መደመርና መቀነስን በጽሑፍና በቃል እንዲያሰሉ ያደርጋሉ
- የመደመርና የመቀነስ ተመሳሳይነትንና ልዩነትን እንዲገነዘቡ ያግዛሉ፡ ፡

አመቻች ማስታወሻ

1. መጀመሪያ ልጆች አንድ አለኝ ወይም መደመር በሌለበት እንዲያሰሉ ማድረግ
2. የቃላት ፕሮብሌሞችን በመጠቀም ማለማመድ ተገቢ ነው፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- የመደመርና የመቀነስ ምሳሌዎችን መስራት
- የክፍል ስራ በመስጠት የመማር ሁኔታዎችን ማየት
- ተማሪዎች በየተራ እየወጡ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማድረግ
- የቤት ሥራና ከተማሪ መጽሐፍ መልመጃ በመስጠት ማጠናከር

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ፡**

- መልመጃ በመስጠት የተማሪዎችን ስራ መገምገም

## (14) ማባዛትና ማካፈል እስከ 10,000 ( ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፦**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- እስከ 10,000 ባሉ ቁጥሮች ማባዛትና ማካፈል እንዲያሰሉ ያደርጋሉ
- በተከፋይ፣ በአካፋይና በድርሻ መካከል ያለውን ዝምድና እንዲገልጹ ያበረታታሉ
- የጊዜ መስፈሪያዎችን ከአንዱ መደብ ወደ ሌላኛው እንዲለውጡ እገዛ ያደርጋሉ
- ማካፈልና ማባዛትን የሚያስከትሉ የቃላት ፕሮብሌሞችን እንዲፈቱ ያግዛሉ

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

(ሀ) ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ በመደመርና ማባዛት፣ በመቀነስና በማካፈል ያለውን ግንኙነት ላይ እንዲወያዩ ማድረግና እንደየሁኔታው ማገዝ፡፡

**ለምሳሌ**፡-3x 40= 40+40+40= 120

60÷10 ማለት ደግሞ

60-10= 50

50-10= 40

40-10=30

30-10=20

20-10=10

10-10= 0

ስለዚህ 60÷10=6 እንደመሆነ ማሳየትና በዚህ መሠረት በየቡድኑ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

በማካፈልና ማባዛት መካከል ያለውን ዝምድና በምሳሌ ማሳየት

ለምሳሌ 60÷10=6

10x6 = 60 በማለት ማስረዳት

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ፡-**

1. የክፍል ሥራ በመስጠት እየሰሩ ማገዝና ማረም
2. የቃላት ፕሮብሌሞችን በመስጠት ማረም
3. የቤት ስራ መስጠትና ማረም

## (15) ክፍልፋዮች (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ዩኒት ክፍልፋዮችን (ለምሳሌ ½ ,1/10 ) ስዕልን ወይም ቁሳቁስን በመጠቀም እንዲለዩ ያስችላሉ፡፡
- የተሰጠን የግማሽና የሩብ ብዜትን እንዲረዱ ያግዛሉ
- ዩኒት ክፍልፋዮችን እንዲያወደድሩ ያበረታታሉ

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- ቁሳቁስንና ምስሎችን በመጠቀም የክፍልፋይ ፅንሰ ሀሳብ ማስረዳት
- ከህይወት ልምዳቸው ጋር በማዛመድ ማሳየት

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ፡-**

- የክፍልና የቤት ስራ በመስጠት ማረም፡፡

## (16) መስፈሪያ መደቦች ( ደረጃ ሦስት)

**የትምህረቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- የጊዜ ፣ የርዝመት፣ የክብደትና የይዘት መለኪያዎች እንዲለዩ ያግዛሉ
- ከአንድ ይዘት መለኪያ ወደ ሌላ እንዲቀይሩ ያበረታታሉ፡፡

ለአመቻች ማስታሻ

- የባህላዊ የጊዜ፣ ርዝመት፣ ክብደትና ይዘት መስፈሪያዎችን ከተማሪዎች ጋር በመዘርዝር መወያየት
- ዘመናዊ የሚባሉትን በሌላ በኩል በመዘርዘር ተማሪዎች እንዲወያዩበትና በተግባር እየተገለገሉ እንዲያሳዩ ቢመቻች

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- ተማሪዎች ጊዜን ጠዋት፣ ከሰዓት፣ማታ ወዘተ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ለማወቅ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡
- በስንዝር፣ በክንድ ወዘተ የጠረጴዛ ርዝመት እንዲለኩ መጠየቅና ያለው ውስንነት እንዲናገሩ መጠየቅ፡፡
- በመቀጠል ሰዓት፣ ግራም፣ሜትርና ሊትር የምን የምን መስፈሪያዎች እንደሆኑ መግለፅ
- ምሳሌዎችን በመስጠት ማስረዳት፡፡

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ፡-**

- የክፍልና የቤት ሥራ በመስጠት መገምገምና ማገዝ፡፡

## (17) ጂኦሜትሪ (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ነጥብና መስመርን እንዲለዩ ያመቻቻሉ
- የምስሎችን ጎንና ጠርዝ እንዲናገሩ ያበረታታሉ

- ጥንድ ኮምፓሶችን በመጠቀም ክብ እንዲሰሩ ያግዛሉ
- የተለያዩ አውታሮችን እርዝመት እንዲያወዳሩ ያገዛሉ
- የፓራሌሎግራምና የሬክታንግል ቅርጾችን እንዲለዩ ያበቃሉ

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- ነጥብና መስመርን በመሳል ማሳየት
- የሬክታንግል፤ የክብና የሬክታንግላዊ ፕሪዝምን ምስሎች በመጠቀም ማስተማር

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ፦**

- ቅርጾችን እንዲለዩ መጠየቅ
- ቅርጾችን እንዲስሉ መጠየቅ
- የክፍልና የቤት ሥራ መስጠት

## (18) የመረጃ አያያዝ (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፦**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ቀለል ካሉ ግራፎች ላይ መረጃን እንዲያነቡ ያደርጋሉ፡፡
- ለተሰበሰቡ መረጃዎች በቀላል ግራፍእንዲሰሩ ያግዛሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- መረጃ ማለት ምን ማለት እንደሆነና ጥቅሙ ላይ መወያየት
- ቀላል የመረጃ ግራፍ በማሳየት ግንዛቤያቸውን መጠየቅ
- መረጃን በመስጠት ተማሪዎች በግራፍ እንዲያስቀምጡ መጠየቅ

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ**

- የተለያዩ መረጃዎች በመስጠት በግራፍ እንዲስሉ መጠየቅ በቡድን በመከፋፈል በግራፍ የተሰጠን መረጃ እንዲያነቡ ማድረግ

## (19) ሙሉ ቁጥሮች እስከ 1,000,000 (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፦**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ሙሉ ቁጥሮችን በቁጥር ዋጋ ቤት እንዲያስቀምጡ ያበረታታሉ፡
- እስከ 1,000,000 ያሉ ቁጥሮችን ቅደም ተከተል እንዲለዩ ያግዛሉ

- አቅራቢ ስሌት በመጠቀም የስሌቶችን አቅራቢ ዋጋ እንዲፈልጉ ያግዛሉ
- እስከ 1,000,000 ያሉ ቁጥሮችን እንዲያወዳድሩ ያበቃሉ

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- አባካስ በመጠቀም የቁጥር ዋጋ ቤት በመጠቀም ቁጥሮችን እንዲያነቡ ማገዝ
- የቁጥር መስመር በመጠቀም ቁጥሮችን እንዲያወዳድሩና መልመጃ እንዲሰሩ እገዛ ማድረግ
- ቢንጎ በመጠቀም ማለማመድ

  ለምሳሌ ፡- 1) ሶስት ካርዶችን ማዘጋጀት

| | | |
|---|---|---|
| 320 | 400 | 1001 |
| 304 | 201 | 567 |
| 4000 | 620 | 2001 |

| | | |
|---|---|---|
| 400 | 340 | 568 |
| 102 | 302 | 403 |
| 765 | 602 | 1001 |

| | | |
|---|---|---|
| 430 | 2001 | 211 |
| 567 | 400 | 2010 |
| 4000 | | 103 |

2) ለ3 ልጆች አንድ አንድ መስጠት
3) መምህር ወይም ሌላ ተማሪ የቁጥር ዝርዝር እንዲያነቡ ማድረግ
4) ቀድሞ በካርዱ ላይ ያሉ ቁጥሮችን ሰርዞ የጨረሰ ቢንጎ ይላል፣ አሸናፊም ይሆናል፡፡

ይህ ጨዋታ ልጆች የውድድር ስሜት በመያዝ እንዲለማመዱና ቁጥሮችን እንዲያነቡት ያግዛል፡፡

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ፡-**

- የቢንጎ ጨዋታውን ልጆች በየተራ እንዲጫወቱ በማድረግ ማገዝ
- የቁጥር ዝርዝር በመስጠት ከትንሹ ወደ ትልቁ ወይም ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል እንዲፅፉ ማድረግ
- ቁጥሮችን ለማወዳደር እንዲችሉ የክፍል ሥራ መስጠት

## (20) አራቱ መሠረታዊ ስሌቶች በሙሉ ቁጥሮች ላይ(ደረጃ ሦስት)

**የትምህሩ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- አራቱን መሰረታዊ ስሌቶች በሙሉ ቁጥሮች ላይ እንዲገለገሉባቸው ያስችላሉ፡፡

- አራቱ መሠረታዊ ስሌቶች የሚያስከትሉ የስሌት ፕሮግራሞችን እንዲፈቱ ያረዳሉ፡፡
- በገንዘብ፣ በርዝመት፣ በመጠን ቁስና በጊዜ መስፈሪያ መደቦች አራቱን መሠረታዊ ስሌቶች እንዲጠቀሙ ያግዛሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- በቂ ምሳሌዎችን በመጠቀም አራቱን መሰረታዊ ስሌቶች ማሳየት
- በአራቱም መሠረታዊ ስሌቶች መልመጃ በመስጠት ማለማመድ
- የቃላት ፕሮብሌሞች ወደ መሠረታዊ ስሌቶች መቀየርን ማሳየትና ማለማመድ

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ÷**

- የክፍል ሥራ በመስጠት ስራቸውን መከታተል
- በአራቱም መሰረታዊ ስሌቶች የቤት ሥራ መስጠትና ማረም

## (21) ክፍልፋዮች (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፦**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- አንድ አይነት ወይም ቆጣሪ ያላቸውን ክፍልፋዮች እንዲደምሩ፣ እንዲቀንሱ ያግዛሉ፡
- አስርዮችን እንዲደምሩ፣ እንዲቀንሱ ያግዛሉ፡፡
- ህገኛና ህገወጥ ክፍልፋዮችን እንዲለዩ ያበረታታሉ
- ክፍልፋዮችን በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ያግዛሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- የቁጥር መስመር በመጠቀም ክፍልፋዮችን ማስረዳት፣ ጥያቄ በመስጠት ማለማመድ፡፡
- ስዕላዊ መግለጫ በመጠቀም የክፍላፎች ግንዛቤያቸው እንዲባር ማሳየት፡

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ፡**

- የቤትና የክፍል ስራ መስጠት ማለማመድ፡፡

## (22) መስፈሪያ አሃዶች (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፦**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- የርዝመት፣ የጊዜ፣ ይዘትና መጠነ ቁስ መለኪያዎችና አሃዶችን እንዲለዩ ያደርጋሉ፡፡
- የተለያዩ የርዝመት፣ የይዘት፣ የጊዜና መጠነቁስ መለኪያዎችን እንዲጠቀሙ ያበረታታሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

ተማሪዎች የርዝመት፣ የመጠነቁስ፣ የይዘትና የጊዜ መለኪያዎች እንዲዘረዝሩ መጠየቅ

- ኪሎ ሜትርን ወደ ሜትርና ሳንቲሜትር፣ ኪሎግራምን ወደ ግራም፣ ሰዓትን ወደ ደቂቃ፣ ሊትርን ወደ ሚሊ ሊትር፣ የመቀየር ዘዴዎች በምሳሌ ማሳየት፣ እንዲለማመዱ ማድረግ

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ፡-**

- ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የክፍልና የቤት ስራ ማሰራት፣ ማረምና መልስ መስጠት፡፡

## (23) ክፍልፋዮች (ደረጃ ሦስት)

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን የትምህርት ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ ተማሪዎች፡

- ማዕዘናዊ አንግልን እንዲለዩ ያበረታታሉ ፡፡
- የቀጥታ መስመሮችን ግንኙነት እንዲገልጹ ያግዛሉ።
- የሬክታንግልን ዙሪያና ስፋት እንዲያሰሉ ያዘጋጃሉ፡፡
- የሬክታንግላዊ ፕሪዝምን ፣ የሲሊንደርን፣ የኮንና የፒራሚድ ቅርጽ እንዲለዩ ያበቃሉ፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ፡-**

- ሞዴል ሬክታንግላዊ ፕሪዝም፣ ስሊንደር፣ ኮንና ፕራሚድ በማዘጋጀት እንዲለዩ ማድረግ፤
- መዓዘናዊ አንግል በስእል ማሳየት
- የሬክታንግል ዙሪያና ስፋት ለማስላት ስእሎችን መጠቀምና መልመጃዎችን በመሥራት ማሳየት

**የምዘናና ግምገማ ዘዴ፡**

- የተለያዩ ቅርጾች (ፕሪዝም፣ሲሊንደር፣ኮንና ፒራሚድ) ያሏቸው ቁሶች እንዲለዩ መጠየቅ

- ፕሪዝም፣ ሲሊንደር፣ ኮንና ፒራሚድ እንዲስሉ መጠየቅ
- የሬክታንግል ዙሪያና ስፋት መደመርና ማባዛት በመጠቀም እንዲያሰሉ መጠየቅ፤

## ክፍል አራት

### 4. በክፍል ውስጥ ህፃናት ተማሪዎችን በማነቃቃትና በማትጋት የማመቻቸት ስልቶች ማስተማር፣

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች ይህንን ንዑስ ክፍል ካነበቡ በኋላ፡-

- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ክፍሎችን ለማመቻቸት የራሳቸውን ፈጠራ (creativity) ተጠቅመው ተጨማሪ የማትጊያና የማነቃቂያ ስልቶችን ለማመንጨት ጥረት ያደርጋሉ፡፡
- ህፃናት ተማሪዎች ተፈላጊውን ዕውቀት እንዲቀስሙ፣ ክህሎት እንዲያዳብሩና ጥሩ የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ የማትጋትና የማነቃቃት ስልቶችን ይጠቀማሉ፡፡


አመቻቾች የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተሳታፊ ህፃናት ተማሪዎችን ለምን ማትጋትና ማነቃቃት ይኖርባቸዋል? ይህ ያስፈለገበት ምክንያት፡-

ሀ) ተሳታፊ ህፃናት በአብዛኛው ከዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የመጡ በመሆናቸው የራሳቸውን ህይወት ተግተው በመማር መለወጥ ስላለባቸው፡-

ለ) ተሳታፊ ህፃናት የሚማሩበት ጣቢያዎች ብዙውን ጊዜ ምቹ የመማር ሁኔታ (conducive learning environment) ስለሌላቸው ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡና እንዳይሰንፉ ማነቃቃት አስፈላጊ ነው፡፡

ሐ) በማስተማር መማር ሂደቱ ወቅት ተማሪዎች የተፈገለውን ዕውቀት ክህሎትና አመለካከት በተቀመጠው ዓላማ መሠረት ጨብተው እንዲገኙ ለማድረግ

የሥነ-ልቦና ሳይንቲስቶች ማነቃቃት (motivation) አንድን ነገር ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ ነው ይላሉ፡፡ በዚህ ረገድ ብዙ የሚወሳው የአብርሃም ማስሎው (1970 እ.ኤ.አ) የሰዎች ፍላጎት ደረጃዎች (human needs hierarchy) ማየት አስፈላጊ ነው፡፡




አመቻቾች እያንዳንዱ ህፃን ከእንዴት ዓይነት አኗኗርና የኑሮ ደረጃ መጥቶ በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት እንደሚሳተፍ ማጤን አለባቸው፡፡ ምክንያቱም የህፃኑ መሠረታዊ ፍላጎቶቹ ከሞላ ጎደል ባልተሟሉበት ሁኔታ ተፈላጊውን ዕውቀት መጨበጥ አስቸጋሪ ሊሆንበት ይችላል፡፡ እንዲሁም ህፃናት በአጠቃላይና በተለይ ሴት ህፃናት ተማሪዎች ያለፍርሃት ወደ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ መጥተው መማር አለባቸው፡፡ ምንም ዓይነት ጥቃት ሊደርስባቸው አይገባም፡፡

በመማር ማስተማሩም ወቅት አመቻቾች የአንድን ህፃን ተማሪ መንፈሳዊና አካላዊ ህይወት የሚጎዳ ርምጃ መውሰድ የለባቸውም፡፡

በትምህርታቸው የላቀ ተሳትፎና ውጤት የሚያሳዩ ህፃናት ተማሪዎችን የበለጠ ማትጋት፤ እንዲሁም ደከም ያሉ ተማሪዎችን መደገፍና ማበረታታት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም የተለያየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ተባብረው የመማር ዝንባሌ (Cooperative learning) ማሳደግ አለባቸው፡፡

# ክፍል አምስት

## 5. በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ክፍሎች የመማር ማስተማር ሂደት አደረጃጀትና አመራር፡-

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

አመቻቾች በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የቀረቡትን ጭብጦች ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሻሻል ሊጠቀሙ የሚችሉ የክፍል ውስጥና ውጪ ግብዓቶችን ይለያሉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ስኬታማ የመማር ማስተማር ክንውን የሚሆን የትምህርት መርሐ-ግብር ያዘጋጃሉ፡፡

የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አተገባበር ስኬታማ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና ከሚጫወቱት ዐበይት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የክፍል ውስጥና ውጪ ግብዓቶችን በጥሩ ሁኔታ አደራጅቶ የመጠቀም ጥበብ ወይም ክህሎት ነው፡፡ ግብዓቶችን በጥሩ ሁኔታ መጠቀምና ማስተዳደር መቻል ከጥሩ አመቻቾች ይጠበቃል፡፡ በአጠቃላይ አመቻቾች የክፍል ውስጥ አመራርን (classroom management) ጠንቅቀው መረዳት አለባቸው፡፡ ይህም ህፃናት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለምን ያልተፈለገ ባህርይ ያሳያሉ የሚለውን ጥያቄ ማየት እንዳለብን ያመላክታሉ፡፡ ህፃናት ተማሪዎች አላስፈላጊ የሆነ ባህርይ የሚያሳዩበት ምክንያቶች፡-

**ሀ) ከአመቻቹ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች** (teacher related factors)

- አመቻቹ በቂ የማስተማር ዝግጅት ሳያደርግ ወደ ክፍል ገብቶ የሚያስተምር ከሆነ፤
- አንድ ወይንም የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ ሁልጊዜ በመማር ማስተማር ሂደት የሚያሳትፍ ከሆነ፤
- አንድ ተማሪ ባጠፋው ሁሉንም የሚተች ከሆነ፤
- ሁልጊዜ እየተነጫነጨ የሚያስተምር ከሆነ፤
- በሚሰጣቸው ምሳሌዎች የፆታ፣ የሃይማኖትና የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነት የሚፃረር ሀሳብ ካቀረበ፣
- ሁሌ በወቀሳ መጀመር፣
- በአሽሙር መናገር ወዘተ.

**ለ) ከተማሪዎች ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች** (student related factors)

- አንዳንድ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ሳያስፈቅዱ ከፍተኛ ድምፅ በማሰማት የሚናገሩ ከሆነ፤
- በመማር ማስተማር ሂደት ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ የመቀመጫ ቦታቸውን የሚቀያይሩ ከሆነ ወዘተ. ናቸው፡፡

**ሐ) የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከል ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች** (ABE center- related factors)

በማእከሉ ለመማር ማስተማር ሂደት አመቺ ሁኔታ ከሌለ አንዳንድ ህፃናት ቶሎ የመበሳጨትና አላስፈላጊ የሆነ ባህርይ በክፍል ውስጥ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡

**መ) ከተማሪዎቹ የቤተሰብ አኗኗር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች** (home environment related factors)

አንዳንድ ህፃናት ተማሪዎች ቤተሰባቸው ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች አለመግባባትና ብጥብጥ ወይንም የፍቺ ሂደት ላይ የደረሰ ሁኔታ ካለ ከዚያ ቤተሰብ የሚመጡ ህፃናት ተማሪዎች አግባብነት የሌለው ባህርይ በክፍል ውስጥ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡

**በክፍል ውስጥ አግባብነት የሌላቸው ባህርያትን** (pupil's misbehavior) **መቀነስ ወይንም ማስወገድ የሚያስችሉ ቴክኒኮች የሚከተሉት ናቸው፡፡**

(1) **አሰቀድሞ የመከላከል ቴክኒኮች** (preventive techniques)

- የክፍል ውስጥ ደንቦችን ከህፃናት ተማሪዎች ጋር በመወያየት መቀመር፤
- አመቻቾች በቂ ዝግጅት አድርገው ወደ ክፍል መግባት፤

(2) **እርምት መውሰጃ ቴክኒኮች** (curative techniques)

**ለአመቻቾች ማስታወሻ ፡-**

- አመቻቾች የትምህርት ጊዜን በአግባቡ መጠቀም አለባቸው፤
- የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም፤
- የመማሪያ ክፍልን መስህብነት (attractiveness) ባለው ሁኔታ ማደራጀት፤
- የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን የማዘጋጀትና የመጠቀም ልምድ ማካበት አለባቸው

# ክፍል ስድስት

## 6. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን መጠቀም

**የትምህርቱ ዓላማዎች፦**

አመቻቾች ይህን ክፍል አንብበው ከተረዱ በኋላ፦

- በቂ የትምህርት መርሐ ግብር ዝግጅት በማድረግ የመማር ማስተማሩን ሂደት ያከናውናሉ፤
- የትምህርት መርሐ-ግብር ዓይነቶችን ይለያሉ፤

**በዚህ ክፍል ስር የተካተቱ ንዑሳን ርዕሶች ፡-**

- የትምህርት ዕቅድ ምንነትና አስፈላጊነት፣
- የትምህርት ዕቅድ ዓይነቶች ፣
- የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን መጠቀም

### (6.1) የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዕቅድ ምንነትና አስፈላጊነት

አመቻቾች በራሳቸው በመተማመንና በተቀነባበረ ሁኔታ ማስተማር ይችሉ ዘንድ የትምህርት ዕቅድ (lesson plan) ማዘጋጀት አለባቸው ፡፡

**የትምህርት ዕቅድ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ፡-**

- ዝርዝር የትምህርቱን ዓላማዎች እንዲያቅፍ ተደርጎ ስለሚዘጋጅ አመቻቾች ይህንን ለማሳካት ጥረት እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል፡፡
- በይዘቶች አቀራረብ መካከል ቅደም ተከተል (sequencing) እንዲኖር ይረዳል፤
- አግባብነት ያላቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ቴክኒኮችን ለመጠቀም ይረዳል፤
- አግባብነት ያላቸውን የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን በቀላሉ በአካባቢው ከሚገኙ ማቴሪያሎች አዘጋጅቶ ለመጠቀም ይረዳል፤
- የተሳታፊ ህፃናት ተማሪዎችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ይረዳል፤
- ሥርዓት ያለው የትምህርት አቀራረብ እንዲኖር ያግዛል፤
- የሰው ጉልበት፣ ጊዜና ቁሳቁስ በከንቱ እንዳይባክን ይረዳል፤

- አመቻቾች እንዲያስተምሩ የተመደበላቸውን የትምህርት ዓይነቶች በአግባቡ በማካሄድ እንዲያጠናቅቁ ይረዳል፤
- የህፃናት ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ደረጃን ለመረዳት የሚያስችሉ መመዘኛዎችን ለማዘጋጀት ይረዳል፤

(6.2) **የትምህርት መርሐ- ግብር ዓይነቶች**

አማራጭ መሠረታዊ የትምህርት መርሐ-ግብርን በሦስት ዓይነቶች ከፍሎ ማየት ይቻላል፤

(1) **ወርሐዊ የትምህርት መርሐ-ግብር** (monthly lesson plan)

ይህ ዓይነት የትምህርት መርሐ-ግብር አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ለማመቻቸት ከተመደበው ጊዜ ውስጥ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሊሸፈኑ የሚገባ ይዘቶች ተተምነው የሚነደፉበት ነው፡፡

**ወርሐዊ የትምህርት መርሐ-ግብር ፎርማት**

| ዋና ርዕስ | የክፍለ ጊዜ ብዛት | ዓላማ | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴ | የትምህርት ማስተማርያ መርጃ መሣርያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |

(2) **ሣምንታዊ የትምህርት መርሐ-ግብር** (weekly lesson plan)

ለአንድ ወር ከተመደበው የትምህርት ይዘት ውስጥ ለአንድ ሳምንት የሚሆነውን ያህል ይዘት ተጨልፎ የሚነደፍበት መርሐ- ግብር ነው፡፡ (የትምህርት ሚኒስቴር ታህሣሥ 2001-50)

**ሣምንታዊ የትምህርት መርሐ-ግብር ፎርማት**

| ዋና ርዕስ | የክፍለ ጊዜ ብዛት | ዓላማ | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴ | የትምህርት ማስተማርያ መርጃ መሣርያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |

## ( 3) ዕለታዊ የትምህርት መርሐ ግብር (daily lesson plan)

የትምህርት መስጫ ጣቢያው ስም--------------------------------------------------

የትምህርት ዓይነት -------------------------------------------------------------

የአመቻቹ/ቹ/ ስም --------------------------------------------------------------

የተሳታፊ ህፃናት ተማሪዎች ብዛት ወንድ -------- ሴት---------------------------------

ትምህርቱ የሚሰጥበት ደረጃ (level) -----------------------------------------------

ትምህርቱ የሚሰጥበት ቀን ---------------------------------------------------------

1. የዕለቱ የትምህርት ርዕስ /ርዕሶች ---------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------:
2. ይዘት/ይዘቶች-----------------------------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------፡፡

3 ዓላማ/ዓላማዎች

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

__________________________________________________------------::

4 አቀራረብ

4.1. የማስተማር ዘዴ/ዘዴዎች

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

_______________________________________________----------::

4.2 በአመቻቿ/ቹ የሚከናወን ተግባሮች

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

__________________________________________________---------------::

4.3 ተሳታፊ ተማሪዎች የሚያከናውኑት ተግባሮች

5. በስራ ላይ የሚውሉ፡፡

5.1. የትምህርት መሣሪያዎች ________________________________________-

---------------------

________________________________________________________________

-----------------------------------------------------፡፡

5.2. የማስተማሪያ መረጃ መሣሪያዎች ______________________________________

-------------------

________________________________________________________________

--------------------------------------------------፡፡

6. ምዘና

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________------------------------

-------------------------------------------------------------::

7. ስለዕለቱ ትምህርት የአመቻቹ/ቿ አስተያየት

________________________________________________________________________

______________________________________________________ ::

## (6.3) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም

የትምህርት መርጃ መሣርያዎች (instructional media) የምንላቸው ‹‹የአንድን ትምህርት ይዘት ግልፅ ለማድረግና ለማበረታታት እንዲያግዙ በገላጭነት የሚቀርቡ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ማለት ነው›› (የትምህርት ሚኒስቴር ታህሳስ 2001 -42)

ሀ) የህፃናት ተመሪዎችን የክፍል ደረጃ (level) ፣ ዕድሜና ባህል መገንዘብ አለባቸው፤

ለ) ህፃናት ተማሪዎች ወደ ማዕከሉ (ABE center) ሲመጡ ይዘው የመጡትን ልምድ መገንዘብ፤

ሐ) የተማሪዎቹን የተለያዩ ችሎታዎች ለመገንዘብ ጥረት ማድረግ (multiple intelligence) በመቀጠልም ከትምህርቱ ዓላማ ጋር የሚዛመድ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻም የትምህርት መርጃ መሣርያውን በመማር ማስተማሩ ሂደት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

# ክፍል ሰባት

## (7) የአማራጭ የትምህርት መስጫ ጣቢያ የሥራ ዕቅድ አዘጋጃጀት

የትምህርት ቤት ዕቅድ በሁለት መንገድ ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፡፡

1- አጠቃላይ የትምህርት ቤቱ አመራርና አስተዳደር የሥራ ዕቅድ
2- የመማር ማተስማር የሥራ ዕቅድ(Lesson Plan)

የመማር ማስተማር የሥራ ዕቅድ ምንነትና አቀራረብ በማኑዋሉ ክፍል ስድስት የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ተብሎ ለብቻው ቀርቧል፡፡ ለዕቅድ ዝግጅት የሚያስፈልጉ ፎርሞችም በዚሁ ክፍል ተገልጿል፡፡ስለሆነም አሁን ትኩረት የምናደርገው በአጠቃላይ የትምህርት ቤት የሥራ አመራርና አስተዳደር ዕቅድ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

ዕቅድ ለምናከናውናቸው ተግባራት አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዕቅዱን ለመተግበር የሚያስፈልጉን ግብዓቶች ዓይነትና ብዛት ( ምሳሌ፡- ጊዜ፣ ገንዘብ ፣ መሣሪያ፣ የሰው ኃይል ወ.ዘ.ተ) በዝርዝር የሚያስረዳ ሰነድ ነው፡፡ጊዜን መሠረት በማድረግ የሚያዘጋጅ ዕቅድ ሊከፈል ይችላል፡፡ በትምህርት ቤት ደረጃ የሚዘጋጅ ዕቅድ ብዙውን ጊዜ ለአንድ ዓመት ስለሚታቀድ የአጭር ጊዜ ዕቅድ እንለዋለን፡፡ ከ2-5 ዓመታት ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ የመካከለኛ ጊዜ ከ6-10 ዓመት የሚፈጅ ከሆነ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ብሎ መክፈል ይቻላል፡፡ በዕቅድ አዘገጃጀት ወቅት ልንከተላቸው የሚገቡን ሂደቶች

1- አጠቃላይና ንዑስ ተግባራትን መለየት
2- የተግባራቱን ዓላማዎች መለየት
3- ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ጊዜ መወሰን
4- የምንሰራቸው ያቀድናቸውን ተግባራት መጠን መወሰን
5- ለዕቅዱ ተግባራዊነት አስፈላጊ የሆነውን የገንዘብ፣ የማቴሪያል እና የሰው ኃይል መጠን መወሰንና መመደብ
6- የእቅድ አፈፃፀም ስትራቴጅ ማዘጋጀት
7- የክትትል ግምገማና ሪፖርት አቀራረብ መንገዶችን መወሰን

የሥራ ዕቅድ ከማዘጋጀት በፊት የሚከተሉትን ሁኔታዎች መገምገም ያስፈልጋል፡፡

ሀ/ ቀደም ሲል የነበረውን ዓመታዊ ዕቅድ ሪፖርት ግምገማ ውጤት መመልከትና የተስተዋሉ ድክመቶች፣ ጠንካራ ጎኖች፣ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች መለየት

ለ/ የአሁኑን የት/ቤት ሁኔታ መተንተንና መከለስ (Analysis & review of current school situation) ይህም ማለት አሁን ያሉትን አመቻቾች ብዛትና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች፣ የመማሪያ ክፍሎች ብዛትና ያሉበት ሁኔታ፣ የተማሪዎች መፃህፍት ብዛት፣ የተማሪዎች ብዛት፣ የመቀመጫ ብዛት፣ የሰሌዳ ብዛት፣ የት/ቤቱ ጥሬ ገንዘብ መጠን፣ ወ.ዘ.ተ

ሐ/ የመንግስት መሣሪያዎችና ሰነዶችን መዳሰስ ይህም ማለት የመንግስት የልማት ዕቅድ፣ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ የትምህርት ሴክተር ልማት ፕሮግራም(ESDP)የተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ፣ የትምህርት ቤት መሻሻል መመሪያ (School Improvement Guideline) ፣ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ዕቅድ፣ የትምህርት ወቅታዊ ካላንደር(Seasonal Calendar)፣ ልዩ ልዩ ኦፊሻላዊ ደብዳቤዎች፣ መመሪያዎች ወ.ዘ.ተ

የሥራ ዕቅድ ማቅረቢያ ፎርም

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት ዝርዝር | መለኪያ | መጠን | አስፈላጊ ገንዘብ መጠን(በጀት) | አስፈላጊ የሆነ ሰው ኃይል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | | |
| 2. | | | | | | |
| 3. | | | | | | |
| 4. | | | | | | |
| 5. | | | | | | |
| 6. | | | | | | |
| 7. | | | | | | |
| 8. | | | | | | |
| 9. | | | | | | |

የሥራ ዕቅድ ድርጊት መርሃ ግብር

| ተ.ቁ | የታቀዱ ተግባራት ዝርዝር | የዕቅድ ክንውን መጠን በሩ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 1. | | | | | |
| 2. | | | | | |
| 3. | | | | | |
| 4. | | | | | |
| 5. | | | | | |
| 6. | | | | | |
| 7. | | | | | |
| 8. | | | | | |
| 9. | | | | | |
| 10. | | | | | |

ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ የሚዘጋጀው የ3ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ከተገመገመ በኋላ መሆን አለበት፡፡ ይህም ለቀበሌው ትምህርትና ስልጠና ቦርድ እንዲሁም ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት መቅረብ ይገባዋል፡፡ የድርጊት መርሃ ግብሩን ሌሎች ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ከ4ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ጋር መቅረብ የችላሉ፡፡

## 7.1 የትምህርት ቤት መረጃ አያያዝ (School Management Infromation System)

የትምህርት ቤት መረጃ ማለት የተከናወኑ ተግባራትን አስመልክቶ የሚሰበሰብ፣ የመተንተን፣ የማሰራጨት፣ የማከማቸትና በተፈለገ ጊዜ እንደገና መልሶ መመልከት የሚቻልበትን ሂደት ማደራጀት ነው፡፡ መረጃ የትምህርቱን ሥራ ውጤታማነትና ስኬታማነት ለመለካት ያገለግላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የትምህርት አመራርና አስተዳደር አስፈላጊ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍና ርምጃዎችን በቀጣይነት ለመውሰድ መረጃን እንደ መሠረት አድርጎ ይጠቀምበታል፡፡ ይህም ማለት መረጃ ውሳኔ መስጠት በሚያስፈልጉ ግብዓቶች መካከል እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መረጃ የሚከተሉት ዋና ዋና ጥቅሞች አሉት፡፡

1- ስለትምህርት ቤት የሰው ኃይል ተፈላጊ መረጃ ይሰጣል( አመቻቾች ፣ ተማሪዎች ፣ የኮሚቴ አባላት)
2- ለትምህርት ጥናትና ምርምር እንደ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል፡፡
3- የመማር ማስተማርና ሌሎች ተጓዳኝ ስራዎች የታለመላቸውን ግብ መምታት መቻላቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡
4- የተማሪዎችና ሌሎች ሰዎችን ሥራ ውጤት ለመዘገብ ያስችላል
5- ለበላይ አካል ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ በሪፖርት መልክ ማቅረብ
6- በትምህርት አመራርና አስተዳደር ሥራ በቀጣይነት ለሚሳተፉ ሰዎች በቂ የሆነ መሠረት ለመጣል ያስችላል
7- በጊዜው የሚገኘውን ሀብት በማወቅ ለወደፊት እቅድ ግብዓት ይሆናል፡፡
8- የትምህርት መስጫ ጣቢያውን የወደፊት ሥራ ለማሻሻል ይረዳል፡፡

የትምህርት ቤት መረጃ ምንጮች

- የት/ቤት መዛግብት
- አመቻቾች
- ተማሪዎች
- ወላጆች
- መማሪያ ክፍሎች
- የት/ቤት ግቢ እና አካባቢው

የት/ቤት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የት/ቤት መረጃ ከተለያዩ ምንጭ ለመሰብሰብ የሚያግዙ የተለያዩ መሣሪያዎች አሉ፡፡ እነዚህም፡

- ቃለ ምልልስ( Interview)
- መጠይቅ( Questionnaire)
- የምልክት መመሪያ(Observation cheek-list)
- ሪፖርቶች
- የመዛግብት ዳሰሳ( Document analysis)
- ፈተናዎች

- ግራፎች/ቻርቶች
- የተለያዩ ፎርሞች

7.2 **የመረጃ ዓይነቶች**

1- *መዘርዝራዊ መረጃ* (Qualitative data)

2- *አኃዛዊ መረጃ* (Quantitative data)

**የትምህርት ቤት መረጃ የሚያካታትታቸው ነገሮች**

የትምህርት ቤት መረጃ የሚከተሉት ጉዳዮችን ማካተት አለበት

i. የተማሪዎች ገጽታ (Student Profile)- ስም ፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ የክፍል ደረጃ፣ የተማሪዎች ብዛት በፆታ ወ.ዘ.ተ
ii. የአመቻች መረጃ- ስም፣ ጾታ ፣ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ ፣ የትምህርት ዓይነት፣ የሥራ ልምድ፣ የቅጥር ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ወ.ዘ.ተ
iii. የመማሪያና ሌሎች አገልግሎት ሰጭ ክፍሎች ብዛት
iv. ስለትምህርት ቤቱ የቦታ ስፋት እና ስለሚገኙበት ንብረቶች ሁኔታ
v. ስለመማሪያ መፃህፍት ብዛት ሌሎች ንብረቶች ዓይነትና ብዛት፣ አሁን ያሉበት ሁኔታ
vi. ስለትምህርት ቤቱ ወጪና ገቢ ሂሳብ
vii. ዕድሜያቸው ለትምህርት ስላልደረሱ ህፃናት ብዛት ( በት/ቤቱ አካባቢ የሚገኙ)
viii. በአካባቢው የሚገኙ የጎልማሶች መረጃ- ስም፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ የሥራ ዓይነት፣ የጎልማሶች አጠቃላይ ብዛት፣ ወ.ዘ.ተ
ix. በአካባቢው ስለሚገኝ የህዝብ ብዛት በጾታ
x. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያው አስተዳደር ኮሚቴ አባላት መረጃ ስም፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣የሥራ መስክ፣ በኮሚቴው ያላቸው ኃላፊነት ፣ ያበረከቱት አስተዋጽኦ፣ ወ.ዘ.ተ

**በትምህርት ቤት የሚገኙ መዛግብትና ማህደሮች**

ተፈላጊውን መረጃ በተፈለገው ጊዜ ለማግኘት እንዲቻል የሚከተሉት መዛግብትና ማህደሮች በት/ቤት ተደራጅተው መገኘት አለባቸው፡፡

ሀ- የአዲስ ተማሪዎች መዝገብ

ለ- የእያንዳንዱ ተማሪ የግል ማህደር

ሐ- የአመቻቾች የግል ማህደር

መ- የገቢና ወጪ ደብዳቤ መዝገብ

ሠ- የተከናወኑ ተግባራት መመዝገቢያ

ረ- የወጪና ገቢ መዝገብ

ሰ- የት/ቤት ቋሚ ንብረት መዝገብ

ሸ- የአመራርና አስተዳደር ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ መዝገብ

ቀ- የአመቻቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ መዝገብ

በ - የተለያዩ ክበባት ሥራ መዝገብ

ተ- የተማሪዎች ውጤት መመዝገቢያ ደብተር እና ሮስተር

ቸ- የተማሪዎች ስም መጥሪያ መዝገብ

ከ- በእያንዳንዱ ትምህርት ዓይነት የተማሪዎች ባህርይ ለውጥ መመዝገቢያ

አ- የአመቻቾች የሰዓት ፊርማ

ነ- የአስተያየት መስጫ መዝገብ

ኘ- የሱፐርቪዥን አስተያየት መስጫ መዝገብ

ኀ- የአመቻቾች የሥራ አፈፀም ውጤት መመዝገቢያ

የተማሪዎች መረጃ መመዝገቢያ ፎርም

የት/ቤቱ ሰም፡-______________________ ዓ.ም_________________

| ተ.ቁ | የተማሪው ስም ከነአያት | ጾታ | ዕድሜ | ክፍል | የአካል ጉዳተኝነት ዓይነት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | | |
| 2. | | | | | | |
| 3. | | | | | | |
| 4. | | | | | | |
| 5. | | | | | | |

የአመቻቾች መረጃ መመዝገቢያ ፎርም

| ተ.ቁ | ስም ከነአያት | ጾታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | የቅጥር ዘመን | የደመዎዝ መጠን | የመታወቂያ ቁጥር | የሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | | | | |
| 2. | | | | | | | | |
| 3. | | | | | | | | |
| 4. | | | | | | | | |
| 5. | | | | | | | | |
| 6. | | | | | | | | |
| 7. | | | | | | | | |
| 8. | | | | | | | | |
| 9. | | | | | | | | |
| 10. | | | | | | | | |

የተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ባህርይ ለውጥ መከታተያ ፎርም(ለተከታታይ ምዘና የሚያገለግል)

| ተ.ቁ | የተማሪው ስም | ጾታ | ዕድሜ | ተማሪው ማሻሻል ያሳየበት/ያዳበረው ችሎታ | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | መፃፍ | ማንበብ | መናገር | መስማት | |
| 1. | | | | | | | | |
| 2. | | | | | | | | |
| 3. | | | | | | | | |
| 4. | | | | | | | | |
| 5. | | | | | | | | |
| 6. | | | | | | | | |
| 7. | | | | | | | | |
| 8. | | | | | | | | |
| 9. | | | | | | | | |
| 10. | | | | | | | | |

## የተማሪዎች የሂሳብ ትምህርት ባህርይ ለውጥ መከታተያ ፎርም

| ተ.ቁ | የተማሪው ስም | ጾታ | ዕድሜ | ተማሪው ማሻሻል ያሳየችበት/ያዳበረችው ችሎታ | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | መደመር | መቀነስ | ማብዛት | ማካፈል | |
| 1. | | | | | | | | |
| 2. | | | | | | | | |
| 3. | | | | | | | | |
| 4. | | | | | | | | |
| 5. | | | | | | | | |
| 6. | | | | | | | | |
| 7. | | | | | | | | |

# የዋቤ መፃህፍት

_MOE (2012) Education Statsitics Annual Abstract 2004 ( 2011/2012) . Addis Ababa

TGE (1994). The new Education and Traning Policy. Addis Ababa

World Bank (2005) Education in Ethiopia: Strengthening the Foundation for Sustainable Progress

የትምህርት ሚኒስቴር ( 2004 ዓ.ም) የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአፍ መፍቻና የእንግሊዝኛ ቋንቋ አጥጋቢ የመማር ብቃትና መርሐ ትምህርት ሰነዶች፤

የትምህርት ሚኒስቴር (2004 ዓ.ም) የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የሂሳብና የአካባቢ ሳይንስ አጥጋቢ የመማር ብቃትና መርሐ ትምህርት ሰነዶች